RESEARCH PROGRAM ON Livestock

More meat, milk and eggs by and for the poor

# ሥነ ፆታዊ ግንኙነቶችን በመለወጥ በደጋማ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚኖሩ የትናንሽ አመንዣኪ የቤት እንስሳት አርቢ ገበሬዎች የሚደርስባቸውን ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን  አደጋ መቀነስ

## ለማኅበረሰብ ውይይት አመቻቾች የተዘጋጀ መመሪያ

ማሙሻ ለማ[1] አኔት ሙለማ[1] ወሌ ቂናቲ[2] እና ባርብራ ዊላንድ[1]

1. ዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI)
2. ዓለም አቀፍ የቆላ አካባቢ ምርምር ማዕከል (ICARDA)



ኖቬምበር 2018

ILRI INTERNATIONAL LIVESTOCK RESEARCH INSTITUTE

ICARDA Science for resilient livelihoods in dry areas

ዓለም አቀፍ የግብርና ምርምር ኮንሰርትየም (CGIAR) ለወደፊት የምግብ ዋስትና አስተማማኝ እንዲሆን ምርምር የሚያደርጉ ድርጅቶችን የሚያስተባብር ዓለም አቀፍ ትብብር ነው፥ ፥ የኮንሰርትየም ቡድኑ በከብቶች ላይ የሚያደርገው የጥናትና የምርምር ፕሮግራም ምርምርን መሠረት ያደረጉ መፍትሔዎችን አነስተኛ ይዞታ ላላቸው ገበሬዎች፣ ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል አርብቶ አደሮች በመስጠት ዘላቂና ችግርን የሚቋቋሙ አምራች ድርጅቶች ወደ መሆን ተሸጋግረው የሚቀጥለውን ትውልድ ለመመገብ እንዲችሉ ማገዝ ነው። በተጨማሪም ዘላቂ በሆነ መንገድ የእንስሳትን ምርታማነትንና ትርፋማነትን በመጨመር በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ብዛት ያለው ስጋ፣ ወተትና እንቁላል በመጠነኛ ዋጋ እንዲገኙ ማድረግ ነው።

ይህ ፕሮግራም አምስት ዋና ዋና ምርምር ተቋም አጋሮችን የሚያጣምር ነው። እነሱም በእንስሳት ላይ የሚሠራው ዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI) ፣ በከብቶች መኖ ላይ የሚሰራው ዓለም አቀፍ የትሮፒካል ምርምር ማዕከል (CIAT) ፣ በትናንሽ አመንዣኪ እንስሳት ላይና በደረቅ መሬት ስርዓቶች ላይ የሚሰራው ዓለም ዓቀፍ የቆላ አካባቢ ምርምር ማዕከል (ICARDA) ፣ በተለይም በእንስሳት ጤናና በጀኔቲክስ ላይ ጥልቅ ዕውቀት ያለው የስዊድን የግብርና ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ (SLU) እና ምርምርን ከልማትና ፈጠራን ከማሳደግ ሒደት ጋር የሚያገናኘው የጀርመን ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (GIZ) ናቸው።

ፕሮግራሙ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለዓለም አቀፍ የግብርና ምርምር አማካሪ ቡድን ትረስት ፈንድ አስተዋፅዖ ለሚያደርጉ እርዳታ ሰጭዎችንና ድርቶችን ሁሉ ምስጋና ያቀርባል።

©2020

ይህን ህትመት ለመጠቀም ፍቃድ የሚሰጠው በ the Creative Commons Attribution 40 በተባለ ዓለም አቀፍ ፈቃድ ሰጭ በኩል ነው። ይህን ፈቃድ ለማየት https://creativecommons.org/licenses/by/4.0 ይመልከቱ።"

ባለቤትነት - በተለይ ካልተገለጸ በስተቀር ይህንን ህትመት መቅዳትና እንደገና በማንኛውም ዓይነት መንገድ ወይንም ፎርማት ማሰራጨትና ንግድን ጨምሮ ለማንኛውም ዓላማ ማሻሻልና ባለው ላይ መጨመር የሚቻል ሲሆን የተጠቀሱትን ለማድረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው።

የሕትመት ውጤቱን ባለቤት ማሳወቅ። የሕትመት ውጤቱን ባለቤት ማሳወቅ ማለት ግን በምንም ዓይነት መንገድ አታሚው ወይንም ፀሐፊዎቹ በዚህ መልክ የተዘጋጀውን የሕትመት ውጤት አፅድቀዋል ማለት አይደለም።

*Patron: Professor Peter C Doherty AC, FAA, FRS*
*Animal scientist, Nobel Prize Laureate for Physiology or Medicine–1996*

Box 30709, Nairobi 00100 Kenya
Phone +254 20 422 3000
Fax +254 20 422 3001
Email ilri-kenya@cgiar.org

ilri.org
*better lives through livestock*

ILRI is a CGIAR research centre

Box 5689, Addis Ababa, Ethiopia
Phone +251 11 617 2000
Fax +251 11 667 6923
Email ilri-ethiopia@cgiar.org

*ILRI has offices in East Africa • South Asia • Southeast and East Asia • Southern Africa • West Africa*

# ይዘት


| | |
|---|---|
| ክፍል 1፣ ዳራ | 1 |
| ክፍል 2፣ የአጠቃቀም ዘዴዎች | 4 |
| ክፍል 3፣ ማቅረብ | 9 |
| አባሪዎች | 37 |
| ማጣቀሻዎች | 47 |

# ክፍል 1፡ ዳራ

## መግቢያ

በከብት አያያዝ ሥራ ውስጥ የሚተገበሩ ልማዳዊ የሥነ ጾታ መመሪያዎችና የሥራ ክፍፍሎች ሴቶችንና ወንዶችን በተለያየ ደረጃ ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች ያጋልጣሉ። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ለበሽታዎቹ ተጋላጭ ከመሆናቸውም በላይ ሲታመሙ ከወንዶች የቤተሰቡ አባላት እኩል እንክብካቤ አያገኙም (kristjanson et al. 2010)።

በኢትዮጵያ ውስጥ የዓለም አቀፍ የግብርና ምርምር ኮንሰርትየም (CGIAR) የከብቶች ምርምር ፕሮግራም በተቋም ደረጃ በስርዓተ ጾታ አቅም ግንባታ ላይ ያተኩራል። እስካሁን ድረስ በሕብረተሰብና በቤተሰብ ደረጃ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በመስራት ገዳቢ የሆኑ ልማዳዊ የሥነ ጾታ መመሪያዎችን በማስወገድና የስሥርዓተ ፆታ ግንኙነቶችን በመለወጥ ከእንስሳት ወደ ሰዎች የሚተላለፉ በሽታዎች የሚያስከትሉትን አደጋ የመቀነስ ስራዎች አልተሰሩም፡ ፡ የማሕበረሰቡ አባላት በተለምዶ የሚተገበረውን የሴቶችንና የወንዶችን የሥራ ክፍፍል እንዲሁም ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦችን ባህላዊ አያያዝ እንደ ትክክለኛ አድርገው ይቀበሉታል። ይህም ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች የበለጠ ተጋላጭ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

የማህበረሰብ ውይይት የማህበረሰቡ አባላት እጅግ ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮቻቸው ላይ እርስ በርስ እንዲወያዩ የሚያደርግ አሳታፊ አቀራረብ ነው። በዚህ ውይይት ሂደት የማህበረሰቡ አባላት በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አስተሳሰብ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲለወጡ ማድረግ ይቻላል። የማህበረሰብ ውይይት ዓላማ ግንዛቤን በመፍጠር ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ገዳቢ የሆኑ የስርዓተ ፆታ ግንኙነቶችን ለመለወጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመውሰድ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች የሚያስከትሉትን አደጋ መቀነስ ያስችላል።

# የማህበረሰብ ውይይት አስፈላጊነት

የማህበረሰብ ውይይት የማህበረሰቡን አባላት አንድ ላይ በማሰባሰብ በከብት ማርባት ሂደት ውስጥ የስርዓተ ፆታ ግንኙነትና ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች ያላቸውን ግንኙነቶች እንዲያስቡ፣ እንዲወያዩና እንዲያጤኑ የሚያበረታታ ሂደት ነው።

የማህበረሰብ ውይይት የሚደረገው ማህበረሰቡ ችግሩ የእርሱ መሆኑን ከተረዳና ከተቀበለ በተናጥልና በጋራ በመሆን በስርዓተ ጾታና በእንስሳት ጤና ላይ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት ዕውቀትና ችሎታ አለው በሚል እሳቤ ላይ በመመርኮዝ ነው።

ይህ አቀራረብ ሴቶችንና ወንዶችን ወደ ውይይት በማምጣት በተለይም አድሏዊ የሥርዓተ ፆታ ልምዶችን፣ አመለካከቶችን፣ ባሕሪዎችን፣ ድርጊቶችን እንዲሁም የኃይል አለመመጣጠን እንዲያጤኑና ጥያቄ ውስጥ እንዲያስገቡ ብሎም እንዲለወጡ ያደርጋል። እንደነዚህ ዓይነት ለውጦች ደግሞ በሴቶች ሚና ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚፈጥሩ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ ሴቶች በቤት እንስሳትና በሌሎች ሀብቶች ላይ ያላቸውን ሚናና ቁጥጥር በተመለከተ ያሉትን አላስፈላጊ ግንዛቤዎችን ይቀንሳል። በሴቶች ውሳኔ ሰጭነት፣ የሥራ ጫና፣ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወርን፣ በከብት እርባታ በቤተሰብ ውስጥ የሚደረገውን የሥራ ክፍፍል በተመለከተ አዎንታዊ ውጤት ይኖረዋል።

የማህበረሰብ ውይይት የሚመቻቸው የሚታዩ ቁሳቁሶችን፣ ሚና ትወናዎችን፣ ታሪክ ነገራን፣ የቪዲዮ ክሊፖችንና ሌሎች መስተጋብራዊ፣ አሳታፊና ለማሰላሰል የሚረዱ ቴክኒኮች በመጠቀም ነው። እነዚህ ቴክኒኮች ውይይቶችን ለመጀመርና ለማነቃቃት፣ የስርዓተ ፆታ ሚናዎችን፣ የስርዓተ ፆታ ልምዶችን፣ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ያሉ ግንዛቤዎችን እንዲሁም ድርጊቶችን ለማጤን/ለማስተዋል ይጠቅማሉ። የማህበረሰብ ውይይት ሂደትም በከብቶች አያያዝና ከእንስሳት ወደ ሰዎች የሚተላለፉ በሽታዎች በተመለከተ የማህበረሰቡን አባላት ዕውቀት፣ አመለካከትና ድርጊት ለመለወጥ ያስችላል።

እነዚህን ለውጦች ቅድመና ድህረ የዕውቀት፣ የአመለካከትና የድርጊት ግምገማ በማድረግ ለይቶ መሰነድ ያስፈልጋል። በተጨማሪም የተለወጡ ተግባራትን፣ ሴቶችና ወንዶች በሚሠሩት ሥራ ያገኙትን ተቀባይነት፣ በተለወጠው የወንዶችና የሴቶች የሥራ ክፍፍል የጊዜ ምደባ እንደሁም በአደገኛ ሁኔታ ጊዜ (በተለይም የእንስሳት ተዋፅዖ ምግቦችን አያያዝን በተመለከተ) የተደረጉ የባህሪ ለውጦች ካሉ ክትትል ተደርጎባቸው በማህበረሰብ ውይይት ወቅት ሊነሱ ይገባል (መሣሪያዎች የሚለውን አባሪ ይመልከቱ)። ይህ መመሪያ በአራቱ የስርዓተ ፆታ ግንኙነቶች ልኬቶች ማለትም በስርዓተ ፆታ የሥራ ክፍፍል፣ በንብረት ላይ ያላቸውን ቁጥጥርና ጥቅም፣ ውሳኔ ሰጭነትና የስርዓተ ፆታ ልምዶች ላይ ያተኩራል።

# ስለ መመሪያው

ለማህበረሰብ ውይይት ስኬታማነት አመቻቾች የሚያከናውኗቸው ጥራታቸውን የጠበቁ የማመቻቸት/የማሳለጥ ሂደቶች ቁልፍ ሚና ይኖራቸዋል።

ይህ የማህበረሰብ ውይይት መመሪያ አመቻቾች ከማህበረሰቡ ጋር በተሳካ ሁኔታ ተወያይተው ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንፃር የሥርዓተ ፆታ ግንኙነት ምን ድርሻ እንዳለው ለማሳወቅና አመለካከታቸውና ድርጊቶቻቸው እንዲቀይሩ ለመርዳት የተዘጋጀ ነው።

ይህ መመሪያ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላፉ በሽታዎችን በተመለከተ የሚደረጉ የማህበረሰብ ውይይቶችን ለማደራጀት፣ ለማመቻቸትና ለመሰነድ የሚያስችሉ የሂደት መመሪያዎችን፣ አሳታፊ መሳሪያዎችን፣ ቴክኒኮችንና ጠቃሚ ምክሮችን ይሰጣል። የማህበረሰብ ውይይት መመሪያው ዓላማ የማህበረሰቡን አባላት በማነቃቃት በኢትዮጵያ በከብት እርባታ መስክ የሚታዩትን በስርዓተ ፆታ ላይ የተመሰረቱና ገዳቢ ልምዶችን በመጋፈጥ በእኩልነት ላይ የተመሰረቱ ልምዶችን በዘላቂነት በስራ ላይ እንዲያውሉ ማድረግ ነው።

የማህበረሰብ ውይይት የማመቻቸት መመሪያው ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች የያዘ ነው። እነዚህም መግቢያ፣ የዘዴ ዳራ እና የሕብረተሰብ ውይይት ማስፈፀሚያ ሂደቶች ናቸው።

የመግቢያው ክፍል የስርዓተ ፆታ ግንኙነትን፣ የእንስሳት ጤናንና ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች ያለውን ሁኔታ ይገልጻል። መመሪያው በከብት ዕርባታ መስክ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንፃር የማህበረሰብ ውይይትን በመጠቀም እንዴት ገዳቢ የሆኑ የስርዓተ ፆታ ግንኙነቶችን ለመቀየር እንደሚቻል ያሳያል።

ሁለተኛው ክፍል የዘዴ ዳራውን ያሳያል። በሌላ አገላለፅ የማህበረሰብ ውይይቶችን ለማመቻቸትና ለመሰነድ የሚረዱ አሳታፊ ዘዴዎችንና መሳሪያዎችን ይገልጻል።

የመጨረሻው ክፍል በማሕበረሰብ ውይይቱ ወቅትና ከውይይቱ በኋላ ደረጃ በደረጃ መደረግ ያለባቸውን ክንውኖች ይገልጻል። አመቻቾች ውይይቶችን በሚያሳልጡበትና ማስታወሻ በሚወስዱበት ጊዜ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን ቴክኒኮችና ሌሎች ተጨማሪ ዕውቀት ሊሰጧቸው የሚችሉ ተጨማሪ ንባቦችም ተካተዋል። በተጨማሪም አባሪዎች የማህበረሰብ ውይይት ሒደትን ለማመቻቸትና በሰነድ ለመያዝ የሚረዱ መመሪያዎችን አካተዋል፡

# የትምህርቱ ግብና አላማ

በዚህ መመሪያ አማካይነት አመቻቾች የሚከተሉትን ትማራላችሁ።

- የማህበረሰብ ውይይት ምን እንደሆነና ለምን እንደሚጠቅም
- በማህበረሰብ ውይይት ወቅት የምንጠቀምባቸው ዘዴዎችና ሂደቶች

የማህበረሰብ ውይይት መመሪያ ግብ የውይይቱ አመቻቾች በከብት እርባታ ሥራ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉትን ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በተለይ በስርዓተ ፆታ ግንኙነት ርዕስ ላይ የሚደረጉ የማህበረሰብ ውይይቶችን ለማቀድ፣ ለመተግበርና፣ ለመሰነድ የሚያስችላቸውን ዕውቀትና ክህሎት ለማስጨበጥ ነው።

አመቻቾች ይህንን መመሪያ በትክክል ከተጠቀሙ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ማከናወን ይችላሉ።

- ስለ ስርዓተ ጾታ ግንኙነት በማኅበረሰቡ ውስጥና ከቤተሰቦቻቸው ጋር አስበው ይነጋገራሉ።
- የበሽታ ከእንስሳት ወደ ሰው የመተላለፍ አደጋን ከስነ ፆታ ሚና አንፃር በመወያየት ይመረምራሉ።
- የሥርዓተ ፆታ ግንኙነትን፣ ውሳኔ ሰጭነትንና ከእንስሳት ወደ ሰዎች ስለሚተላለፉ በሽታዎች ያላቸውን ግንዛቤ፣ አመለካከትና ድርጊት በመፈተሽ ትክክለኛነቱን ይመረምራሉ።
- ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፉ በሽታዎች ዙርያ ባሉ ጥያቄዎች ላይ ይወያያሉ
- የስርዓተ ጾታ ግንኙነቶችን በመለወጥ በቤተሰብና በማኅበረሰብ ደረጃ የሚከሰቱትን ከእንስሳት ወደ ሰውና ከሰው ወደ እንስሳት የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ዕቅዶችንና የድርጊት መርሃ ግብሮችን ይነድፋሉ።

# የትምህርቱ ይዘት

- የስርዓተ ጾታ ሚና በከብት እርባታና ግብይት
- ሴቶች የከብት ሀብትን በባለቤትነት ስለመያዝ ስለመቆጣጠር ያሉ አመለካከቶችና ግንዛቤዎች
- ከእንስሰሳት ወደ ሰው በሚተላለፍ በሽታዎች ላይ ያለው ዕውቀት፣ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች ከስርዓተ ጾታ አንፃር
- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንፃር ያሉ ተቋማዊና መዋቅራዊ ሁኔታዎች

# ክፍል ሁለት፡ የአጠቃቀም ዘዴዎች

## የዘዴዎች፣ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች አጠቃላይ ዕይታ

ይህ ክፍል የማህበረሰብ ውይይቶችን አቅደን በምናዘጋጅበት ዘዴ ላይ ያተኩራል። አጠቃላይ አቀራረቡንና የተወሰኑ አሳታፊ የሆኑ ዘዴዎችን ይገልጻል። አመቻቾች በእያንዳንዱ ርዕስ ዳራና አውድ ላይ በመመስረት የተለያዩ በጋራ የሚተገበሩ የማህበረሰብ ውይይት ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ።

ሆኖም የማህበረሰብ ውይይት አመቻቾች ዘዴዎችን በሚተገብሩበት ወቅት የፈጠራ ችሎታቸውን መጠቀምና ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ማገናዘብ ይኖርባቸዋል።

## አጠቃላይ አቀራረብ

የማህበረሰብ ውይይት በማህበረሰቡ ላይ የተመሰረተ አሳታፊ አቀራረብ እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ የማህበረሰቡ አባላትን በአንድ ላይ በማምጣት ለእነሱ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያወያያል። ይህንን በማድረግም የማህበረሰቡ አባላት አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ይለያሉ፣ በጉዳዮቹ ላይም ያላቸውን ግንዛቤ፣ ድርጊቶቻቸውንና እሴቶቻቸውን መርምረው ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች የሚያጋልጧቸውን ገዳቢ የስርዓተ ፆታ ግንኙነቶችንና ድርጊቶችን ለመለወጥ ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች የጋራ መግባባት ላይ ይደርሳሉ። የአፕሬሴቲቭ ኢንኩሪ (appreciative inquiry) አቀራረብን በማኅበረሰብ ውይይቶች በመጠቀም አመቻቾችና የማኅበረሰቡ አባላት ምን ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ያጠናሉ።  ይህ አቀራረብ ሰዎች በጋራ ራዕዮቻቸው ላይ በማተኮርና ያሉትን አጋጣሚዎች በመጠቀም በቤተሰብና በማሕበረሰብ ደረጃ ዘላቂ የሆኑ ለውጦች እንዲያመጡ ያግዛል።

ከተለያዩ ምንጮች የሚወሰዱና ተሳታፊዎችን ንቁ ተሳታፊ ሊያደርጉ የሚችሉ የመማሪያ ዘዴዎችና መሣሪያዎችን በመጠቀም ስርዓተ ፆታንና ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ የሚደረጉ የማሕበረሰብ ውይይቶች እንዲኖሩ ማበረታታትና ማሳለጥ ይቻላል። አመቻቾች የተለያዩ በትብብር የመማሪያ ቴክኒኮችንና እንደየተጨባጭ ሁኔታው የፈጠራ ችሎታቸውን በመጠቀም በዕይታ ሊያስተምሩ የሚችሉ ቴክኒኮችን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።

በእርግጥም በጉዳዩ ዳራና በሕብረተሰቡ ቡድኖች ስብጥር ላይ በመመርኮዝ የተለያዩ የማህበረሰብ ውይይቶችን ማበረታታትና የተለያዩ ማሳለጫ መንገዶችን መጠቀም ይቻላል። ይህ መመሪያ በማህበረሰብ ውይይት ውስጥ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸውን የተወሰኑ ዘዴዎችና ሒደቶችን እንደ ምሳሌ ለማሳየት የተዘጋጀ ብቻ ነው። አንድ የተወሰነ ዘዴ ብቻ በራሱ በቂ አይደለም። በማህበረሰብ ውይይቱ ወቅት የተለያዩ ዘዴዎችን  በመጠቀም አባላት በሚገባ እንዲገነዘቡ ብሎም የተማሩትን በተግባር እንዲተረጉሙ ማድረግ ያስፈልጋል።

## ዘዴዎችና መሣሪያዎች

በማህበረሰብ ውይይቱ ጊዜ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው ዘዴዎች የሚከተሉትን ያካትታል።

ታሪክ ነገራ (storytelling)። ታሪክ ነገራ የሕብረተሰብ ውይይት አመቻቾች የውይይቱን ርዕሶች ለተሳታፊዎች ተሞክሮዎችና እሴቶች የቀረቡ እንዲሁም የሚጥሙ አድርገው እንዲያቀርቡ ይረዳቸዋል። በውይይቱ አርዕስት ላይ ተሳታፊዎቹ ያላቸውን ተሞክሮዎችና ዕሴቶች በታሪክ መልክ በውይይቱ መጀመሪያ ላይ ቢያቀርቡ ተሳታፊዎቹ የስርዓተ ፆታ ሚናዎችን የሀብትንና ጥቅሞችን ቁጥጥርና ተደራሽነትን፣ ውሳኔ ሰጭነትንና ከእንስሳት ወደ ሰውና ስለሚተላለፉ በሽታዎች የሚደረጉ ውይይቶች አዎንታዊና ማሰላሰልን የሚያበረታቱ ሊሆኑ ይችላሉ።

ታሪኮቹ በዋናው ጉዳይ ላይ የተፈጠሩ ወይም ከሌሎች ምንጮች የተወሰዱ ሊሆኑ ይችላሉ። በታሪክ መልክ ሲቀርቡ ውይይቶች እንዲኖሩ ለማበረታታትና ሌሎች አዳዲስ ጭብጦችንና መልዕክቶች ለማሰስ ይረዳሉ። ሰዎች በተሞክሮዎቻቸው፣ ግንዛቤዎቻቸውና ተግዳሮቶቻቸው ላይ ተመስርተው ታሪኮችን ሲናገሩ

ምቾት ይሰማቸዋል። የሌሎችን ሰዎች ሀሳቦች፣ እሴቶች፣ ተሞክሮዎችና ዕይታዎች ለመቀበል ክፍት ይሆናሉ። ይህም ደግሞ ትርጉም ያለው ውይይት በማድረግ ምኞቶቻቸውን፣ ስጋቶቻቸውን እንዲሁም መፍትሔዎቻቸውን እንዲለዩ ያስችላቸዋል።

የምርመራ ጥያቄዎች (probing questions)። እውነታውን በሚገባ መርምሮ ለመረዳት የሚያስችሉንን ጥያቄዎች መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡ ፡ እንደነዚህ አይነት ጥያቄዎች የልምድ ልውውጥ እንዲኖር ከማስቻላቸውም በላይ በሚነሱ ችግሮች ላይ ጥልቅ የሆነ ትንታኔና ችግሩ ስለሚፈታበት መንገድ ማብራሪያ ለመስጠት ይረዳሉ። በማህበረሰብ ውይይቱ ወቅት ጥያቄዎችን መጠየቅ አባላቱ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ልምድ እንዲያንፀባርቁና ለለውጥ ያላቸውን ሐሳብ እንዲጋሩ ይረዳል።

ሚና መተውን (role play)። ሚና የሚተውነው በሁለት ወይንም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል ሲሆን አንድን ችግር ወይንም ሁኔታ ለመመርመር ይጠቅማል። ይህ ዘዴ በአንድ በተወሰነ ሁኔታ ወይንም ጉዳይ ላይ ሰዎች ምን ሊያስቡና ሊሰማቸው እንደሚችል እንዲሁም አመለካከታቸውና ግንዛቤያቸው ምን እንደሆነ ለመረዳት ያስችላል።

የፓናል ውይይት (panel discussions)። ገበሬዎችና የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች የማኅበረሰብ ውይይት ማመቻቸትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በፓናል ውይይት መልክ ሊወያዩ ይችላሉ። አመቻቾቹ ቁልፍ የመወያያ ነጥቦችን ለይተው በማውጣት የፓናሉ ተሳታፊዎች እንዲወያዩና ሀሳቦቸውን እንዲያንፀባርቁ ያደርጋሉ። ውይይቱን ተከትሎ ተሳታፊዎች ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፣ ግብረ መልስም ይሰጣሉ።

ምስሎችና ፖስተሮች። በፖስተሮች ፣ በፎቶዎች፣ በስዕሎችና በመሳሰሉት የሚደገፉ የተግባቦት ዘዴዎች የማሕበረሰብ ውይይቶችን ለመጀመርና ለማነቃቃት ይረዳሉ። እነዚህ ዘዴዎች ሰዎች ታሪኮችንና የራሳቸውን ልምዶች እንዲያጋሩ ይረዳሉ። ምስሎች ትኩረትንና ትውስታን ከመጨመራቸውም በላይ ሰዎች እርስ በርስ እንዲነጋገሩና ታሪኮችን ሆነ ልምዶቻቸውን በግልጽ እንዲለዋወጡ ያደርጋሉ። ካልተማሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ለሚደረግ መስተጋብር ምስሎች/ስእሎች ጠቃሚነታቸው የጎላ ነው። ምስሎችን መሠረት በማድረግ ሐሳቦችን በማንሳትና ታሪኮችን በመናገር የሕብረተሰቡ አባላት በጉዳዩ ላይ ያላቸውን እሴቶችና ግንዛቤዎች በጥልቀት እንዲመረምሩ ማድረግ ይቻላል። ስዕላዊ መግለጫዎችን ውይይቶችን ለመጀመር መጠቀም ይቻላል። ሆኖም እራሱን እንደቻለ እንደ አንድ ስልጠና መሣሪያ አብዝቶ መጠቀም አስፈላጊ አይደለም። ሰዎች አንዴ መናገር ከጀመሩ በኋላ ትኩረት ማድረግ ያለብን የምርመራ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኮቻቸውንና ልምዶቻቸውን አውጥተው እንዲናገሩ በማድረግ ላይ መሆን ይኖርበታል።

የማህበረሰብ ቲያትሮች (Community theaters)። የአንድን አካባቢ ጉዳዮች የሚመለከቱና ከማህበረሰቡ ጋር ወይንም በራሱ በማህበረሰቡ ለማህበረሰቡ ጥቅም የተሰሩ ቲያትሮች አሳታፊ ከመሆናቸው በተጨማሪ የማኅበረሰቡን ቀልብ በቀላሉ የሚስቡ ናቸው። ቲያትሮች ሙሉ በሙሉ በሕብረተሰቡ ወይንም በባለሙያ አርቲስቶች ድጋፍ ሊሰሩ ይችላሉ። የማህበረሰብ ቲያትሮች የማሕበረሰቡን አባላት ማህበራዊ ካፒታል (social capital) ከማበልጸግ በተጨማሪ ስርዓተ ፆታንና የእንስሳት ጤናን የተመለከቱ ችግሮችን ለመፍታት የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ። ቲያትሮችን የማህበረሰቡ አባላት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውይይቶች እንዲያደርጉ ለማነቃቃትና የማሕበረሰቡ አባላት ያላቸውን ግንዛቤና እሴቶቻቸውን እንዲመረምሩ/እንዲያጤኑ ለማድረግ መጠቀም ይቻላል።

አሳታፊ ቪዲዮች (participatory videos)። የፈጠራ ሂደቶችንና የማህበረሰብ ተሳትፎን ለማሳየት ሰዎችን አንድ ላይ በማምጣት አንዳንድ ጉዳዮችን እንዲያነሱ፣ ልምዶቻቸውንና ተግዳሮቶቻቸውን በታሪክ መልክ እንዲናገሩ ለማድረግ በማህበረሰብ ቡድኖች የተሰሩ ቪዲዮች በጣም ተመራጭ ናቸው፡ ፡ የማህበረሰብ ቪዲዮች የማህበረሰቡ አባላትና ከውጭ የሚመጡ ባለሙያዎች ያላቸውን ማህበራዊ ርቀት (social distance) ሊቀንሱ ይችላሉ። የማህበረሰቡ አባላት በቪዲዮ ውስጥ ከነሱ ውጭ ያሉ ሰዎች (ገበሬዎች ወይንም ሌሎች ሰዎች) እነሱ ባሉበት ሁኔታ ላይ ሆኖ ሲያዩ እራሳቸውን ቪዲዮ ውስጥ ከሚታዩ ሰዎች ጋር ስለሚያዛምዱ ተነሳሽነታቸው ጨምሮ ልምዶቹና ድርጊቶች በተመልካቾቹ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

## ወደ ማህበረሰቡ መግባት

ወደ ማህበረሰቡ መግባት አመቻቾች ማህበረሰቡንና የአመራር መዋቅሩን አውቀው ማህበረሰቡን ለማነቃነቅ ማከናወን ያለባቸው አንድ ሥራ ነው። ወደ ማኅበረሰቡ ለመግባት የሚከተሉትን ድርጊቶች ማከናወን አስፈላጊ ነው።

- የማህበረሰብ መሪዎችንና የሀገር ሽማግሌዎችን እንዲሁም ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎችን መለየት
- ራስን ከማህበረሰቡ መሪዎች፣ ተሰሚነት ካላቸው ሰዎችና ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ጋር ማስተዋወቅ
- የማህበረሰብ ውይይቱን ዓላማ ለማህበረሰቡ መሪዎችና ሌሎች ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎች መግለጽ
- የማህበረሰብ ውይይቶችን ለማካሄድና ሕብረተሰቡን የማነቃነቅ ሥራን የሚያዳበሩ መሪዎች የማህበረሰብ ውይይቱን ዓላማ እንዲደግፉ ማድረግ
- የማህበረሰብ ውይይቶችን በሥራ ላይ ለማዋልና የውይይቱን ክፍለ ጊዜዎች ለመከታተል የሚረዱ ከማኅበረሰቡ የተውጣጡ ተወካዮች (contact persons) እንዲኖሩ የማህበረሰቡን መሪዎች እገዛ መጠየቅ

- የጤና ባለሙያዎችን፣ የልማት ሠራተኞችን፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን፣ የሴቶች ቡድኖችን እንዲሁም የገበሬ የልማት ቡድኖችን በመለየት በተወካይነት ድጋፍ እንዲሰጡ ማድረግ
- በማህበረሰብ ውይይት መክፈቻና መዝጊያ ወቅት የማህበረሰቡ ሽማግሌዎችና መሪዎች እንዲገኙ በመጋበዝ የማህበረሰቡ አባላት ጉዳዮቹና እርምጃዎቹ ጠቃሚ መሆናቸውን እንዲረዱ ማድረግ ናቸው።

የማህበረሰብ ውይይት ተሳታፊዎችን መምረጥና መጋበዝ

- የበለጸገ ውይይት ይኖር ዘንድ የፆታና የዕድሜ ስብጥር እንዲኖር እንዲሁም የተለያዩ አስተያየቶችና እይታዎች እንዲንፀባረቁ ማድረግ
- ለማህበረሰብ ውይይቱ ብዙ ጊዜ እንደሚደረገው ሞዴል ገበሬዎችንና የመሳሰሉ ሰዎችን ብቻ አለመጋበዝ
- የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ ሰዎች በማህበረሰብ ውይይት እንዲገኙ መጋበዝ
- ብዙ የሕይወት ልምድና ለማህበረሰባቸው ራእይ ያላቸውንና በንቃት ተሳትፈው አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የማህበረሰቡ አባላትን ማካተት
- ከማህበረሰቡ አባላት ጋር በግል በመገናኘት ለውይይት መጋበዝና ተሳትፏቸው በጣም አስፈላጊ መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ
- ፆታዊ ስብጥሩ የተስተካከለ መሆኑንና የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተካተቱበት መሆኑን ለማረጋገጥ የተሳታፊዎችን ዝርዝር በማየት መገምገም

## አመቻቾችንና ማስታወሻ ያዦችን መምረጥና ማሰልጠን

- የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችን፣ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን፣ የልማት ባለሙያዎችን የመሳሰሉ ለማህበረሰቡ የሚሰሩ ሰራተኞችን እንዲሁም መምህራንን ወይንም የሴቶችን ቡድኖች፣ የገበሬ ቡድኖችን፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት የእርባታ ቡድኖችንና ሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎችን በማንቀሳቀስ በትናንሽ ቡድኖች በማመቻቸትና ማስታወሻ በመያዝ ሊረዱ የሚችሉ ሰዎችን መለየት
- የልማት ተጠሪዎችን፣ የጤና ሰራተኞችን፣ የእንስሳት ሕክምና ባለሙያዎችንም በመለየት በማህበረሰብ ውይይት አመቻችነትና በማስታወሻ ያዥነት ማሰልጠን ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑና እያንዳንዱን የማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜና አጠቃላይ የውይይቱን ሂደት እንዲሰንዱ ማድረግ

## የሒደትና የክትትል ዘዴዎች

1. የማሰላሰል ጽሁፍ። በተሞክሮዎቻችን ላይ በመመርኮዝ በግል በማሰላሰልና  በማስተዋል ጥልቅ የሆነ ትምህርት ልናገኝ እንችላለን። በእያንዳንዱ የማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜ የተነሱትን ዋና ዋና ሀሳቦች፣ ከውይይቱ የወጡ ጭብጦችንና የተጠቀሙ እርምጃዎችን እንዲሁም የውይይቱን ሒደት መከለስና ማሰላሰል ያስፈልጋል። በዚህ ሒደት የምንይዘው ማስታወሻ አጭርና ቀላል መሆን ይኖርበታል።
2. የተሳታፊ የዳሰሳ ጥናት። በእያንዳንዱ የማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ በቃለ መጠይቆች ወይንም በግብረ መልስ ጥናቶች አማካኝነት የተሳታፊዎችን ግብረ መልስ ማግኘት።
3. የምስሎች ሰነድ። የቡድኖችን ውይይቶችና ውጤቶችን እንዲሁም የቡድን እንቅስቃሴዎችን በካሜራ መቅረፅና ሪፖርቶችን የበለጠ ገላጭ እንዲሆኑ ማድረግ
4. ቃለ መጠይቆች። የማህበረሰብ ውይይቶች በሚከሄዱበት ወቅትና የክትትልና ድጋፍ ሥራ በሚካሄድበት ወቅት ሰዎች በማህበረሰብ ውይይቶች በመሳተፋቸው ምክንያት ያሳዩዋቸውን ለውጦች በለውጥ ታሪኮች መልክ መመዝገብ
5. የአመቻቾችና የማስታወሻ ያዦች የማሰላሰልና የግምገማ ስብሰባ። በእያንዳንዱ ስብሰባ መጨረሻ አጠር ያሉ ስብሰባዎች በማድረግ የማህበረሰብ ውይይቱን ሂደትና ተሳታፊዎቹ የሰጡትን ምላሽ፣ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶችና በሚቀጥለው የውይይት ጊዜ መደረግ ስለሚኖርባቸው ማሻሻያዎች መነጋገር ያስፈልጋል። በተጨማሪም ማስታወሻዎቹን ምልከታዎቹንና ቁልፍ ግንዛቤዎችን መገምገም አስፈላጊ ነው።
6. ቪዲዮዎች። የሚቻል ከሆነ የማህበረሰብ ውይይቶችን ሂደትና በአካባቢው ከከብቶች አያያዝ ወይንም ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦችን አያያዝ በቪዲዮ መቅረጽ።
7. ውህድ ሪፖርት (synthesis report)። ከማህበረሰብ ውይይቱ ሪፖርቶች የተገኙትን ዋና ዋና ጭብጦችና የእርምጃ ሀሳቦችን አንድ ላይ በማዋሀድ በአጠቃላይ ሒደቱና ልምዶቹ ላይ ማሰላሰልና ትምህርት መውሰድ

## ክትትል

ከእያንዳንዱ የማሕበረሰብ ውይይት በኋላ የመማርና የስርጭት ቡድኖችን በማቋቋምና በመሳሰሉት ዘዴዎች ክትትል ለማድረግ ማቀድ።

- የክትትል ጉብኝቶችን በማድረግ የመማርና የስርጭት ቡድኖቹ መረጃ በማሰራጨትና ሰዎች እንዲማሩ ለማድረግ የሚፈጽሟቸውን ድርጊቶች በመሰነድ ድጋፍ መስጠት (አባሪ 6ትን ይመልከቱ)

## ቁሳቁሶች

- ተጣጣፊ ገበታዎች (Flipcharts)
- የተጣጣፊ ገበታዎች መቆሚያ (በአካባቢው ሊሰሩ ይችላሉ)
- ማርከሮች
- ፖስተሮች
- የስም መመዝገቢያ ወረቀቶች (sign-in-sheets)
- ምስሎችና ስዕሎች
- የቪዲዮና የድምጽ መቅረጫ መሳሪያዎች
- የፎቶ ካሜራ
- ቪዲዮ ክሊፖች
- የተግፋ ታሪኮች
- የሚና ትወና እስክሪፕቶዎች
- በራሪ ወረቀቶች
- የማስታወሻ ደብተሮችና እስክሪፕቶች

## የማኅበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜያት ቅርፀት (ፎርማት)

እንደየአካባቢው ሁኔታ የማኅበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜዎቹ የተለያዩ ቅርጸት ሊኖራቸው ይችላል። በዚህ የውይይት መመሪያ የሚመከረው የሚከተለው ቅርፀት ሲሆን አመቻቾች ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ (ለምሳሌ በተሳታፊዎች ቁጥርና ዓይነት እንዲሁም ከስብሰባው ቦታ) ጋር በማዛመድ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

- በእያንዳንዱ የማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜ አራት አመቻቾች ይኖራሉ። አንደኛው አመቻች እንደ መሪ ሲያገለግል ሌሎቹ በትናንሽ ቡድኖች የሚደረጉ ውይይቶችን በማሳለጥና ማስታወሻ በመያዝ ያገለግላሉ።
- እያንዳንዱ የውይይት ክፍለ ጊዜ ከ2-4 ሰዓታት ይኖሩታል
- ውይይቶቹ ሰፊ ቦታዎች ባሏቸው ቦታዎች ለምሳሌ በትምህርት ቤቶችና በገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከሎች ቢካሄዱ ይመረጣል። ብዙ ሰዎች ያሉባቸውን ውይይቶች እንደ አስፈላጊነቱ በትናንሽ ቡድኖች ከፍሎ ማካሄድ ይቻላል።
- የአንድ የማህበረሰብ ውይይት ተሳታፊዎች ቁጥር ቢበዛ ከ50 በላይ መሆን የለበትም
- ትናንሽ ቡድኖች ከ10-15 የሚሆኑ ተሳታፊዎች ይኖሯቸዋል።
- ትናንሽ ቡድኖችም አመቻቾችና ማስታወሻ ያዦች ይኖሯቸዋል።

# ተጨማሪ ንባብ

Kaner, S. with Lind., Toldi, C., Fisk, S. and Berger, D. 1996. Facilitator’s guide to participatory decision making. Vancouver, B.C: New Society Publishers.

Lemma, M., Hoekstra, D., Tegegne, A. and Berhanu, G. 2015. Capacity development tookit. LIVES Toolkit 1. Nairobi, Kenya. Internaiotal Livestock Institute (ILRI).

# ክፍል 3፡ ማቅረብ

## ክፍለ ጊዜ 1፡ መጀመር

### መግለጫ

በዚህ ክፍለ ጊዜ የማሕበረሰብ ውይይቶች ዓላማና የመተግበሪያ ዘዴዎችን ሂደት ትማራላችሁ። ክፍለ ጊዜው የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት።

- የማህበረሰብ ውይይቶችን የምናካሄድባቸውን ምክንያቶች፣ ዓላማዎችና ሂደቱን መግለፅ
- በማህበረብ ውይይት አማካይነት ታይተው ሊፈቱ የሚችሉ ዋና ዋና ጉዳዮችን ማሳወቅ
- በማህበረሰብ ውይይት ወቅት የማህበረሰቡ አባላት ያላቸውን ሚና ማብራራት
- በማህበረሰብ ውይይት ወቅት ሊከበሩ በሚገባቸው መሰረታዊ ህጎች (ground rules) ላይ ስምምነት መድረስ
- የማህበረሰብ ውይይት ስለሚካሄድበት ቦታና ጊዜ ስምምነት ላይ መድረስ
- ከማህበረሰብ ውይይቱ የሚጠበቁ ውጤቶችን ለይቶ ማውጣት

የትውውቅ ክፍለ ጊዜው የማህበረሰቡን አባላትና አመቻቾችን አንድ ላይ በማምጣት እንዲግባቡና ለወደፊት ለሚኖሩ ውይይቶች ጭምር ለመማማር አመቺ የሆነ ሁኔታን ለመፍጠር ያለመ ነው። ይህ ክፍለ ጊዜ እንደሚኖረው ሰዓት ሁኔታ ብቻውን ሊከናወን ወይንም ከሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ጋር አብሮ ሊቀናበር ይችላል። ለአንድ ዓመት ለሚደረጉ የውይይት ክፍለ ጊዜዎች የትውውቅ ክፍለ ጊዜው ለብቻ ቢደረግ መግባባትን ለመፍጠርና ከመጀመሪያው ጀምሮ የሚጠበቁ ውጤቶችን ለማብራራት እንዲሁም የተጠበቁ ውጤቶች ስለመገኘታቸው የሚገልፁ ጠቋሚ ምልክቶች ምን መሆን እንዳለባቸው ተወያይቶ መስማማት ይቻላል።

### ዓላማዎች

የማህበረሰብ ውይይቱ ሲጠናቀቅ  አመቻቾች የሚከተሉትን ማከናወን ይችላሉ።

- ከማህበረሰቡ የተለያዩ ክፍሎች የተውጣጡ ሰዎችን በማሰባሰብ የማህበረሰብ ውይይቶችን ሂደትና ዓላማ ማስተዋወቅ
- በሁሉም የማህበረሰብ ውይይት ሂደቶች በማህበረሰቡ አባላት መካከል በመተማመን ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲኖር መሠረት መጣል
- በማህበረሰብ ውይይቶች ውስጥ ለመሳተፍ ፍላጎቱ ያላቸውን የተነቃቁና በራሳቸው የሚተማመኑ የማህበረሰብ አባላት ፈልጎ ማግኘት
- ከማህበረሰብ ውይይቱ የሚጠበቁ ነገሮችንና ስጋቶችን ግልጽ ማድረግ
- የማህበረሰብ ውይይቶችንና መሰረታዊ ሕጎችን መመስረትና የተሳታፊዎችን ሚና ግልጽ ማድረግ

### ይዘት

- የተሳታፊዎችና የአመቻቾች ትውውቅ
- የማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜዎች ዓላማዎችና ሂደት
- የማህበረተሰብ ውይይት ጉዳዮች
- የማህበረሰቡ አባላት ሚና

- የማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜዎች መሰረታዊ ሕጎች
- ከማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

የመማሪያ ዘዴዎችና ቁሳቁሶች

- መስተጋብራዊ ዘዴዎች
- ጥያቄና መልስ
- የልምድ ልውውጥ
- ፊሊፕ ቻርቶች

ሊወስድ የሚችለው፥ ጊዜ 2 ሰዓታት

## የመማር እንቅስቃሴዎች

1. ጥሩ አቀባበል ማድረግና ጓደኝነት የሰፈነበት ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ነው። ተሳታፊዎች ወደ ስብሰባው ቦታ ሲመጡ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ሞቅ ያለ ሰላምታ በማቅረብ የጓደኝነት ስሜትን ለመፍጠርና መልካም ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግ ይረዳል። የሚቻል ከሆነም ተገቢነት ያላቸውን ፖስተሮች በመለጠፍ ወይንም በመስቀል ተሳታፊዎችን መሳብና ማነሳሳት ያስፈልጋል።

2. ስብሰባው በሚከፈትበትና በሚተዋወቅበት ጊዜ የአካባቢውን ወጎችና ልምዶች ማክበር ያስፈልጋል። የማህበረሰቡ ሽማግሌዎች ወይም መሪዎች ስብባውን እንዲከፍቱና የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር እንዲያደርጉ ጋብዟቸው። በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ወቅትና በውይይቱ መጀመሪያ የሚፈጠሩ ሁኔታዎች ለወደፊት በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል።

ሰዎች በተለያዩ ቡድኖች (ለምሳሌ የሀይማኖት መሪዎች፣ ሽማግሌዎች፣ የማህበረሰብ መሪዎች፣ ባልና ሚስት ወዘተ) ለትንሽ ጊዜ ቆም እንዲሉ በማድረግ የተሳታፊዎችን ስብጥር መረዳት አስፈላጊ ነው። ይህ ማድረግ በስብሰባው የሚገኙ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች በስብሰባው ወቅት ሌሎችን ተሳታፊዎች እንደይጫኗቸው ለመጠንቀቅም ይጠቅማል። ብዙ ጊዜ ተሳታፊዎች የሃይማኖት አባቶችንና የማህበረሰቡ መሪዎችን አስተያየቶች ሳይመረምሩ በቀላሉ ይቀበላሉ።

በውይይቱ ወቅት ብዙ ተሳታፊዎች ሲኖሩና ቦታው ጠባብና ከወዲህ ወዲያ የማያንቀሳቅስ ሲሆን የቡድን ትውውቅ ዘዴ ተመራጭ ይሆናል። ይህ ዘዴ ጊዜን ይቆጥባል። በቂ ቦታ ሲኖር ግን ተሳታፊዎች ከተቀመጡበት ተነስተው በተሰጣቸው ሰዓት ውስጥ በተቻላቸው መጠን ብዙ ሰዎችን አግኝተው እንዲያነጋግሩ ይጠይቋቸው።

ተሳታፊዎቹ በማበረሰቡ ውስጥ ለሚኖሩ ሴቶችና ወንዶች እንዲሁም ለከብቶቻቸው ጤንነት ያላቸውን መልካም ምኞቶች እንዲለዋወጡ ይጠይቋቸው።

ማስታወሻ ወሳጆችን ጨምሮ ሌሎችን የአመቻቾች ቡድን አባላትን አስተዋውቋቸው። በእጅ የተሳሉ የገዛ ራስ ስዕሎችን (self portraits) በመሳል የቡድን አባላቱ በማህበረሰብ ውይይቶች ያላቸውን ሚና ግለጹላቸው። ይህን በማድረግ ዘና ያለ አካባቢ መፍጠርና በተሳታፊዎቹ መካከል የበለጠ መግባባት እንዲኖር ማድረግ ይቻላል።

ሁሉም ተሳታፊዎች ባሉበት ስብሰባ ስለ ትውውቁ ምን እንደተሰማቸው ጠይቋቸው። ለወደፊቱ አብረው ስለሚሰሩና ተከታታይ ውይይቶችን ስለሚያደርጉ የበለጠ ሊተዋወቁ እንደሚችሉ ይንገሯቸው።

3. የማህበረሰብ ውይይቱን ዓላማዎችና ከውይይቱ የሚጠበቁ ውጤቶችን አስተዋውቁ። ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት ዓላማዎቹንና የሚጠበቁ ውጤቶች በአካባቢው ቋንቋ በፊሊፕ ቻርት ወረቀቶች ላይ በሚገባ ሊታይ በሚችል ሁኔታ ፅፋችሁ አዘጋጁ። ፊሊፕ ቻርቶችን በመጠቀም የማሕበረሰብ ውይይትን አስፈላጊነትንና ጠቃሚነት እንዲሁም ሌሎች በማሕበረሰብ ውይይቱ ሊነሱ ስለሚችሉ ቁልፍ ጉዳዮች ያስረዷቸው።

ሁሉም ተሳታፊዎች የተሰበሰቡበት ምክንያት ምን እንደሆነና የማህበረሰብ ውይይት እንዴት ሊሰራ እንደሚችል በሚገባ መረዳታቸውን ያረጋግጡ።

አመቻቾች በምን ያህል ፍጥነት ቢናገሩ ተሳታፊዎች አዳምጠው ሊረዷቸው እንደሚችሉ መገመት ይኖርባቸዋል። ይህንንም የተሳታፊዎችን የሰውነት ቋንቋ (body language) በማስተዋልና ተሳታፊዎቹን በመጠየቅ ማወቅ ይችላሉ።

4. የማሕበረሰብ ውይይት ሒደትን ያስረዷቸው። ስብሰባው በሚደረግበት ቦታና ሰዓት ላይ ስምምነት መኖሩን ያረጋግጡ። በትናንሽ ቡድኖች ሆነው በመወያየት የማህበረሰብ ውይይቱን ቦታና ሰዓት እንዲወስኑ ይርዷቸው። አስፈላጊ ከሆነ ሴቶችና ወንዶችን በተለያዩ ቡድኖች እንዲወያዩ ማድረግ ይቻላል። ይህን ማድረግ ሴቶች ያለምንም ፍራቻ በነፃነት እንዲወያዩ ከማስቻሉ በላይ ከውይይቱ በሚገኘው መረጃ ላይ ተመስርቶ የስርዓተ ፆታ ትንተና ለማድረግ ይጠቅማል።

በፊሊፕ ቻርቱ ላይ ተግባራቱን በግልጽ በመፃፍ ቡድኖቹ መተግበር ያለባቸውን መረዳታቸውን ያረጋግጡ።

- ለተሳታፊዎቹ (ለወንዶቹና ለሴቶቹ) አመቺ የሚሆነው ምን ዓይነት ቦታ ነው? የተጠቆመው ቦታ አመቺ ሆኖ የተገኘው ለምንድነው?
- በምን ያህል ድግግሞሽ ስብሰባው ቢካሄድ ይመርጣሉ? (በወር አንድ ጊዜ ወይንስ በየወሩ?) ለምን?
- ስብሰባው በምን ዓይነት ጊዜ ቢካሄድ ይመርጣሉ (ወር በገባ በመጀመሪያው ሳምንት ወይንስ ወር በገባ በሁለተኛው ሳምንት?)

ሁሉም ተሳታፊዎች በሚገኙበት ስብሰባ ተሳታፊዎቹ ምርጫቸውን አቅርበው እንዲነጋገሩ ያድርጓቸዋል። ተሳታፊዎቹ ሀሳቦቻቸውን ለውይይት አቅርበው የሕብረተሰብ ውይይቱን ቦታና ጊዜ ላይ እንዲስማሙ አበረታቷቸው። ተሳታፊዎች የሚያቀርቧቸውን አማራጭ ሀሳቦች ሁሉ በፊሊፕ ቻርት ላይ በሚገባ ይመዝግቧቸው። በመጨረሻም ስምምነት የተደረሰባቸውን አማራጮች በፊሊፕ ቻርት ላይ በግልጽ በመፃፍ ሁሉም ተሳታፊዎች ውሳኔውን ማወቃቸውን ያረጋግጡ፡

ከአደራጆች ወይንም ከአመቻቾች ጋር በመገናኘትና በመነጋገር ተሳታፊዎች በሚቀጥሉት ውይይቶች ላይ እንዲገኙ የሚያስተባብሩ የማህበረሰቡ ተጠሪዎችን እንዲመርጡ ተሳታፊዎቹን ይጠይቁ። እንደ አመቻችነትዎ እርስዎም በበኩልዎ ተሳታፊዎች በሁሉም ውይይቶች ላይ መገኘታቸውን እንደሚከታተሉ ተሳታፊዎች ይንገሯቸው።

5. መሠረታዊ ሕጎች (ground rules) - መሠረታዊ ሕጎችን ይወስኑ። በውይይቱ ወቅት ሊከበሩ የሚገባቸውን ሕጎች አስቀድመው ያውጡ፡ ፡ የማሕበረሰብ ውይይቱ ስኬት የሚወሰነው ሁሉም ተሳታፊዎች የተስማሙባቸውን የውይይቶቹን መሠረታዊ ሕጎች ማክበር አለማክበራቸው ላይ መሆኑን ይንገሯቸው። ያዘጋጇቸውን መሠረታዊ ሕጎች ለተሳታፊዎች በማካፈል ተነጋግረው እንዲስማሙባቸውና ለተግባራዊነቱ ቁርጠኝነታቸውን እንዲገልጹ ይጠይቋቸው።

ብዙ ጊዜ እንደሚታየው በውይይቱ ወቅት ተሳታፊዎች አንዳንድ ህጎችን ላያከብሩና አንዳንዶቹን ያልተነጋገሩባቸውን ሕጎች ደግሞ ሊጨምሩ ይችላሉ። ስለሆነም የጋራ ስምምነት የተደረሰባቸውን ሕጎች በግልጽ መጻፍና ሁሉም ሊያያቸው በሚችልበት ቦታ በማስቀመጥ ተሳታፊዎቹ ውይይቶቹ በሚካሄዱባቸው ጊዜ ሁሉ እንዲያከብሯቸው ማስታወስ ይኖርብናል።

6. በማሕበረሰብ ውይይቱ ወቅት ያሉትን ሚናዎችን አብራሩዋቸው። በማህበረሰብ ውይይቶች ውስጥ ሶስት ሚናዎች ይኖራሉ። እነሱም የአመቻቾች፣ የተሳታፊዎችና የማስታወሻ ያዦችን ሚናዎች ናቸው።

የአመቻቾችን ቡድን ሚና በሚከተለው መልክ ያስተዋውቁ።

“የእኔ ሚና ከስርዓተ ጾታ አንፃር ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች የተለያዩ ጥያቄዎች በመጠየቅ ውይይቶች እንዲኖሩ ማድረግና ውይይቶቹን መምራት ነው። ሆኖም እኔ በውይይቶቹ በመሳተፍ አስተያየቴን አልሰጥም። ማስታወሻ ያዦች በውይይቱ ወቅት የሚነሱትን ሐሳቦችን  ይመዘግባሉ። የእኔ የሥራ ድርሻ የሚሆነው አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች ሁሉ በማስታወሻው ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ ነው። እንደ ተሳታፊ የእናንተ ድርሻ የሚሆነው ከስርዓተ ጾታ አንፃር ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች ያላችሁን ዕይታ፣ ዕውቀት፣ ልምዶችና እሴቶች ማካፈል ነው። እናንተ በማህበረሰብ ወይንም ሌሎች ቡድኖች ውስጥ ሌሎች ሚናዎችን መጫወት ትችላላችሁ። አንዳንዶቻችሁ በግብረ መልስ ቡድኖች ውስጥ ማገልገል ትችላላችሁ። ሌሎቻችሁ ደግሞ የተለያዩ ታሪኮችን በመናገር ተሳታፊዎቹን ማነቃቃት ትችላላችሁ። አንዳንድ ተሳታፊዎች ደግሞ በአመቻቾች ስም ተሳታፊዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለትና በሌሎች መንገዶች መሳተፍ ይችላሉ።

ሴቶችና ወንዶች የተለያየ ሚና እንዲጫወቱ ይንገሯቸው።

7. በመጀመሪያ ያሰላስሉ። ግብረ መልስ ይስጡና ውይይቱን ይዝጉት። የውይይቱን ሒደት በማሰላሰል፡ ዋና ዋና ሀሳቦችን ያስቀምጡ።

የሚከተሉትን የማሰላሰያ ጥያቄዎች በፊሊፕ ቻርት ላይ ይጻፉ

- ዛሬ በግልጽ የተረዳሁት ____________________________________________
- ያለኝ ስጋት/ስጋቶች ____________________________________________
- ያለኝ ጥያቄ /ጥያቄዎች ____________________________________________

ሁሉም ተሳታፊዎች በተገኙት ውጤቶች በውይይት ሂደት የተማሩትን እንዲያሰላስሉና ስጋቶቻቸውን እንዲያወጡ ጠይቋቸው። ተሳታፊዎች የሚመልሷቸውን መልሶች በፊሊፕ ቻርት ላይ ይጻፉ። የጋራ የሆኑ ጭብጦችን ለይተው ለስጋቶቹ የመፍትሔ ሀሳብ ለመስጠት ይሞክሩ።

ተሳታፊዎችን በውይይቱ በመሳተፍ ላዎሉት ጊዜ ምስጋና ካቀረቡ በኋላ በሚቀጥሉት ተከታታይ የማህበረሰብ ውይይቶች እንደሚሳተፉ ያሎትን ምኞት ይግለጹ።

# ለአመቻቾች ተጨማሪ መረጃዎች

የማህበረሰብ ውይይት ዓላማዎች

- የአንድ ማህበረሰብ አባላት አንድ ላይ ተሰብስበው በመነጋገር ዕይታዎቻቸውንና አመለካከታቸውን ለመለወጥ የሚያስችላቸውን ቅንጅትና ነጻ መድረክ በመፍጠር በከብት እርባታ የስርዓተ ፆታ ግንኙነትንና ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች ያላቸው መረዳትና ዕይታ ማጎልበት
- የማህበረሰቡ አባላት በከብት ማርባት ሥራ ውስጥ የስርዓተ ጾታ ግንኙነትና ከእንስሳት ወደ ሰው  የሚተላለፉ በሽታዎችን መከላከልን በተመለከተ ላሏቸው አስተሳሰቦችና ምኞቶች ምክንያት የሆኑ ዕሴቶቻቸውን፣ ስጋቶቻቸውንና ግምቶቻቸውን በጥልቀት አስበው እንዲነጋገሩ ማድረግ
- በከብት እርባታ ሥራ ውስጥ የሚታዩትን የተገደቡ የስርዓተ ጾታ ግንኙነቶችንና  በሽታዎች ከእንስሳት ወደ ሰው የመተላለፍ አደጋን አስመልክቶ የህብረተሰቡ አባላት በግልም ሆነ በጋራ ማድረግ ያለባቸውን እንዲያስቡ ማበረታታት

ከማህበረሰብ ውይይት ስብሰባዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

- ማህበረሰቡ በከብት አያያዝ ላይ ሚዛናዊ ያልሆኑ የስርአተ ፆታ ግንኙነቶች ስለሚያስከትሉት ችግሮች የተሻለ ግንዛቤ ይኖረዋል።
- ማህበረሰቡ ሴቶች በከብት ዕርባታ ውስጥ ያላቸውን ሚና ተገንዝቦ ለዚህም ዕውቅና በመስጠት በቤተሰብ ውስጥ ሥራን ለመከፋፈል ፈቃደኝነት ያሳያል።
- በከብት ሀብት ላይ ሴቶች ስላላቸው የባለቤትነትና የመቆጣጠር ሁኔታ ሕብረተሰቡ ያለው አመለካከትና ድርጊት ይቀየራል።
- ማህበረሰቡ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ የተለመዱ በሽታዎች የሚከሰቱበትን ምክንያቶችና ጉዳቶቻቸውን በተመለከተ ያለው ግንዛቤ ይጨምራል።
- ማህበረሰቡ የተለመዱ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ስለመከላከልና ስለመቆጣጠር ያለው ግንዛቤ ይጨምራል።

በእንስሳት እርባታ ሥራ ውስጥ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ከመከላከል አንፃር ገዳቢ የሆነውን የስርአተ ጾታ ግንኙነት ለመወለጥ በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ ዕቅዶች ታቅደው እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

የማህበረሰብ ውይይቱ ቀን ሰዓትና ቦታ

- ተሳታፊዎች ተገናኝተው በመወያየት የማህበረሰብ ውይይቱ ክፍለ ጊዜ የሚካሄድበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ተስማምተው እንዲወስኑ ያድርጓቸው። የስብሰባዎቹ ቦታና የሚካሄዱበት ሰዓት በማህበረሰቡ ውይይቶቹ ስኬትና በሚያስገኙት ውጤት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል። የስብሰባው ቦታና ሰዓት ማን ሊሳተፍ እንደሚችልና የውይይቱን ጥራት ሊወስን ይችላል።
- የቀን መደራረብ እንዳይኖር የቀን መቁጠሪያውን ይመልከቱ።ለማህበረሰብ ውይይት ሌላ አመቺ ቀን ማግኘት የሚያዳግት ከሆነ ዕቁቦች፣ ዕድሮችና ማህበራት የሚውሉበትን ቀናት ለመጠቀም ይሞክሩ።
- ለሴቶችና ለወንዶች ተሳታፊዎች አመቺ የሆነ የውይይት ጊዜ ርዝመትና ድግግሞሽ ላይ ከስምምነት መድረስ ያስፈልጋል። ዓይነተኛ የሆነ የማሕበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜ በ15 ቀናት አንድ ጊዜ ወይንም በወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል። እያንዳንዱ የማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜ ከ3 እስከ 4 ሰዓት ሊወስድ ይችላል። ሆኖም ተሳታፊዎቹ በውሳኔው ላይ መስማማታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ውይይቱን በ15 ቀናት አንዴ ማካሄድ ተሳታፊዎች የውይይቱን ፍሰት ጠብቀው እንዲወያዩ ስለሚያስችላቸው የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል። በአንፃሩም በሁለት የውይይት ክፍለ ጊዜዎች መካከል ብዙ መራራቅ ካለ ተሳታፊዎች ባለፈው ስብሰባ ላይ የተወያዩበትን ሃሳብ ሊረሱ ከመቻላቸውም በላይ የውይይቱ ሞቅታ ሊቀዘቅዝ ይችላል።
- ተሳታፊዎቹ ለስብሰባ የተመረጠው ቦታና ጊዜ የሚመቻቸው መሆኑንና ለመገኘት የቀረጡ መሆኑን ያረጋግጡ።

የስብሰባ ቦታ ሲመረጥ ከግምት መግባት ያለባቸው ጉዳዮች

- ተሳታፊዎቹ ቦታውን ማወቃቸውና በተደጋጋሚ መጠቀማቸው
- የሚገኘው በማህበረሰቡ ውስጥ መሆኑ
- ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑ
- በጣም ከፍተኛ ድምጾችና ሌሎች የሚረብሹ ነገሮች አለመኖራቸው
- ሁሉም ተሳታፊዎች (ሴቶችና ወንዶች) በቀላሉ ሊደርሱባቸው መቻላቸው

የማህበረሰብ ውይይት መሠረታዊ ህጎች

- በሰዓቱ መገኘት
- በውይይቱ ወቅት ስልክ አለመደወል ወይንም የስልክ ጥሪ አለመቀበል
- ሌሎች ሲናገሩ ጣልቃ አለመግባት
- የሀሳብና የአመለካከት ልዩነቶችን በፀጋ መቀበል
- የሌሎች ሰዎችን ዕይታ ማክበር
- በውይይቱ ወቅት ብዙ ጊዜን በመናገር የሌሎችን ተራ አለመውሰድ/አለመሻማት
- እውነታውን መቀበል

- ሌሎች የሚናገሩትን በጥሞና ማዳመጥ
- የተሳሳቱ መልሶች አሉ ብሎ አለማመን
- ሐሳቦችን ለመቀበል አእምሮን ክፍት ማድረግ

# ክፍለ ጊዜ 2፡ የስርኣተ ፆታ ሚና በከብት እርባታ

## የክፍለ ጊዜው መግለጫ

የዚህ ክፍለ ጊዜ ዓላማ በከብት እርባታ ሴቶች ያላቸውን ሚና የበለጠ በማሳወቅ ወንዶችና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ሴቶች በመስኩ ላይ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ እንዲገነዘቡና አድናቆት እንዲለግሱ ማድረግ ነው።

ይህ ክፍለ ጊዜ በከብት እርባታ ሥራ ሚዛናዊ ስላልሆነ የሥራ ክፍፍልና ስለማይታዩ የሴቶች ሚናዎች የተሻለ መረዳት፣ አድናቆትና እውቅና ለመፍጠር ያልማል። በከብት ማርባት ሂደት በቤተሰብ አባላት መካከልም ፍትሃዊና ሚዛናዊ የሥራ ክፍፍል እንዲኖርና ለሥራቸው እኩል ዋጋ እንዲሰጠው ለማድረግም ያልማል።

## የክፍለ ጊዜው ዓላማዎች

በማህበረሰብ ውይይቱ ክፍለ ጊዜ መጨረሻ ተሳታፊዎቹ የሚከተሉትን ለማከናወን ብቁ ይሆናሉ።

- በከብት እርባታ ሥራ ወንዶች፣ ሴቶችና ሕጻናት የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች ለመለየት
- ሴቶች እንዲያከናውኑ ሀላፊነት የተሰጧቸው ሥራዎች በመለየት ሥራዎቹ የሚፈጁትን ጉልበትና ለማከናወን የሚወስዱትን ጊዜ ወንዶች ከሚሰሯቸው ሥራዎች ጋር በማነፃፀር ለሥራዎቻቸው ማህበረሰቡ የሚሰቸጣውን ዋጋ መግለጽ
- የስርኣተ ፆታ የሥራ ክፍፍል በከብት ምርታማነትና በቤተሰብ ጤና ላይ ስለሚያስከትለው ውጤት ያሉትን ግንዛቤዎች መመርመር
- በከብት እርባታ ሚዛናዊ የሆነ የሴቶችና የወንዶች የሥራ ክፍፍል እንዲኖር የሚያስችሉ ዕድሎችን መለየትና የእርምጃ ሐሳቦችን ማቅረብ

## የክፍለ ጊዜው ይዘት

- ወንዶችና ሴቶች በከብት እርባታ ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባራት
- የከብት እርባታ ሥራ የሚፈጀው ጉልበትና ሰዓት በሴቶችና ወንዶች ከሚያከናውኗቸው ሥራዎች አንፃር ሲመዘን
- በከብት እርባታ ለሴቶች ሚና የሚሰጠው ዋጋና ታዋቂነት

## የመማሪያ ዘዴዎችና ቁሳቁሶች

- በስርዓተ ጾታ የሥራ ክፍፍል ላይ ያተኮረ ፖስተር
- ታሪክ ነገራ
- የምርመራ ጥያቄዎች (probing questions)

# የመማር ተግባራት (learning activities)

1. ከዚህ በፊት የቀረበውን ክፍለ ጊዜ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተመርኩዘው ይወያዩ። ምን ተስማማን? ምን ተለወጠ? መረጃዎቹን በምን አይነት መልኩ ተለዎወጣችሁ? ተሳታፊዎቹን እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ ጊዜያቸውን ሰውተው ለስብሰባው ስለመጡ ያመስግኗቸው። ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ማጠቃለል የሚያስፈልገው ከአሁኑ ክፍለ ጊዜ ጋር ለማያያዝና ውይይቱ ጥሩ ፍሰት እንዲኖረውና ተሳታፊዎቹ የክፍለ ጊዜውን ዓላማ በሚገባ እንዲረዱ ነው።

የማጠቃለያውን አረፍተ ነገሮች በፊሊፕ ቻርት በግልጽ ጻፏቸው።

- ካለፈው የውይይት ስብሰባ የተማርኩት______________________________________
- ከሌሎች ሰዎች ጋር የተለዋወጥነው መረጃ/መረጃዎች____________________________
- ባለፈው ስብሰባ ተሳትፌ በመወያየቴ ያመጣኋቸው ለውጦች ___________________________

ጊዜውና ቦታው ከፈቀደ ተሳታፊዎች ክብ ሰርተው እንዲቀመጡ ይጠይቋቸው። ከላይ የተጠቀሰውን ተግባር እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው ያስረዷቸው። ተሳታፊዎች በክፍለ ጊዜው ያገኟቸውን ልምዶች በፊሊፕ ቻርቱ ላይ የተጀመሩትን ዓረፍተ ነገሮች እንዲጨርሱ ንገሯቸው። ልምዶቹ ተሳታፊዎች ስላደረጓቸው የመረጃ ልውውጦች፣ ስላከናወኗቸው ተግባራት፣ ስላስተዋሏቸው ነገሮች ወይንም ስላደረጓቸው ለውጦች ሊሆን ይችላል።

በመጀመሪያ ፍቃደኛ ከሆነ ተሳታፊ በመጀመር ከዚያ መደዳውን መቀጠል ይቻላል። ተሳታፊዎች ሳይጨናነቁ በአእምሮአቸው የመጣውን ሐሳብ ብቻ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። ያልተማሩና በውይይቱ ብዙ የማይሳተፉ ሰዎችን እንዲሳተፉ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ሐሳቦቻቸውን እንዲናገሩ አበረታቷቸው።

ይህ ተሞክሮ ለተሳታፊዎች የሚያስደስት እንጂ የሚስፈራ እንዳይሆን ያድርጉ። ተሳታፊዎች ስለሰጡት ምላሽ ያሎትን አድናቆት ከተናገሩ በኋላ በፊሊፕ ቻርት ላይ ይፃፉ። ምላሾችን በመከለስ ከውይይቱ አጀንዳ ጋር ያገናኟቸው።

በፊሊፕ ቻርቱ ላይ የተጻፉትን መሠረታዊ የውይይቱ ሕጎች በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ አስቀምጠው ተሳታፊዎች እንዲያነቧቸውና ሕጎቹን እንዲያከብሩ ያስታውሷቸው።

ውይይቱን በመከታተል ከተሳታፊዎቹ ግብረ መልስ በመቀበል ምልከታቸውንና ከተሳታፊዎች ያገኙትን ግብረ መልስ ለአመቻቾች የሚያቀርቡ ፍቃደኛ የሆኑ የግብረ መልስ ቡድኖችን ይመስርቱ።

2. የዕለቱን አጀንዳ በመጠቀም የማህበረሰብ ውይይት ርዕሱን ያስተዋውቁ። ርዕሱን በሚከተለው መልክ ማስተዋወቅ ይችላሉ። "በዛሬው ዕለት በከብት እርባታ ሥራ የሴቶችና የወንዶችን ሚናና እነዚህ ሚናዎች የሚሰጣቸውን ዋጋና በሕብረተሰቡ እንዲሁም በቤተሰብ ደረጃ ሴቶች ያላቸው ቦታ ላይ እንወያያለን።"

ተሳታፊዎቹ የዕለቱን አጀንዳና የመማር አላማውን በትክክል መረዳታቸውን ያረጋግጡ፡ "ግልጽ ነው ወይ? ጥያቄ አላችሁ? በዚህ ዓይነት መንገድ እንቀጥል?" የሚሉ ጥያቄዎችን በማቅረብ ተሳታፊዎች ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ይጠይቁ። ተሳታፊዎች ለሚሰጡት ግብረ መልስ አድናቆትዎን በመስጠት እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው።

ተሳታፊዎቹ ምናልባት አመቻቾቹ የመጡት ሊያመቻቹ ሳይሆን ሊያሰለጥኑን ነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ስለሆነም የክፍለ ጊዜውን ዓላማ በሚገባ ማስረዳትና ከውይይቱ መጠበቅ ያለባቸውን ከመጀመሪያው ጀምሮ ግልጽ ማድረግና ተሳታፊዎቹ ከአመቻቾች መጠበቅ ብቻ ሳይሆን አንድ ላይ ሆነው በመስራት ለራሳቸው ስጋቶች እራሳቸው መልስ ማግኘት እንዲችሉ መርዳት ያስፈልጋል።

3. የማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜውን ያካሂዱ። በከብት እርባታ ሥራ በሥርዓተ ጾታ የሥራ ክፍፍልንና ሴቶችና ወንዶች ለሚያከናውኗቸው ሥራዎችና ለሥራዎቻቸው የሚሰጣቸውን ዋጋ የተመለከተ ውይይት ለመጀመር እንዲያስችል የሴቶችንና የወንዶችን ተግባራትን የሚገልጹ ምስሎችን ይጠቀሙ።

በከብት እርባታ ውስጥ የሥርዓተ ፆታ የሥራ ክፍፍልን የሚያሳዩ ምስሎችን ያድሉ። ሁለት ሁለት ተሳታፊዎች አንድ ላይ ሆነው ምስሎቹ ለነሱ ምን ትርጉም እንደሚሰጧቸው እርስ በእርስ እንዲወያዩ ይጠይቋቸው። ሁሉም ተሳታፊዎች የተግባሩን መመሪያ መረዳታቸውንንና በነፃነት ለመወያየት ዝግጁ መሆናቸውንና የሌሎችን ሰዎች ሀሳብ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጡ። አስፈላጊ ከሆነ ሴቶችንና ወንዶች በተለያዩ ቡድኖች እንዲቧደኑ ያድርጉ።

ሁሉም ተሳታፊዎች አንድ ላይ ባሉበት ስብሰባ በቤተሰብ ወይም በማኅበረሰብ ደረጃ በወንዶችና በሴቶች መካከል ስላለው የሥራ ክፍፍል ያላቸውን ተሞክሮ እንዲያቀርቡ ይጠይቋቸው። ተሳታፊዎቹ ምስሎቹ ላይ ብቻ ሊያተኩሩ ይችሉ ይሆናል። ሆኖም ምስሎችን መጠቀም ያለብን ሰዎች ውይይቱን እንዲጀምሩ ብቻ ነው። አንድ ጊዜ ሰዎች መናገር ከጀመሩ በኋላ የምርመራ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። በውይይቱ መጀመሪያ አካባቢ ተሳታፊዎቹ መሆን ከሚገባው ይልቅ በማኅበረሰቡ ውስጥ የተለመደውን ስነ ምግባር ወይንም ባህርይ ሊያሳዩ ይችሉ ይሆናል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ በውይይቱ ወቅት የተለያዩ

የምርመራ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ግንዛቤዎቹን ማጋለጥና ወደ ጭብጡ መምጣት ያስፈልጋል። በምርመራና ታሪኮችን በመጋራት ሂደት ተሳታፊዎቹ እርስ በርስ መተማመንና በራስ መተማመንን በመፍጠር ያላቸውን ዕይታዎችና ግንዛቤዎች እንደገና ለመመርመር ሊወስኑ ይችላሉ።

ሰዎች ተነቃቅተው መናገር ሲጀምሩ እያንዳንዱ ሰው ያቀረበውን ሐሳብ ለማጠቃለል በመሞከር የውይይቱን ሞቅታ ማቀዝቀዝ አስፈላጊ አይደለም። ይልቁንም ተሳታፊዎቹ ንግግራቸውን እንዲቀጥሉ ያበረታቷቸው። በርዕሱ ላይ ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን በበቂ ሁኔታ መግለፃቸውን ካረጋገጡ በኋላ ማጠቃለያ መስጠት ይችላሉ። ከማጠቃለያው በኋላ እንደሁኔታው ተጨማሪ የምርመራ ጥያቄዎችን ይጠይቁ ወይንም ወደሚቀጥለው የውይይቱ ክፍል ይሂዱ።

ሁሉም ተሳታፊዎች በአንድ ላይ ባሉበት ስብሰባ ተሳታፊዎች በከብት እርባታ የወንዶችን የሴቶችንና የህፃናት የሥራ ድርሻዎች በዝርዝር እንዲያቀርቡ ጠይቋቸው። የተሳታፊዎቹን መልሶች በፊሊፕ ቻርት ይፃፉ።

በውጤቱ ላይ በጥልቀት ያሰላስሉ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። የትኞቹ ሥራዎች የበለጠ ዋጋ ወይም ጥቅም ያላቸው ናቸው። ለምን? ከጉልበትና ከጊዜ አንፃር የትኞቹ ስራዎች የሚከብዱ ናቸው?

ስለ ስርዓተ ፆታ የሥራ ክፍፍልና የሴቶች ሚና አለመታየት ምክንያቶች፣ መገለጫዎችና የሚያስከትሉትን ውጤት የተለያዩ የማብራሪያ ጥያቄዎች በመጠየቅ ጉዳዩ እንዲብራራ/እንዲፍታታ ያደርጉ።

በከብት እርባታ ውስጥ የሥርዓተ ፆታ የሥራ ክፍፍልን የሚያሳዩ ምስሎችን ያድሉ



በከብት እርባታ ከሥርዓተ ጾታ የሥራ ክፍፍልና የሴቶችን ሚና ዋጋ ከመስጠት ጋር የተዛመዱ ጉዳዮችን ለመፍታት የማብራሪያ ጥያቄዎችን እንደየአመቺነቱ በተለያየ መንገድ መጠቀም ይቻላል። ጥያቄዎቹ ከእያንዳንዱ ምስል ጀርባ ቢፃፉ ለአጠቃቀም የበለጠ ምቹ ይሆናሉ።

- በምስሉ ላይ የምታዩት ታሪክ በቤተሰባችሁ ወይንም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ሁኔታ በምን መልኩ ይገልጸዋል?
- አሁን እየተነጋርን ያለናቸው የስርዓተ ጾታ ጉዳዮች በቤተሰብዎ እና በማህበሩ ወይንም በግልዎ በእርሶ ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ያሳድራሉ? በዚህ ረገድ ያሎት የግል ተሞክሮ ምንድነው? ሌሎች የቤተሰብዎ አባላትስ ምን ተሞክሮ አላቸው?
- የከብት እርባታን በተመለከተ በቤተሰብዎ ወይንም በማህበረሰብዎ ውስጥ ማን ምን ይሰራል? ይህንን ጥያቄ ከከብቶች ዝርያዎች ጋር በማገናኘት ሀሳብዎን ይግለፁ።
- ለዚህ የሥራ ክፍፍል ማህበራዊና ባህላዊ መሠረቱ ምንድነው?
- ይህ የሥራ ክፍፍል የማይቀየር ነው? ወይንስ እንደሁኔታው ተለዋዋጭ ነው? ተለዋዋጭ ከሆነ በምን ዓይነት ሁኔታዎች ሊቀየር ይችላል?
- በቤተሰቡ ውስጥ የበዙትን ስራዎችና በቀን ውስጥ ለረዥም ሰዓታት የሚሰራው ማነው? በእንስሳት እርባታ በሴቶችና በወንዶች መካከል ሚዛናዊ የሆነ የሥራ ክፍፍል አለ ብለው ያስባሉ?

- በእንስሳት እርባታ በቤተሰብዎ ወይንም በማህበረሰብዎ ወንዶች መስራት የለባቸውም የሚባሉ ስራዎች የትኞቹ ናቸው? ለምን?
- በእንስሳት እርባታ በቤተሰብዎ ወይንም በማህበረሰብዎ ሴቶች መሥራት የለባቸውም የሚባሉ ስራዎች የትኞቹ ናቸው? ለምን?
- በእንስሳት እርባታ ወንዶች የሚሰሩት ሥራ ሴቶች ከሚሰሩት ሥራ የበለጠ ዋጋ ወይንም ጥቅም አለው ብለው ያስባሉ? ለምን?
- በማህበረሰብዎ ውስጥ የእንስሳት እርባታ ሥራዎችን ወንዶችና ሴቶች እኩል የሚከፋፈሉ ቤተሰቦች አሉ? እነዚህን ቤተሰቦች ከሌሎች የማህበሰቡ አባላት የተለዩ የሚያደርጋቸው ምንድነው?
- በቤተሰብዎና በማህበረሰብዎ ውስጥ ምን ዓይነት የሥራ ክፍፍል እንዲኖር ይፈልጋሉ? ይህ ዓይነቱ የሥራ ክፍፍል አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው? አሁን ካለው ሁኔታ በምን ይለያል?
- በቤተሰብዎ/በማህበረሰብዎ እርስዎ የሚፈልጉት ዓይነት የስርዓተ ጾታ የሥራ ክፍፍል እንዲኖር ምን አስተዋጽዖ ማድረግ ይችላሉ?
- እርስዎ የሚፈልጉት ዓይነት የስርአተ ጾታ የሥራ ክፍፍል እንዲኖር የራስዎን አስተዋጽዖ ከማድረግ ሊገታዎት የሚችል ምን ነገር አለ?

የሥርዓተ ፆታ የሥራ ክፍፍልንና የሴቶችን ሚና እውቅና ከመስጠት አንፃር የተደረጉ ውይይቶች ላይ የተነገሩ ታሪኮችን፣ ጭብጦችን/አንኳር ነጥቦችን በፊሊፕ ቻርቱ ላይ ይፃፏቸው። ሴቶችና ወንዶች በሰጧቸው ሐሳቦች ላይ ልዩነት ሊኖር ስለሚችል ሐሳቦቹን በትኩረት ይመልከቱ/ያጢኑ።

ከውይይቱ የመነጩ ጭብጦችንና ቁልፍ መልዕክቶች ያጠቃሏቸው። በውይይቱ የተነሱትን ተሞክሮዎች፣ ታሪኮች፣ እሴቶችንና ዕይታዎችን በማሰላሰል ተሳታፊዎች ስለጉዳዮቹ በጥልቀት እንዲያስተውሉና እንዲረዱ ያድርጓቸው።

ተሳታፊዎች መውሰድ ያለባቸውን እርምጃዎችንና እርምጃዎቹን መውሰዱ የሚያስገኘውን ጥቅም በግልጽ ይንገሯቸው። ለምሳሌ ለተሳታፊዎቹ የሚከተለውን ሊሉ ይችላሉ። “ከውይይታችን በግልጽ መረዳት እንደቻልነው…”

- በከብት እርባታ ውስጥ ለሴቶች ሚና ዕውቅናና ዋጋ መስጠት ሴቶች መረጃዎችንና አገልግሎቶችን የበለጠ እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል።
- የተሻለ ሚዛናዊና ፍትሐዊ የስርዓተ ፆታ የሥራ ክፍፍል መኖር የቤተሰቡን ምርታማነትና ደህንነት ይጨምራል።
- የቤተሰብ አባላት የጋራ ውሳኔና እርምጃ የከብቶች ምርታማነትንና የቤተሰብን ገቢ ይጨምራል።”

ከተሳታፊዎቹ ግብረ መልስ በመቀበል መልዕክቶቹን መቀበላቸውን ያረጋግጡ። ከውይይቱ የተገኙትን ጭብጦች አጠቃለው ቁልፍ የሆኑ መልክቶችን ካስተላለፉ በኋላ ተሳታፊዎቹ በግልና በጋራ ለወደፊት ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች ተነጋግረው እንዲያቀርቡ ጠይቋቸው።

ሁሉም ተሳታፊዎች ባሉበት ስብሰባ በውይይቱ በከብት እርባታ ስላለው የሥርዓተ ፆታ የሥራ ክፍፍልና ሴቶች ስለተሰጣቸው ቦታ ጠቃሚ ጉዳዮች ተለይተው መውጣታቸውን ይንገሯቸው።

እነዚህን ጉዳዮች ወደየቤታቸው ይዘው ሄደው በውይይቱ በተነጋገሩት መሠረት እርምጃ እንዲወስዱ መልዕክት ያስተላልፉ። ለምሳሌ ያህል ለተሳታፊዎቹ የሚከተሉት ሊሏቸው ይችላሉ “አሁን በውይይቱ ያገኘናቸውን አዳዲስ ሀሳቦች በግል ሕይወታችን ላይ ተግባራዊ በማድረግ በከብት እርባታ ምርታማነትና በቤተሰባችን ደህንነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያደርሱትን የስርዓተ ፆታ ግንኙነቶችን ለመለወጥ የተለያዩ ሐሳቦችን አቅርበን ስምምነት ላይ እንደርሳለን።”

ሁሉም ተሳታፊዎች በሚገኙበት ያለው የስርዓተ ጾታ ግንኙነት ተቀይሮ ሚዛናዊ የስርዓተ ጾታ የሥራ ክፍፍል እንዲኖር ተሳታፊዎቹ በግልም ሆነ በጋራ ምን ዓይነት እርምጃዎች እንደሚወስዱ ጠይቋቸው።

የእርምጃ ነጥቦች፡

- ሚዛናዊ ያልሆነ የስርዓተ ጾታ የሥራ ክፍፍል ችግርን ለመፍታት በቤተሰብዎ እንዲሁም በማህበረሰብዎ ምን እርምጃዎችን መውሰድ ይፈልጋሉ?
- ከውይይቱ ያገኟቸውን ቁልፍ መልዕክቶች ለቤተሰብዎ፣ለጎረቤቶችዎና ለማህበረሰብዎ አባላት በምን መልኩ ሊያካፍሉ አቅደዋል?
- ዕቅድዎን ለመተግበር ምን ተግዳሮቶች ሊገጥሙኝ ይችላሉ ብለው ያስባሉ?
- ምን ዓይነት ለውጦች እንደመጡስ እንዴት ማወቅ እንችላለን? እርስዎ የወሰዷቸው እርምጃዎች ለውጥ ስለማስከተላቸው ምን ምን ነገሮች ጠቋሚ ሆነው ሊያመለክቱ ይችላሉ? ውጤቶቹን/መልሶቹን በፊሊፕ ቻርት ላይ ይመዝግቡ። ሴቶችንና ወንዶችን ነጥለው የሚመለከቱ እርምጃዎች ካሉ ይህንኑ የተለየ ከለር ባለው መጻፊያ አጉልተው ያሳዩ።

እርምጃዎቹ ለግለሰቦችና ለቡድኖች ሊያስገኙ የሚችሉትን ለውጥና ጥቅም የሚያሳዩ ታሪኮች በመናገር ተሳታፊዎቹ እርምጃዎቹን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያነሳሷቸው። ተሳታፊዎቹ ጉዳዩን እንደራሳቸው ጉዳይ ወስደው የቀረቡትንና ስምምነት ላይ የተደረሱባቸውን የመፍትሔ ሀሳቦች ለመተግበር መነሳሳታቸውን ያረጋግጡ።

ለእያንዳንዱ እርምጃና የመማማር ቡድን ተጠሪ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን በመምረጥ የክትትልና የግብረ መልስ ቡድኖች እንዲኖሩ ያድርጉ። በእያንዳንዱ ቡድን ሴቶችና ወንዶች እንዲኖሩበት ይመከራል። ቡድኖቹ እስከሚቀጥለው የማህበረሰብ ውይይት ጊዜ ድረስ መማማራቸውን እንዲቀጥሉ እርስዎ ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው ያረጋግጡላቸው።

4. የማህበረሰቡ ውይይቱ ላይ ጥቂት ካሰላሰሉ በኋላ ይደምድሙት። የሚከተለውን ማለት ይችላሉ። "አሁን ውይይቱን የምንቋጭበት ጊዜ ነው። ዋና ዋና ሐሳቦችን፣ ያስተዋልናቸውን ነገሮች፣ አሃ ያሰኙንን ነገሮች፣ ያስደነቁንን ነገሮችንና ቀጣይ እርምጃዎችን ጠቅለል አድርገን ለጥቂት ጊዜ እናሰላስልባቸው። የማሰላሰያ ጥያቄዎቹን በፊሊፕ ቻርት ላይ ይፃፉ።

"እኔ እንደማስበው ከውይይቱ የተገኙ አንኳር ነጥቦች                    ናቸው።

- እያንዳንዱ ተሳታፊ የማሰላሰያ ጊዜ እንዲኖረው ይጠይቁ።
- ተሳታፊዎች ያገኙትን ግንዛቤ እንደመጣላቸው ወዲያውኑ እንዲጋሩ ይጠይቁ።
- ተሳታፊዎች ያገኙትን ግንዛቤ ወይንም አሰላስለው ያፈለቋቸውን ሀሳቦች በፊሊፕ ቻርቱ ላይ ይፃፉ።
- ተሳታፊዎቹ አሰላስለው ያመነጯቸውን ሀሳቦች ገምግመው ጭብጦቹን ልዩ ቀለም ባለው መፃፊያ አጉልተው ያሳዩ።
- ጭብጦቹን በፊሊፕ ቻርት ላይ ይመዝግቡ።

ተሳታፊዎቹ ለመማር ያደረጉት ጥረት የሚደነቅ መሆኑን ጠቅሰው ያመስግኗቸው። በክፍል ጊዜው መጨረሻ ከማስታወሻ ያዡ ጋር በመቀመጥ በሂደቱ ላይ ያሰላስሉ። ማስታወሻው ላይ የሰፈረውን አብራችሁ በመገምገም ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች በማስታወሻው ያልተካተቱ ከሆነ አካቷቸው። ማስታወሻዎቹና ሪፖርቶቹ ወዲያውኑ መጻፍ ይኖርባቸዋል።

ለአመቻቾች ተጨማሪ መረጃዎች

የስርዓተ ጾታ ጉዳዮች በእንስሳት እርባታ አጠቃላይ እይታ

- ሴቶች ውሃ ቀድቶ ማምጣትን፣ የከብቶችን ቤቶች ማፅዳትንና የመሳሰሉ ብዙ ጉልበት የሚጠይቁ ስራዎችን የመስራት ሀላፊነት አለባቸው። ሆኖም ሥራቸው የማይታይ በመሆኑ ለስራቸው የሚሰጠው ዋጋና ግምት አናሳ ነው።
- የእንስሳት እርባታን በተመለከተ በቤተሰብ ውስጥ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው የስራ ክፍፍል ሚዛናዊነት የጎደለው ነው። ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ብዙ የሥራ ጫና አለባቸው። ይህ እንደ እንስሳቱ ዝርያ ሊለያይ ይችላል።
- ምንም እንኳ ሴቶች በእንስሳት እርባታ ቁልፍ ሚና ቢኖራቸውም ከእንስሳቱ በሚገኘው ጥቅም ላይ ተደራሽነት ያላቸውና በበላይነት ውሳኔ የሚሰጡት ወንዶች ናቸው። የሴቶች በእንስሳት ላይ ያላቸው ቁጥጥር ውስን ነው።
- በቤተሰብ ውስጥ ሴቶች የራሳቸውን ጉልበት እንኳን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የመወሰን መብታቸው የተገደበ ነው። ሴቶች የኢኮኖሚ ጥገኛ መሆናቸው በሚያስፈልጋቸውና በሚመርጧቸው/በሚወዷቸው ነገሮች ላይ የራሳቸውን ውሳኔ እንዳይወስዱ ይገድባቸዋል። ሆኖም በአንዳንድ ማህበረሰቦች ሴቶች የእንስሳት ተዋፅዖችን በመሸጥ፣ በአነስተኛና ጥቃቅን ንግድ ወይንም በጉልበት ሥራ በመሰማራት አነስተኛ የሆነ ገቢ ያገኛሉ። ይህም በወንዶች ላይ ሙሉ በሙሉ ጥገኛ እንዳይሆኑ ይረዳቸዋል። በአንዳንድ ቤተሰቦች ከእንስሳት ሽያጭ የሚገኝ  ዳጎስ ያለ ገቢ ላይ ሴቶችና ወንዶች በጋራ የሚወስኑበት ሁኔታም አለ።
- ሴቶች ስልጠናን፣ የእንስሳት ቴክኖለጂዎችን እንዲሁም የኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን የማግኘትና የመጠቀም እድላቸው ውስን ነው።
- ይህንን ሁኔታ ለመለወጥና እየታዩ ያሉ መልካም ተሞክሮዎችን ለማበረታት ወንዶችና ሴቶች ችግሮቹ በእርግጥም መኖራቸውን መቀበልና ግንዛቤ መፍጠር እንዲሁም ገዳቢ የሆኑ የስርዓተ ፆታ ግንኙነቶችን መለወጥ ይኖርባቸዋል።

ክፍለ ጊዜውን ለመከለስ የሚጠቅሙ ምክሮች

- ክፍለ ጊዜውን ከባለፈው ትምህርት ጋር በማገናኘት ውይይቱ ፍሰት እንዲኖረው ያድርጉ፡፡ ይህም ተሳታፊ ቡድኖች ለማሰራጨት የያዙትን እቅድ እንዲሁም የሚወስዷቸው እርምጃዎች የበለጠ እንዲረዱ ያስችላቸዋል።
- የክለሳ ክፍለ ጊዜዎችን ለማካሄድ ብዙ መንገዶች አሉ። እነዚም በትንሽ ቡድኖች ሆኖ ማሰላሰል (small group reflection)፣ ሁሉም ተሳታፊዎች ባሉበት ማሰላሰልን (plenary reflection)፣የጋራ ጭብጦች በትላልቅ ክቦች ሆኖ መስራትን፣ ከትምህርታዊ መጽሔቶችና ከቡድን ከለሳዎች የተገኙ ሪፖርቶችን መጠቀምና የመሳሰሉት ናቸው።
- ተሳታፊዎቹ ውይይቶችን እንዲያስታውሷቸውና ትውስታቸውንም ለማደስ ምስሎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ይህንን ማድረጉ ተሳታፊዎች እንዲነሳሱና ተሞክሯቸውን እንዲያሰላስሉ ይረዳል።

# ተጨማሪ ንባቦች

Kinati, W. and Mulema, A.A. 2016. A gendered analysis of community profiles of target sites for small ruminant value chain interventions in Ethiopia. ICARDA/ILRI Project Report, Nairobi, Kenya: ILRI.

Mulema, A.A., Farnworth, C.R. and Colverson, K.E. 2017, Gender based constraints and opportunities to women's participation in the small ruminant value chain in Ethiopia. A community capitals analysis Community Development 48:1-19. http://dx.doi.org/10.1080 15575330.2016.1267785

# ክፍል ጊዜ 3፡ በሴቶች የከብት ሀብት ባለቤትነትና ቀጥጥር ላይ ያሉ ግንዛቤዎችና አመለካከቶች

## የክፍል ጊዜው መግለጫ

የዚህ ክፍል ጊዜ ትኩረት ሴቶች በከብት ሀብት ላይ ስላላቸው የባለቤትነትና የመቆጣጠር ሁኔታን በተመለከተ ሰዎች ያላቸውን ግንዛቤዎችና አመለካከቶች እንዲሁም እነዚህ ግንዛቤዎችና አመለካከቶች በሴቶች ውሳኔ ሰጭነት በእንስሳት ምርታማነትና በቤተሰብ ደህንነት ላይ የሚያሳድሯቸውን ተፅዕኖዎች ለማጥናት ነው።

## የክፍል ጊዜው ዓላማዎች

በማህበረሰቡ ውይይት መጨረሻ ተሳታፊዎቹ የሚከተሉት ተግባራት ማከናወን ይችላሉ

- በከብት ሐብት ላይ ሴቶች ያላቸውን ባለቤትነትና ቁጥጥር በተመለከተ ያሉትን ግንዛቤዎችንና አመለካከቶችን በማጥናት ጥያቄ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋሉ።
- ሴቶች በከብት ሀብት ላይ ውስን የሆነ የባለቤትነት መብት እንዲኖራቸው ያደረጉትን ምክንያቶችና መገለጫዎቻቸው በመለየት ይተነትናሉ።
- ሴቶች በከብት ሀብት ላይ ስላላቸው ባለቤትነትና በማሕበረሰቡ ውስጥ ያሉ ስውር ዘይቤዎች (stereotypes) በሴቶች፣ በቤተሰቡና በማሕበረሰቡ የሚኖራቸውን ውጤቶች በመለየት በጥያቄ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋሉ።
- ሴቶች በከብት ሀብት ላይ ያላቸውን ባለቤትነትና ቁጥጥር የሚገድቡ ግንዛቤዎችና ስውር ዘይቤዎችን እንዲሁም የሚያስከትሏቸውን ችግሮች ለማስተካከል እርምጃ ይወስዳሉ።

## የክፍል ጊዜው ይዘት

- ከብቶችን የማግኛ መንገዶች
- ሴቶች በከብቶች ላይ ያላቸው ባለቤትነትና ቁጥጥር
- ሴቶች በከብቶች ላይ ያላቸውን ባለቤትነትንና ውሳኔ ሰጭነትን በተመለከተ ያሉ ችግሮችና መልካም ዕድሎች
- ሴቶች በከብቶች ላይ የባለቤትነት መብት ማጣትና የሚያስከትሏቸው ውጤቶች
- ሴቶች በከብቶች ላይ ያላቸውን ባለቤትነት ለመጨመር የሚወሰዱ እርምዎች

## የመማሪያ ዘዴዎችና ቁሳቁሶች

- ሚና ተውኔት
- የማሰላሰል ውይቶች
- ታሪክ ነገራ
- የምርመራ ጥያቄዎች

ሊወስድ የሚችለው ጊዜ ከ 3-4 ሰዓታት

## የመማር ተግባሮች

1. ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ይከልሱ። ተሳታፊዎቹን እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ ጊዜያቸውን በማህበረሰብ ውይይቱ ላይ በማዋላቸው አመስግኗቸው። ክፍለ ጊዜውን መከለሱ ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ከአሁኑ ጋር አገናኝቶ ውይይቱ ፍሰትና ቀጣይነት እንዲኖረው ከማስቻሉም በላይ ተሳታፊዎቹ የዚህን ክፍለ ጊዜ አላማ በሚገባ እንዲረዱት ያስችላል። ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ሳይሳተፉ የቀሩ ሰዎች መኖር አለመኖራቸውን ያጣሩ። አዲስ ተሳታፊዎች ካሉ እራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ይጠይቋቸው። ክለሳው በሚደረግበት ጊዜ ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዋና ዋና ሐሳቦች ሊያገኙ እንደሚችሉ ይንገሯቸው።

የክለሳውን ዓረፍተ ነገሮች በፊሊፕ ቻርት ወረቀት ላይ በግልጽ ይጻፉ።

- ባለፈው ስብሰባ የተወያየነው ____________________________________________ ____________ነበር

- የተስማማንባቸው እርምጃዎች________________________________________________________ ነበሩ።

- እኔ እያመጣኋቸው ያለኋቸው ለውጦች _________________________________________________ ናቸው።

ቦታውና ጊዜ ከፈቀደ ተሳታፊዎች በክብ ቅርጽ እንዲቀመጡ ይጠይቋቸው። እያንዳንዳቸው ባለፈው ክፍለ ጊዜ ያገኙትን ተሞክሮዎች (ዋና ዋና ሐሳቦች፣ የእርምጃ ሐሳቦችንና ያስተዋሏቸውን ነገሮች) አረፍተ ነገሮቹን በመሙላት እንዲገልጹ ይጠይቋቸው።

ለትንሽ ጊዜ በግል የማሰላሰያ ጊዜ እንዲኖራቸው ካደረጉ በኋላ ተሳታፊዎች አንድ ላይ እንዲሆኑ ያድርጉ። በመጀመሪያ ፈቃደኛ በሆነ ተሳታፊ በመጀመር ከዚያ በኋላ በክቡ የተቀመጡትን አንድ በአንድ ባለፈው ክፍለ ጊዜ ያገኙትን ተሞክሮ ብዙም ሳይጨነቁ በአእምሮአቸው የመጣውን እንዲናገሩ ይገፋፏቸው። ያልተማሩ በመሆናቸው በውይይቱ እምብዛም ለማይሳተፉ ተሳታፊዎች ምሳሌዎችን በመስጠት እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። ሴቶች እንዲሳተፉ ማበረታት አስፈላጊ ነው። ይህ የመማማር ተሞክሮ ለተሳታፊዎች አስደሳች እንጂ አስፈሪ እንዳይሆን የበኩልዎን ጥረት ያድርጉ።

- ተሳታፊዎቹ ለሚሰጥዋቸው ምላሾች ተገቢውን አድናቆት ከሰጡ በኋላ ምላሾቹን ፊልፐ ቻርቱ ላይ ይጻፉ። ምላሾቹንም በመገምገም ከዕለቱ የማህበረሰብ ውይይት አጀንዳ ጋር ያገናኟቸው።

- የውይይቱን መሠረታዊ ህጎች ተሳታፊዎች በቀላሉ ሊያዩአቸው በሚችሉበት ቦታ በማስቀመጥ ህጎቹን እንዲከተሉ ያሳስቧቸው።

- የግብረ መልስ ቡድኖችን በእነሱ በጎ ፈቃደኝነት ላይ ተመስርተው ይመድቡ።

2. በአጀንዳው ላይ ተመርኩዘው የዕለቱን የማህበረሰብ ውይይት ርዕሶች ያስተዋውቁ

አርዕስቶችን ለማስተዋወቅ የሚቀጥለውን ማለት ይችላሉ። "ዛሬ ሴቶች በእንስሳት ሀብት ላይ ስላላቸው ባለቤትነትና ቁጥጥር ላይ እንወያያለን። የሴቶች የእንስሳት ባለቤትነትን በሚመለከት ያሉትን ግንዛቤዎች፣ አመለካከቶችንና ድርጊቶችን፣ መገለጫቸውን እንዲሁም የሚያስከትሉት ውጤቶች እንዳስሳለን። ፣ በመጀመሪያ የዚህ ስብሰባ ተሳታፊ የሆኑ ሁለት ሰዎች አጠር ያለ ሚና ሲጫወቱ እንስማለን። የሚና ትወናውን በጥሞና ካዳመጥን በኋላ በትወናው ወቅት በተንፀባረቁ ግንዛቤዎች፣ አመለካከቶችና ባሕሪዎች ላይ ውይይት እናደርጋለን። በማስተዎልም ሴቶች በማህበረሰባችን ውስጥ እንዴት የከብት ሐብቶችን በባለቤትነት እንደሚቆጣጠሩ የሚያሳዩ የሕይወት ተሞክሮዎቻችንን፣ ምልከታዎቻችንና የተለያዩ ተግባራትን እያነሳን እንነጋገራለን።

የሴቶችን የእንስሳት ባለቤትነትን በተመለከተ ያሉትን ተግዳሮቶችና የተግዳሮቶቹን መንስዔዎችና እንዲሁም የሚያስከትሉትን ውጤቶች ካሰላሰልን በኋላ ችግሮቹን ለመቅረፍ የመፍትሔ ሀሳቦችን አቅርበን ለመተግበር ቃል እንገባለን።

ሐሳቡ ለተሳታፊዎቹ ግልጽ መሆኑን ያረጋግጡ። ጥያቄዎች እንዳሏቸው ወይንም ተጨማሪ ማብራሪያ የሚፈልጉ መሆን አለመሆናቸውን ያረጋግጡ።

3. የማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜውን ያካሂዱ። ውይይቱን በሚና ትወና ያስጀምሩ። አጫጭር ትወናዎች፣ መቼቶች (scenarios) ወይንም ክርክር የሚያስነሱ መልዕክቶችን መጠቀም ሰዎች በጥሞና እንዲያስቡና ታሪኮቻቸውን እንዲጋሩ ያደርጓቸዋል። ሆኖም እነዚህን በሚገባ ለመጠቀም አስቀድሞ የትወናውን ጽሑፎች በሚገባ ማዘጋጀት፣ የሚተውኑ ሰዎችን መለየትና ማሰልጠን ይጠይቃል። በተውኔቱ ውስጥ ወንዶችንና ሴቶችን ማካተት ሁለቱ ፆታዎች ስለሴቶች በከብት ሀብት የባለቤትነት ጥያቄ ላይ ያላቸውን ግንዛቤና አመለካከት እንዲያንጸባርቁ ይረዳል።

በመጀመሪያ ተውኔቱን የሚያቀርቡ ተሳታፊዎች ወደ መድረኩ እንዲመጡ ጋብዟቸው። ከተውኔቱ በኋላ ተዋንያኑ በመድረኩ ላይ ጥቂት እንዲቆዩ ይጠይቋቸው። ተወናዮቹን በመድረኩ እንዲቆዩ ማድረግ ውይይቱ በሚደረግበት ጊዜ ተሳታፊዎቹ ተዋናዮቹ ያሉትን በመጥቀስ እንዲናገሩ/ አስተያየት እንዲሰጡ ይረዳል።

ተሳታፊዎቹ በተውኔቱ ላይ በተነሱት ሀሳቦች/መልዕክቶች ላይ ተመርኩዘው የራሳቸውን ምልከታና ተሞክሮዎች ለተሳታፊዎቹ እንዲያካፍሉ ይጋብዟቸው። የተሳታፊዎቹ ምላሽ የቀዘቀዘ ከሆነ ከልምድ የተገኙ የተለያዩ ምሳሌዎችንና እውነታዎችን በማቅረብ ሴቶች በከብት ሀብት ላይ ስላላቸው የባለቤትነት መብት ላይ የራሳቸውን ግንዛቤ አስበው እንዲናገሩ ያድርጓቸው። ክርክር የሚያስነሱ ሀሳቦችንም ሆን ብለው በማንሳት ተሳታፊዎች በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አቋም ይወቁ።

የሚከተሉት የማሰላሰያ ጥያቄዎችን ይጠቀሙ

- በተውኔቱ ወቅት ምን እንደተከሰተ /እንደታየ ይታዘባሉ?

- ስለ ውይይቱ ገጸ ባህሪዎች ምን ያስባሉ? እነዚህን ገጸ ባህሪዎች የመሳሰሉ ሰዎች በቤተሰባችሁና በማህበረሰባሁ ውስጥ አሉን?

- ተውኔቱ በቤተሰባችሁና በማሕበረሰባችሁ ያለውን ሁኔታ በምን አይነት ሁኔታ ያንጸባርቃል/ይገልፃል?

የሚከተሉትን የውይይት/የማብራሪያ ጥያቄዎችን ይጠቀሙባቸው።

- የማህበረሰቡ አባላት ባለቤትነትንና ቁጥጥርን በምን መልክ ይገልጹታል?

- በማህበረሰባችሁ ውስጥ ሴቶች የእንስሳት ሙሉ ባለቤትነትና ቁጥጥር የማድረግ ሀላፊነት አላቸው? መልሱ አዎ ከሆነ ለየትኛው የከብት ዝርያ? ለምን?

- ሴቶች ከከብቶች የሚገኘውን ገቢ ይቆጣጠራሉ? የትኞቹን ዝርያዎች?
- ሴቶች ከከብቶች የሚገኘው ገቢ አጠቃቀም በተመለከተ ባሎቻቸው ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ? በምን መንገድ? እስቲ ታሪኮችዎን ይንገሩን።
- ሴቶች በከብቶች ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ሊኖራቸው የሚችለው በምን ሁኔታ ነው? ለምሳሌ በጋብቻ ወቅት በስጦታ ወይም በሌላ መልክ የተሰጧቸውን ከብቶች የመቆጣጠር መብት አላቸው?
- ባልና ሚስት በሚፋቱበት ጊዜ ንብረቶቹን በተመለከተ የሚደረገው ምንድነው?
- የሴቶች በከብት ሀብት ላይ ያላቸው ባለቤትነትና ቁጥጥር ሴቶች ተሰሚነት እንዲኖራቸውና የሚመርጡትን ማድረግ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል? መልሱ አዎን ከሆነ የትኞቹ ከብቶች? ምሳሌ ይስጡ።
- አሁን በሕብረተሰቡ ውስጥ የተለመደው የሴቶች የከብት ሐብት ባለቤትነትና ቁጥጥር መኖር ወይንም አለመኖር ሁኔታ የማህበረሰቡን አባላት እንዴት ሊጠቅም ወይም ሊጎዳ ይችላል?
- የሴቶችን የከብት ሐብት ባለቤትነትና ቁጥጥር በተመለከተ ከራስዎ ተሞክሮ ተነስተው ምን ታሪኮችን ሊነግሩን ይችላሉ?
- በአጠቃላይ ከብቶችን በተመለከተ ማን የበለጠ የባለቤትነትና የመቆጣጠር መብት አለው? ወንዶች ወይንስ ሴቶች?
- ሴቶች የከብቶች ባለቤት ቢሆኑና የመቆጣጠር መብት ቢኖራቸው ምን በጎና መጥፎ ውጤቶች ይኖሩታል?
- በእርስዎ ማህበረሰብ የሴቶችን የከብት ሀብት ባለቤትነትና ቁጥጥርን በተመለከተ ምን አይነት አባባሎች ምሳሌዎችና አገላለጾች አሉ? ትርጉማቸውስ ምንድነው? ከአባባሎቹ ጋር ይስማማሉ ወይንስ አይስማሙም? የነዚህ አባባሎች ምሳሌዎችና አገላለጾች አንደምታ ምንድነው?
- ሴቶች የከብት ሀብትን በባለቤትነት ቢይዙና ቢቆጣጠሩ ወንዶች ኃይላቸውንና ስልጣናቸውን ያጣሉ? ለምን?
- እርስዎ በቤተሰብዎ ውስጥ ከብቶችን መግዛትን ወይንም መሸጥን በተመለከተ የምትወስኑት በምን ዓይነት ነው? ለምን? ታሪኩን በዝርዝር ይንገሩን።
- እስካሁን የተወያየንባቸውን መሰረት በማድረግ የጉዳዩ ተለዋዋጭነት የከብት ምርታማነትንና የቤተሰብ ጤና ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል?

በውይይቱ ወቅት የተካፈልናቸውን ልምዶችን፣ ተሞክሮዎችን፣ ዋና ዋና ሐሳቦችን ወይንም ጭብጦችን በፊሊፕ ቻርቱ ላይ ይጻፉ። ተሳታፊዎቹ ያነሷቸውን ሐሳቦች ይጭመቋቸው። ጭብጦቹን እንደ ውይይቱ ማጠቃለያ ቁልፍ መልዕክቶች በመያዝ በተነሱት ተሞክሮዎች፣ ታሪኮች፣ እሴቶችና አመለካከቶች ላይ ያሰላስሉ።

ተሳታፊዎቹ መውሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎችና እንዲከተሉ የተመከሩትን ባሕሪዎች በተመለከተ ግልጽ የሆነ መልዕክት ያስተላልፉ። መልዕክቱን በሚከተለው መንገድ መግለፅ ይችላሉ።

ከውይይታችን በግልጽ ያገኘናቸው የሚከተሉት ናቸው።

- የሴቶች በከብት ሀብት ላይ ባለቤትነትና ቁጥጥር ማጣት ውሳኔ የመስጠት አቅማቸውንና ለመረጃና አገልግሎት ያላቸውን ተደራሽነት ይገድባል።
- ወንዶችና ሴቶች በከብት ሐብት ላይ የጋራ ባለቤትነትና ቁጥጥር ሲኖራቸው ሴቶችን ለማብቃት ከማስቻሉም በላይ ሴቶች በውሳኔ ሰጭነት ያላቸውን ተሳትፎ ይጨምራል።በተጨማሪም የከብቶችን ምርታማነትና የቤተሰብ ደህንነትን ይጨምራል።

አሁን የተስማማንባቸው ቁልፍ መልዕክቶች በግል በራሳችን ሕይወት ላይ በጋራ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለንን ሀሳቦች አቅርበን እንስማማለን። መማማሩና ማሰላሰሉን እስከሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ በመቀጠል የሴቶች የእንስሳት ባለቤትነት በተመለከተ ለውጦች እናመጣለን።

ሁሉም ተሳታፊዎች በአንድ ላይ ባሉበት ስብሰባ ሴቶች በከብት ሀብት ባለቤትነትና ቁጥጥር እንዲሁም ከከብቶች የሚገኙ ጥቅሞችን በተመለከተ ያሉትን ገዳቢ ግንዛቤዎችና ድርጊቶች ለመቀየር ተሳታፊዎች በግል ወይንም በግልና በጋራ ሊወስዷቸው የሚችሉትን እርምጃዎች እንዲለዩ ይጠይቋቸው።

- የሴቶችን የከብት ሀብት ባለቤትነትና ቁጥጥር በተመለከተ ያሉትን ገዳቢ ግንዛቤዎችና ድርጊቶች ለመቀየር እርስዎ በቤተሰብዎ ወይንም በቤተሰብዎና በማህበረሰብዎ ውስጥ ምን እርምጃ ሊወስዱ ይፈልጋሉ?
- ከዚህ ውይይት ያገኙትን ቁልፍ መልዕክቶች በምን ዓይነት መንገድ በቤተሰብዎና በሰፈርዎ ለማሰራጨት አስበዋል?
- በወሰዱት እርምጃ ምክንያት ምን አይነት ለውጥ እንደመጣ በምን ልናውቅ እንችላለን? የወሰዱት እርምጃ ውጤት ማምጣቱን የሚያሳዩ ምን ዐይነት ጠቋሚ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ?

ውጤቱን በፊሊፕ ቻርት ላይ ይመዝግቡና የታቀዱትን እርምጃዎች የተለየ ቀለም ባለው ከለር አጉልተው ያሳዩ።

ተሳታፊዎቹ የታቀዱትን እርምጃዎች እንዲተገብሯቸው እርምጃዎቹ ለግለሰቦች፣ ለቡድኖችና ለቤተሰቦች ሊያመጡ የሚችሉትን ጥቅሞች በምሳሌ በማስረዳት ያነሳሷቸው። ተሳታፊዎቹ ችግሩን የተረዱ መሆናቸውንና በመፍትሔ ሀሳቦች ላይ ተስማምተው እርምጃ ለመውሰድ የተነሳሱ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

4. በክፍለ ጊዜው መጨረሻ ቁልፍ ትምህርቶቹ ላይ ያሰላስሉ። የሚከተለውን መናገር ይችላሉ። “አሁን ውይይቶቻችንን ልናበቃ ነው። ውይይቱን ጠቅለል አድርገን ዋና ዋና ነጥቦች ላይ፣ ያስተዋልናቸው ነገሮች ላይ፣ አሃ ያሰኙንና ያስደነቁን ነገሮች ላይ እናሰላስል።”

የማሰላሰያ ጥያቄዎችን በፊሊፕ ቻርት ላይ ይጻፉ፤፤

- ከውይይቱ ለእርስዎ በግልዎ ግልጽ የሆነሎት ምንድነው?

ተሳታፊዎቹ በጥንድ በጥንድ በመሆን በአእምሯቸው ውስጥ ጎልቶ የታዩአቸውን ነገሮች ለጥቂት ጊዜ እንዲያሰላስሉ ጠይቋቸው። ሁሉም ተሳታፊ ባለበት ስብሰባ ላይ ተሳታፊዎች ያስተዋሏቸውን ነገሮች ወዲያው ወደ አእምሯቸው እንደመጣ እንዲያጋሩ ጠይቋቸው። ተሳታፊዎች ያስተዋሏቸውን ነጥቦች በፊሊፕ ቻርት ላይ በማስፈር የጋራ የሆኑ ጭብጦች መኖራቸውን ይመልከቱ። እነዚህን የጋራ ጭብጦች በፊሊፕ ቻርቱ ላይ ይመዝግቡ። ሴቶችን ወይንም ወንዶችን በተናጠል ወይንም ሁለቱን ጾታዎች የሚመለከቱ እርምጃዎች ካሉ በተለየ ከለር አጉልተው ያሳዩአቸው። ተሳታፊዎች ለመማር ያሳዩትን ጥረቶች በማድነቅ ምስጋና ይስጧቸው።

ማስታወሻ ያዦችን ያመስግኑ። የሚቀጥለውን ስብሰባ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ከነገሯቸው በኋላ በተጠቀሰው ሰዓትና ጊዜ ሁሉም ተሳታፊዎች እንደሚገኙ ያሎትን ተስፋ ይገልጹላቸው።

ለአመቻቾች ተጨማሪ መረጃዎች

ሴቶች በከብቶች ላይ ያላቸው ባለቤትነትና ውሳኔ ሰጭነት

ተጠቃሚነት - ማለት አንድን ሀብት መሸጥን መለወጥን ማሻሻልን ሳያካትት የመጠቀምን ዕድል ብቻ የሚሰጥ ነው።ተጠቃሚነት በተለያዩ የውሳኔ ሰጭነት ደረጃዎች ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።

ቁጥጥር - ማለት ሀብቶቹን ለመግዛት ለመሸጥ ወይንም ለማሻሻል የሚያስችል ሙሉ ስልጣን ማለት ነው። ቁጥጥሩ በጣም ትንሽ የተወሰነ ወይንም ሙሉ ቁጥጥር ሊሆን ይችላል።

በአጠቃላይ እንደሚታየው የከብቶች ባለቤትነት የወንዶች ሆኖ ሴቶች የባለቤትነት መብት ካላቸው ብዙውን ጊዜ የሚኖሯቸው ባለቤትነት በጎችንና ፍየሎችን የመሳሰሉ ትናንሽ እንስሳት ላይ ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ሴቶች የእንስሳት ባለቤትና ተቆጣጣሪ ከሆኑና በሕዝባዊ ስብሰባዎች የሚሳተፉ ከሆነ እንዲሁም ከቤት አካባቢ ርቀው የሚጓዙ ከሆነ አመራር ሰጭነታችንን ወይንም ተፅዕኖ አድራጊነታችንን እናጣለን ብለው ወንዶች ስለሚፈሩ ነው። በሌላ አባባል ሴቶች የከብት ሀብትን የሚቆጣጠሩ ከሆነና ከከብት እርባታ ጋር የተያያዙ የህብረት ሥራ ማህበራት አባላት ከሆኑ ወንዶች የአባወራነት ሚናችንን እናጣለን ብለው ይሰጋሉ ማለት ነው።

ባለቤትነት እንደየቦታው/እንደየሀገሩ ይለያያል። የጋራ ወይንም የግል ባለቤትነት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ተለዋዋጭነቱን እንደየአግባቡ ማጤን አስፈላጊ ነው።

በማህበራዊ ቡድኖች የአርቢዎች የህብረት ሥራ ማህበር ጨምሮ የሴት አባላት ቁጥር በጣም አነስተኛ ወይንም ምንም ከሆነባቸው ምክንያቶች አንዱ ይኸው በሴቶች የባለቤትነት መብት ላይ ያለ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው።

በሁሉም የቤተሰብ ኑሮ ገጽታዎች የወንዶች የበላይነት በተደጋጋሚ በተለያዩ አካሎች እንዲጠናከር ይደረጋል። እነዚህ አካሎች ወንዶች፣ ሴቶች፣ የማህበረሰብና የልማት ባለሙያዎች፣ የውጭ አማካሪዎች እንዲሁም በወንዶች በኩል የቤተሰብ አገልግሎቶችን የሚሰጡ አካላት ሊሆኑ ይችላሉ። ወንዶችና ሴቶች ይህንን የተለመደና ትክክለኛ የሆነ ድርጊት አድርገው ሊቀበሉ ይችላሉ። ይህ አድራጎት ስልታዊ በሆነ መንገድ ሴቶችን ከውሳኔ ሰጭነት፣ ከአቅም ግንባታ ዕድሎች፣ የቴክኖሎጂ መረጃና የምክር አገልግሎቶችን ከማግኘት እንዲሁም እንስሳትን ጨምሮ ሌሎችን ምርታማነትን ከሚያስከትሉ ሀብቶች እንዲገለሉ ያደርጋቸዋል። ሴቶች እንዲሰሙና መብታቸውን እንዲጠቀሙ ሊረዷቸው የሚችሉ ማህበራዊ ቡድኖች አባል እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን አቅም ስለማያገኙ የቡድኖቹ የአባልነት መስፈርቶችን አሟልተው አባል አይሆኑም።

ሴቶች በከብት አስተዳደር ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። በምርታማ ሀብቶች ላይ ተሳትፎ ማድረጋቸው በከብቶች ምርታማነትና ብሎም በቤተሰብ ኑሮ መሻሻል ላይ ወሳኝ  ሚና እንዲኖራቸው ያደርጋል። ስለሆነም የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት አስፈላጊ ነው። የአስተሳሰብና የባህርይ ለውጥ ማምጣት የሚኖርብን ሴቶች የከብት ባለቤትነትና ቁጥጥር እንዲሁም ውሳኔ ሰጭነትን በተመለከተ ነው።

ወንዶች የሚከተሉት ድርጊቶች እንዲፈጽሙ እናበረታታለን

- ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር ከድል አድራጊነት ስሜት/ፍላጎት ይልቅ በእኩልነትና አብሮነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ለመመስረት መሻት። ይህም ሴቶችና ወንዶች እኩል መብት እንዳላቸውና ሴቶች የራሳቸው ፍላጎቶች፣ ምኞቶች፣ ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮችና ዕውቀት እንዲሁም እንደ ወንዶች ሁሉ እነዚህን የማግኘት ወይንም የመፈፀም መብት እንዳላቸው መቀበል

- ሴቶች በከብት አያያዝ ላይ ያላቸውን ዕውቀትና ሚና መገንዘብና ማድነቅ
- ሴቶች በውሳኔ ሰጭነት፥ በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችና በከብት ኤክስቴንሽን ሥራዎች እንዲሁም በሌሎች ከእንስሳት ሥራ ጋር በሚሰሩ ስራዎች እንዲሳተፉ ማበረታታት
- ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር ባላቸው ሀብት ላይ ቁጥጥርን፣ ውሳኔ ሰጭነትን፣ ሚዛናዊ ያልሆነ የስርአተ ፆታ ግንኙነትንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ለመነጋገር መፈለግና ቅድሚያ መውሰድ
- የሴቶችን የእንስሳት ባለቤትነትን በሚመለከት ያሉትን ግንዛቤዎች መፈተን/መቃወም ይጠበቅባቸዋል። ይህም ሴቶች እንስሳትን በባለቤትነት ከያዙና ከተቆጣጠሩ በሕዝባዊ ስብሰባዎች ከተሳተፉ እንዲሁም ከቤታቸው ውጭ የሚጓዙ ከሆነ ወንዶች የቤተሰብ የበላይ አስተዳዳሪዎችና ተፅዕኖ አሳዳሪዎች መሆናቸው ይቀራል የሚለውን የወንዶችን ግንዛቤ መፈተንን/መቃወምን ይጨምራል።
- ሴቶች እንስሳትን እንደ ንብረታቸው የመያዛቸውን አስፈላጊነትና ቤተሰብ በቂ ምግብ እንደያገኝ የተለያዩ ምግቦችን እንዲመግቡ በማድረግ ረገድ ያላቸውን አዎንታዊ ተፅዕኖ ማድነቅ

## ተጨማሪ ንባብ

Galie, A., Mulema, A., Mora Benard, A.M., Onzere, S. and Colverson, K. 2015, Exploring gender perceptions of resource ownership and their implications for food security among rural livestock owners in Tanzania, Ethiopia and Nicaragua. Agriculture and Food Security 4:2.

Njuki, J., Waithanji, E., Baglawa, N and Kariuki, J. 2013. Guidelines on Integrating gender in livestock projects and programs, Nairobi, Kenya: ILRI.

# ክፍለ ጊዜ 4፡ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ያሉ ዕውቀቶች፣ አመለካከቶችና ልምዶች

## የክፍለ ጊዜው መግለጫ

የዚህ ክፍለ ጊዜ ዓላማ የማህበረሰቡ አባላት ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች መንስኤዎች፣ ስለሚተላለፉባቸው መንገዶችና በሽታዎቹን እንዴት መከላከልና መቆጣጠር እንደሚቻል ያላቸውን ዕውቀት፣ አመለካከትና ልምድ ለማሰስ ነው። በመጀመሪያ ወንዶችና ሴቶች ስላላቸው ዕውቀት ይዳስሳል። ከዚያም ሴቶችና ወንዶች ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች ስላላቸው ዕውቀት፣ አመለካከት፣ ልምድ እንዲሁም ሴቶችና ወንዶች በፆታቸው መነሻነት የተሰጧቸው ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦችን የማዘጋጀት የመመገብ ሚናዎቻቸው ምክንያት ለበሽታዎቹ በምን ያህል ደረጃ እንደሚጋለጡ ይመረምራል።

## የክፍለ ጊዜው ዓላማዎች

በክፍለ ጊዜው መጨረሻ ተሳታፊዎቹ የሚከተለውን ማከናወን ይችላሉ።

- ሴቶች ስለ እንስሳት በሽታዎች ያላቸውን እውቀት አውቀው ለዕውቀታቸው ተገቢውን ዋጋ ይሰጣሉ።
- የትኞቹ በሽታዎች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ መሆናቸውን ይለያሉ።
- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን መንስኤ፣ የመተላለፊያ መንገዶችንና እንዴት መከላከልና መቆጣጠር እንደሚቻል ያላቸውን እውቀትና አመለካከት አስሰው ይረዳሉ።
- የታመሙ እንስሳትን አያያዝና ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦችን አመጋገብ በተመለከተ ያሉትን አመለካከቶች ያስሳሉ።
- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች በምርታማነትና በቤተሰብ ደህንነት ላይ የሚያስከትሉትን ውጤቶች በግልጽ ይናገራሉ።

- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችንና የእንስሳት ጤንነትን በተመለከተ የቤተሰቡ አባላት በውሳኔ ሰጭነትና በድርጊት አፈፃጸም ላይ በሚገባ እንዲሳተፉ የሚያደርጉ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።
- ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች ተጋላጭነትን ለመቀነስ ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦች አያያዝና አመጋገብን በተመለከተ ደህንነቱን የሚያስጠብቅ ባሕርይ ይከተላሉ።

## የክፍለ ጊዜው ይዘት

- ወንዶችና ሴቶች ስለ እንስሳት በሽታዎች ያላቸው ዕውቀት
- ሴቶች በእንስሳት በሽታዎች ላይ ያላቸውን ዕውቀት መቀበል
- ሴቶችና ወንዶች ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች ያላቸው ዕውቀትና አመለካከት
- ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦችን አያያዝና የአመጋገብ ልምድ
- በስርዓተ ፆታ የሥራ ክፍፍልና ውሳኔ በመስጠት አቅም ልዩነት የተነሳ ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች መጋለጥ
- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች የሚያስከትሏቸው ውጤቶች መከላከልና ቁጥጥር

## የመማር ዘዴና ቁሳቁሶች

- ምስሎች/ፖስተር
- ታሪክ ነገራ
- የማሰላሰል ውይይት
- ቪዲዮ ክሊፖች
- በራሪ ወረቀቶች

ሊፈጅ የሚችለው ጊዜ ፡ 4 ሰዓት

## የመማር እንቅስቃሴዎች

1. ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ይከልሱ።ለተሳታፊዎቻ ሞቅ ያለ አቀባበል ያድርጉላቸው። አዲስ ተሳታፊዎች ካሉ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ይጠይቋቸው። የአሁኑን ክፍለ ጊዜ ከበፊቱ ጋር ለማገናኘትና ክፍለ ጊዜው ጥሩ ፍሰትና ቀጣይነት እንዲኖረው እንዲሁም ተሳታፊዎቹ የአሁኑን ክፍለ ጊዜ ዓላማ በሚገባ እንዲረዱ በሚያስችል መልኩ ይከልሱ።

የሚከተሉትን የክለሳ ዓረፍተ ነገሮችን በፊሊፕ ቻርት ላይ በሚገባ ይፃፉ።

- ባለፈው ስብሰባ የተወያየንባቸው ______________________________ ናቸው።
- ባለፈው ስብሰባ ልንወስዳቸው የተስማማንባቸው እርምጃዎች ________________ ናቸው።
- እኔ ማምጣት የጀመርኳቸው ለውጦች ____________________________ ናቸው።

ጊዜውና ቦታው ከፈቀደ ተሳታፊዎቹ በክብ ቅርጽ እንዲቀመጡ ይጠይቋቸው። የክለሳ ዓረፍተ ነገሮችን በመሙላት በባለፈው ክፍለ ጊዜ ባገኟቸው ተሞክሮዎች (አንኳር ሀሳቦች፣ ግንዛቤዎች፣ የእርምጃ ነጥቦች) ላይ በግል እንዲያሰላስሉ ይጠይቋቸው። በመጀመሪያ ግን ይህን ተግባር እንዴት ሊያከናውኑ እንደሚችሉ በሚገባ ያስረዷቸው። ለተሳታፊዎቹ ትንሽ በግል የማሰላሰያ ጊዜ ከሰጧቸው በኋላ አጠቃላይ ስብሰበውን ይጀምሩ። ፈቃደኛ በሆነ ተሳታፊ ጀምረው በክቡ ውስጥ በመደዳ ሊቀጥሉ ይችላሉ። ተሳታፊዎቹ ተሞክሮአቸውን በአእምሮአቸው ውስጥ እንደመጣላቸው ወዲያውኑ ለሌሎች እንዲያካፍሉ ያበረታቷቸው። የተማሩ ባለመሆናቸው ምክንያት ተሳትፎ ለማያደርጉ ሰዎች የተለያዩ ምሳሌዎች በመስጠት በተማሯቸው ጉዳዮች ላይ እንዲያሰላስሉ ይርዷቸው። ሴቶች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው። ይህ ክፍለ ጊዜ ተሳታፊዎችን የሚያስደስት ነው እንጂ የሚያስፈራቸው እንዳይሆን ጥረት ያድርጉ።

ተሳታፊዎችን ለምላሾቻቸው አድናቆት በመስጠት ምላሾቹን ፊሊፕ ቻርት ላይ ይፃፉ። ምላሾቻቸውንም በመገምገም ከዕለቱ የማህበረሰብ ውይይት አጀንዳ ጋር ያገናኟቸው።

የውይይቱን መሰረታዊ ሕጎች በግልጽ በሚታይ ቦታ በማስቀመጥ ተሳታፊዎች እንዲያዳብሯቸው ያድርጉ።

የግብረ መልስ ቡድኖችን ይመድቡ። የቡድኖቹ አባላት ይህን ለማከናወን ፈቃደኝነታቸውን የገለጹ መሆን አለባቸው።

የዕለቱን አጀንዳ በመጠቀም የማህበረሰብ ውይይቱን ርዕሶች ያስተዋውቁ። የሚከተለውን በመናገር መጀመር ይችላሉ። "ዛሬ ሴቶችና ወንዶች ስለ እንስሳት በሽታዎች ያላቸውን ዕውቀትና ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች ስላላቸው አመለካከትና ልምዶች እንወያያለን። ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፍ በሽታ ስለተጎዳ ቤተሰብ ታሪክ እንሰማለን። በተጨማሪም ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች እንዴት እንደሚተላለፉ፣ የሚያስከትሏቸውን ውጤቶችና የመከላከያ ዘዴዎችን የሚያሳዩ ምስሎችን እናያለን። ከዚያም በኋላ በምስሎቹና ባየናቸውና በታሪኩ በሰማናቸው አመለካከቶችና ባሕሪዎች ላይ እናሰላስላለን፡ ፡ እርስዎም በግልዎ በእንስሳት በሽታዎችና ከእንስሳት ወደ ሰዎች የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ የራስዎን ተሞክሮና ከሌሎች የሰሟቸውን ታሪኮች ለተሳታፊዎች ያጋሩ።

2. የማህበረሰብ ውይይቱን ያከናውኑ

## ርዕስ 1፡ የእንስሳት በሽታዎችን በተመለከተ ወንዶችና ሴቶች ያላቸው ዕውቀት

በበሽታ የተጎዱ እንስሳት ምስል ለተሳታፊዎች በማሳየት ውይይቱን ይጀምሩ። ተሳታፊዎቹ የበሽታዎቹን አይነት እንዲለዩ ክሊኒካዊ ምልክቶቻቸውን ይጠይቋቸው።

ተሳታፊዎቹን በሴቶችና በወንዶች ቡድኖች ይከፋፈሏቸው።

የሴቶቹንና የወንዶቹን ቡድኖች የሚከተለውን እንዲያከናውኑ ይጠይቋቸው።

- በአካባቢው ቋንቋ የተለያዩ የበሽታ ዓይነቶችንና በሽታዎቹ የትኞቹን እንስሳት እንደሚያጠቁ ይለዩ።
- የበሽታዎቹን መንስኤዎችና በየትኛው ወቅት እንደሚከሰቱ ይግለጹ።
- የበሽታዎቹን ክሊኒካዊ ምልክቶች ይለዩ።
- በሽታዎቹ በከብት ምርታማነትና በቤተሰብ ደህንነት ላይ ያላቸውን ውጤቶች/ተፅዕኖ ይግለጹ።
- በሽታዎቹን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የምንጠቀምባቸውን ባሕላዊና ሳይንሳዊ ዘዴዎች ይለዩ፤፤

በአጠቃላይ ስብሰባ ውስጥ ትናንሽ ቡድኖች በማደራጀት ያገኟቸውን ውጤቶች እንዲጋሩ ያደርጉ። ወንዶችና ሴቶች ያገኟቸውን ውጤቶች በተናጠል በፊሊፕ ቻርቱ ላይ ይመዝግቡ። የወንዶችንና የሴቶችን ውጤቶች በማወዳደር ከዚህ የሚያገኙት ሌላ ውጤት መኖሩን ይመልከቱ።

የቡድኖቹ ውጤት ሴቶች ወንዶች ካላቸው ዕውቀት የሚስተካከል ወይንም የሚበልጥ መሆኑን ካሳየ ለዚህ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ፈልገው ያግኙ።

ሴቶችና ወንዶች የተገኘው ውጤት የጠበቁት መሆን አለመሆኑንና ለምን ይህን ውጤት እንደጠበቁ ወይንም እንዳልጠበቁ ይጠይቋቸው። ለዚህም የምርመራ ጥያቄዎችን ይጠቀሙ። ሴቶች ስለ እንስሳት በሽታዎች ያላቸው ዕውቀት አለመቀበል ምን ውጤት ወይንም አንድምታዎች ሊኖራቸው እንደሚችል ይወያዩ፡ ፡ ሴቶች በእንስሳት በሽታዎች ላይ ያላቸውን ዕውቀትና ውሳኔ ሰጭነት ለመቀበል ወይንም ለማሻሻል ወይንም ሁለቱንም ለማድረግ ተሳታፊዎች ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ በማሰብ ይናገሩ።

የምርመራ ጥያቄዎች

- የእንስሳት ጤና ጉዳይ የሴቶች ወይንስ የወንዶች ጉዳይ ነው? ለምን? ጉዳዩ የቤተሰብ ነው ወይስ የማህበረሰቡ? ለምን?
- ስለ እንስሳት በሽታዎች ከሴቶችና ከወንዶች ማናቸው የበለጠ ዕውቀት አላቸው? ለምን?
- በቤተሰብዎ ውስጥ የእንስሳት በሽታዎችን በተመለከተ ለሚሰጡ ስልጠናዎች፣ መረጃዎችና የማማከር አገልግሎቶች የበለጠ ተደራሽ የሚሆኑት ማን ናቸው? ሴቶች ወይስ ወንዶች? ለምን?
- ሴቶች ስለ እንስሳት በሽታዎች ያላቸው ዕውቀት የማይታወቀው /የማይታየው ለምንድነው?
- የሴቶች ስለ እንስሳት በሽታዎች ያላቸው ዕውቀት መታወቅ ወይም አለመታወቅ በሴቶች ስልጠና መረጃና የምክር አገልግሎት ማግኘትና አለማግኘት በውሳኔ መስጠት ችሎታ ላይ ምን አንድምታ አለው?
- ሴቶችን በእንስሳት ጤና አያያዝ ላይ ማሳተፍ ምን ጥቅም ይኖረዋል?

## ርዕስ 2፥ ከእንስሳት ወደ ሰውየሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ያለው ዕውቀትና አመለካከት

ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ተሳታፊዎች ምን እንደሚያስቡ ይወቁ። ተሳታፊዎች እንስሳት በሽታዎችን (በጥገኛ ነፍሳት? በባክቴሪያ በቫይረስና ፈንገሶች አማካይነት) ሊያስተላልፋ ይችላሉ ወይስ አይችሉም ብለው ያስባሉ?

በአጠቃላይ ስብሰባ ውስጥ እንዲህ ብለው ይጠይቁ "እንስሳት በሽታዎችን ወደ ሰው ሊያስተላልፉ ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? እንዴት? ወይንም ለምን?"

የተሳታፊዎችን ምላሾች በበለጠ ይመርምሩ። ተሳታፊዎች እንስሳት በሽታዎችን ሰው ማስተላለፍ አይችሉም ብለው የሚያስቡ ከሆኑ በእንስሳት አማካይነት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ስም በመጥቀስ ምሳሌዎችን ይስጧቸው። በእንደነዚህ ዓይነት በሽታዎች የተጎዱ ቤተሰቦችን ምስሎች በማሳየት እንዲወያዩባቸው ያድርጉ። ተሳታፊዎች በተመለከቷቸው ምስሎች ላይ በመመርኮዝ የራሳቸውን ተሞክሮዎችና ምልከታዎች በታሪክ መልክ እንዲያነሱ ያበረታቷቸው። የተለያዩ ጥያቄዎች በማንሳት ተሳታፊዎቹ የተናገሯቸውን ታሪኮችና ተሞክሮዎች በመመርመር ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ያሉ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች መሠረታዊ ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ገልጠው ለማሳየት ይሞክሩ። ነገሮችን ሳይጠይቁ ወይም ሳይመረምሩ እንዲሁ እንደተናገሩ አይቀበሉ። ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን ቃላት፣ አረፍተ ነገሮችና አባባሎች በጥሞና ያስተውሏቸው።

ከቀረቡት ተሞክሮዎችና ታሪኮች የተሟሯቸውን ነገሮች በማጠቃለል ይግለጻቸው።

ተሳታፊዎቹ እንስሳት ወደ ሰዎች በሽታዎችን ማስተላለፍ ይችላሉ ብለው የሚያስቡ ከሆነ በሽታዎቹንና የበሽታውን ምልክቶች እንዲለዩ ይጠይቋቸው። ከሴቶችና ከወንዶች የሚገኙትን ውጤቶች በሁለት የፊሊፕ ቻርት ወረቀቶች ላይ ለያይተው ይጻፉና ያነጻጽሩዋቸው።

ዋና ዋና ውጤቶችን ያጠቃሏቸው።

- እንስሳት ጎጂ የሆኑ በሽታ አምጭዎችን (pathogens) በመሸከምና ወደ ሰው በማስተላለፍ ህመምን ሊያስከትሉ ይችላሉ።
- ሁሉም የእንስሳት በሽታዎች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ አይደሉም።
- ብዙ ዓይነት ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ የእብድ ውሻ በሽታ፣ አባሰንጋ፣ ብሩሴሎሲስ የሚጠቀሱ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ የመተላለፊያ መንገዶችና ክሊኒካዊ ምልክቶች አሏቸው።

የምርመራ ጥያቄዎች

- በሽታዎች ከእንስሳት ወደ ሰዎች ሊተላለፉ ይችላሉ ብለው ያስባሉ? መልስዎ አዎ ከሆነ የትኞቹ በሽታዎች?
- ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች የበለጠ እውቀት ያለው ማነው? ሴቶች ወይስ ወንዶች? ለምን?
- በቤተሰብዎ ውስጥ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ለመረጃና ለምክር አገልግሎት ተደራሽነት/ቅርበት ያለው ማን ነው? ለምን?
- በቤተሰብዎ ውስጥ ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች የበለጠ ተጋላጭ የሆነው ማነው? ለምን?

## ርዕስ 3፥ የበሽታዎች ከእንስሳት ወደ ሰው መተላለፍ

ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ የተለመዱ በሽታዎችን በፖስተር አማካይነት ትምህርት ያቅርቡ (አባሰንጋና ኮክሲላ)

በመቀጠልም ተሳታፊዎች የትኛው የእንስሳት እርባታ ሥራ ሰዎችን ለየትኛው ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፍ በሽታ ሊያጋልጥ እንደሚችል በቡድን ሆነው ሊለዩ እንደሆነ ይንገሩአቸው።

ተሳታፊዎቹን በወንዶችና በሴቶች ቡድን ይከፋፍሏቸው። በእያንዳንዱ ቡድን "የተለመዱ ከእንስሰት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች"፣ "የከብት እርባታ ሥራዎች፣ "የእንስሳት ተዋጽኦዎችን መመገብ"፣ "ማን ምን ይሰራል?" የሚሉ ጽሑፎችን በወረቀት ላይ ጽፈው ያስቀምጡ። "የተለመዱ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች" በሚለው ጽሑፍ ስር የእብድ ውሻ በሽታ፣ አባ ሰንጋ፣ ቶክሶፕላስሞሲስ፣ ብሩሴሎሲስ ብለው ይፃፉ "የከብት እርባታ ሥራዎች" ከሚለው መለያ ስም ስር ደግሞ ማለብ፣ የከብቶች ቤት ማጽዳት፣ ማዋለድ፣ የታመሙ እንስሳት ማዋለድ፣ ማረድ፣ የሞቱ እንስሳት ማስወገድ፣ ከእንስሳት ጋር መጠለያ መጋራትና የመሳሰሉትን ወንዶችና ሴቶች የሚሰሯቸውንና ለተለያዩ በሽታዎች ሊያጋልጧቸው የሚችሉ ሥራዎችን የሚያሳዩ ምስሎችን ያኑሩ።

"ማን ምን ይሰራል?" የሚለው መለያ ስም ስር ደግሞ የተለያየ የከብት እርባታ ሥራን የሚያከናውኑና ለሚተላለፉ በሽታዎች የሚያጋልጧቸውን ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦችን የሚመገቡ ሴቶችና ወንዶች ምስሎች ያስቀምጡ።

በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ያሉትን ሴቶችና ወንዶች ፈቃደኞች የካርድ ምስሎቹን ከተፃፉት መለያ ስሞች እንዲያመሳስሉ ይጠይቋቸው።

ቡድኖቹ ለእያንዳንዱ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፍ በሽታ የትኛው የከብት እርባታ ሥራና የትኛውን የእንስሳት ተዋፅዖ መመገብ ለየትኛው በሽታ እንደሚያጋልጥና በስርዓተ ፆታ የሥራ ክፍፍል የተነሳ ማን የበለጠ ተጋላጭ ሊሆን እንደሚችል እንዲለዩ ያድርጉ። ፈቃደኛ የሆኑ ወንዶችና ሴቶች የከብት እርባታ ሥራዎችንና የእንስሳት ተዋፅዖዎችን መመገብን የሚያሳዩ ስዕሎች የተሳሉባቸውን ካርዶች ከበሽታው መተላለፍ ጋር ግንኙነት አላቸው ብለው የሚያስቡበት ቦታ ላይ እንዲያስቀምጡ ይጠይቋቸው። በየቤተሰቦቻቸው በተለምዶ ማን ያንን ሥራ እንደሚያከናውንና የእንስሳት ተዋጽዖዎችን እንደሚመገብ እንዲወያዩ ያድርጉ።

የሴቶቹንና የወንዶቹን ቡድኖች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

- የትኛው የከብት እርባታ ሥራ ለየትኛው ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፍ በሽታ ሊያጋልጥ እንደሚችል ለዩ።
- የትኛው የአያያዝ ልምድና ከየትኞቹ እንስሳት የሚገኝ ምግብ ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች ሊያጋልጥ እንደሚችል ለዩ።
- ከተለያዩ የከብት እርባታ ሥራና የእንስሳት ተዋፅዖን መመገብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ስም ይጥቀሱ።
- በስርዓተ ጾታ የሥራ ክፍፍሉና የእንስሳት ተዋጽዖአችን ከመመገብ ልምድ ጋር ተያይዞ ማን የበለጠ ለበሽታዎች ተጋላጭ ሊሆን እንደሚችል ይለዩ። የካርዶቹን አደራደር /አቀማመጥ በቀየሩ ቁጥር ትንሽ ቆም አድርገው ጥያቄዎችን ይጠይቁ። ምላሻቸውን በማዳመጥና በመመርመር ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች መንስዔ ያላቸውን ግንዛቤና አመለካከት ይረዱ።

ቡድኖቹ ያገኟቸውን ውጤቶች ለጠቅላላ ስብሰባው እንዲያጋሩ ይጠይቋቸው። የወንዶችና የሴቶች ቡድኖች ያገኟቸውን ውጤቶች መዝግበው ያነፃፅሯቸው። በተለያዩ ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች ላይ ተሳታፊዎች ውይይት ያድርጉ።

እንደ አባ ሰንጋና ኮሴሊያ ለመሳሰሉ ለተወሰኑ በሽታዎች ክሊኒካዊ ምልክቶችን ይግለጹ። እነዚህ ምልክቶች ትኩሳት፣ ተቅማጥ ጭንገፋና ሌሎች ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

የምርመራ ጥያቄዎች

- የትኞቹን ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ያውቋቸዋል?
- እነዚህ በሽታዎች ከእንስሳት ወደ ሰዎች የሚተላለፉት እንዴት ነው?
- ጥሬ ስጋን መብላትና ያልተፈላ ወተት መጠጣት ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች የሚያጋልጥ ይመስሎታል? መልስዎ "አዎን" ከሆነ ለየትኞቹ በሽታዎች? ለምን?
- ከእንስሳት ጋር መጠለያን መጋራት ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች እንዲተላለፉ ማድረግ የሚችል ይመስልዎታል? ለምን?
- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ አንዳንድ በሽታዎችን ምልክቶች ያውቃሉ? መልስዎ አዎን ከሆነ ምልክቶቹ ምንድናቸው?
- ምን ዓይነት የግብርና ሥራዎች እርስዎንና ቤተሰብዎን እርስዎ ለሚያውቋቸው ከእንስሳት ወደ ሰውለሚተላለፉ በሽታዎች ሊያጋልጡ ይችላሉ?
- ምን ዓይነት የከብት አያያዝና የእንስሳት ተዋፅዖዎች አመጋገብ እርስዎንና ቤተሰብዎን እርስዎ ለሚያውቋቸው ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች ሊያጋልጡ ይችላሉ?
- በቤተሰብዎ ውስጥ በሥርዓተ ፆታ የስራ ክፍፍሉ መሠረት በሚያከናውኗቸው የከብት እርባታ ሥራዎችና የእንስሳት ተዋፅኦ አመጋገብ ምክንያት ማን የበለጠ ለበሽታዎቹ ተጋላጭ ነው ብለው ያስባሉ?
- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች ጋር በተያያዘ የሰዎች መገለል ይፈጸማል? መልስዎ ‹አዎን› ከሆኑ ይህንኑ ይግለፁ። መገለሉ በምን መልኩ ይገለፃል ወይም ከምን ጋር የተያያዘ ነው? ስርዓተ ፆታዊ ነው?

# ርዕስ 4፡ ከእንስሳት ወደ ሰውየሚተላለፉ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር

ተሳታፊዎች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች በአንድ ቤተሰብ ምርታማነትና ደህንነት ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉ ውጤቶችን በአጠቃላይ ስብሰባው ላይ እንዲወያዩ ያድርጓቸው። በሽታዎቹን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እርምጃዎች ካልተወሰዱ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ተሳታፊዎቹን ጠይቋቸው።

ተሳታፊዎቹን በፆታቸው ከፋፍለው ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች ሊያጋልጧቸው የሚችሉትን የእንስሳት እርባታ ልምዶችን እንዲለዩ ይጠይቋቸው።

በአጠቃላይ ስብሰባ ላይ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች ተጋላጭነትን ለመከላከል ተሳታፊዎች ሊያደርጉ የሚችሉትን ይወያዩ።ከውይይቱ የሚጠበቀው ውጤት በአሁኑ ወቅት በመተግበር ላይ ያሉ ለበሽታው የሚያጋልጧቸውን ልምዶችንና ለወደፊት እንዲተገበሩ የሚፈለጉና ለበሽታው እንዳይጋለጡ የሚያደርጓቸውን ልምዶች ንፅፅር ነው።

ተሳታፊዎችን የሚከተለውን ጥያቄ ይጠይቋቸው። "እርስዎና የቤተሰብዎን አባላት ለበሽታ  አደጋ እንዳይጋለጡ ምን ማድረግ ይችላሉ" ?

ለተሳታፊዎቹ ሀሳብ ለመስጠትና ውይይቱን ለማሳለጥ በከብት እርባታና የእንስሳት ተዋፅዖዎችን አመጋገብ በተመለከተ መወሰድ ያለባቸውን ተገቢ እርምጃዎችን የሚያሳዩ ምስሎች ይጠቀሙ። ምስሎቹ መደበኛ የእንስሳት ህክምናን ቁጥጥርን፣ እጅ መታጠብን፣ ጓንትና ጭንብል መጠቀምን፣ የሞቱ እንስሳት አወጋገድን፣ ወተት ማፍላትንና ስጋን ማብሰልን የሚያሳዩ ሊሆኑ ይችላሉ።

የሚከተሉትን የምርመራ ጥያቄዎችን ይጠቀሙ።

- በዚህ ምስል ላይ ምን ታያላችሁ? እርስዎ ወይንም ቤተሰብዎ በምስሉ ላይ የምታዩትን ትተገብራላችሁ? ለምን?
- የእንስሳት በሽታ ሲከሰት ለእንስሳት ሕክምና ባለሙያዎች ሪፖርት ያደርጋሉ?
- እንስሳትን እንዲከተቡ ያደርጋሉ? ለምን?
- ላሞችን ካለቡ በኋላና የእንስሳትን መጠለያ ካጸዱ በኋላ እጅዎን ይታጠባሉ? ለምን?
- የታመሙ እንስሳትን በሚንከባከቡበት ጊዜ ጭንብል ጓንትና የመሳሰሉ የመከላከያ ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ? ለምን?
- በቤተሰብዎ ውስጥ ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፉ በሽታዎች የተጠቁ ሴቶች ከወንዶች እኩል የሕምና እርዳታ ያገኛሉ?
- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን የሚያገኙት ከየት ነው? ይህ የመረጃ ምንጭ በቂ፣ ተገቢነት ያለውና አስተማማኝ መረጃ የሚሰጥ ነው?

ከውይይቱ የተገኙትን ጭብጦች/ዋና ሐሳቦች በቁልፍ መልዕክቶች መልክ ያጠቃሏቸው። በስብሰባው በተነሱ ልምዶች፣ ታሪኮች፣ አይታዎችና እሴቶች ላይ ያሰላስሉ።

ተሳታፊዎች መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎችን በግልጽ ይንገሯቸው። እርምጃዎቹ የሚያስገኟቸውን ውጤቶችም በሚገባ ይንገሯቸው።

ቁልፍ መልዕክቶች

- ላሞችን ካለቡ በኋላና የከብቶችን ቤቶች ካፀዱ በኋላ እጅዎን በውሃና በሳሙና በሚገባ ይታጠቡ።
- የታመሙ እንስሳትን ከነኩ በኋላ እጅዎን በውሃና በሳሙና ይታጠቡ ወይንም አስቀድመው ጓንት ያድርጉ።
- ወተትን አፍልተው መጠጣት ለጤናዎ ጠቃሚ ነው።
- ጥሬ ስጋ መመገብ እርስዎንና የቤተሰብዎ አባላት በጥገኛ ነፍሳትና በባክቴሪያ እንድትጠቁ ያደርጋል።

ይህ ውይይት ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ጠቃሚ ጉዳዮችን የለየ ከመሆኑም በላይ ወደ ቤታችን ይዘን ሄደን የምንተገብራቸውን መልዕክቶች ያስተላለፈ ስለመሆኑ ለተሳታፊዎች ይግለጹ። ይህንን ካደረጉ በኋላ ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች ተጋላጭነትን ለማስወገድ በግልጽና በቡድን ሆነው ሀሳብ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው።

ተሳታፊዎቹ የተወሰኑ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመካለከልና ለመቆጣጠር ምን ዓይነት ርምጃዎች መውሰድ እንደሚገባቸው በአጠቃላይ ስብሰባ ሆነው እንዲለዩ ይጠይቋቸው።

- በከብት እርባታና ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦች በመመገብ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን አደጋ ለመከላከል ምን እርምጃ ይወስዳሉ?
- ያቀዷቸውን እርምጃዎች በሚተገብሩበት ጊዜ ምን ተግዳሮቶች ሊያጋጥሙኝ ይችላል ብለው ያስባሉ?
- ያቀዷቸውን እርምጃዎች በትክክል መተግበርዎን በምን ሊያውቁ ይችላሉ?

የድርጊት ነጥቦቹን በፊሊፕ ቻርቱ ላይ ይመዝግቡ። ሴቶችን፣ ወንዶችንና ሕፃናትን በተለየ መልኩ የሚመለከቱ እርምጃዎች ካሉ ለየት ባለ ቀለም አጉልተው ያሳዩ።

እርምጃዎቹ ለግለሰቦች፣ ለቤተሰቦችና ለቡድኖች ሊያስገኟቸው የሚችሉትን ውጤቶችና ጥቅሞች የሚያሳዩ ታሪኮች በመናገር ተሳታፊዎቹ የታቀዱትን እርምጃዎች እንዲተገብሩ አነሳሷቸው። ተሳታፊዎቹ መንስዔውን ለይተው ማወቃቸውንና በተነሱት የመፍትሔ ሀሳቦች ላይ መስማማታቸውን እንዲሁም ለመተግበር መነሳሳታቸውን ያረጋግጡ።

የመማርና የመተግበር ቡድኖችን በማደራጀት እስከሚቀጥለው የማህበረሰብ ውይይት ድረስ መማሩና ማሰላሰሉ እንዲቀጥልና በማኅበረሰቡ ደረጃ የሚደረገውን ትምህርትና ድርጊት መከታተል እንዲቻል ያደርጉ።

3. ቁልፍ በሆኑ ትምህርቶች ላይ ካሰላሰሉ በኋላ ክፍለ ጊዜውን ይጨርሱ። የሚከተለውን ሊናገሩ ይችላሉ። “እንግዲህ ወደ ውይይቱ ወይንም አሳታፊ ስልጠናው መጨረሻ ላይ ደርሰናል። አሁን ጠቅለል በማድረግ በዋና ዋና ሐሳቦቻችሁ፣ በግንዛቤዎቻችሁ እንዲሁም ባስደነቋችሁና አሃ ባሰኟችሁ ነገሮች ላይ እናሰላስል።

ተሳታፊዎች ለትንሽ ጊዜ እንዲያሰላስሉ ይጠይቋቸው።

በአጠቃላይ ስብሰባው ውስጥ ጥቂት ተሳታፊዎች የተገነዘቧቸውን ነገሮች በአእምሮአቸው እንደመጣ ወዲያውኑ ለሌሎች እንዲያጋሩ ይጠይቋቸው። ግንዛቤዎቹን በፊሊፕ ቻርት ላይ ይጻፉ።

ምላሾችን በመገምገም የጋራ የሆኑ ጭብጦች መኖራቸውን ያረጋግጡ። ሴቶችን፣ ወንዶችን ወይንም ሁለቱንም ፆታዎች በተለይ የሚመለከቱ ግንዛቤዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ይህን ለማስተዋል የተለየ ትኩረት ይስጡ።

ተሳታፊዎቹ በጥሩ ሁኔታ ትምህርቱን የተከታተሉ መሆኑን በመግለጽ ያመስግኗቸው። ማስታወሻ ያዦችንም በሚገባ ያመስግኑ። የሚቀጥለውን ስብሰባ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ እንዲሁም የዕለቱን አጀንዳ ከገለጹ በኋላ ተሳታፊዎች በሙሉ በተባለው ቀንና ሰዓት በቦታው እንደሚገኙ ያሎትን ተስፋ ይገልጹ።

ለአመቻቾች ተጨማሪ መረጃዎች

ሴቶች በከብት እርባታ ውስጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። ሆኖም የማህበረሰቡ አባላት በተለይ ወንዶች ሴቶች ስለ እንስሳት በሽታዎች ብዙም አያውቁም የሚል ግንዛቤ አላቸው። እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ ሰው በአንድ ሥራ ያለው ዕውቀት የሚወሰነው በዚያ ሥራ ላይ ባለው ተሳትፎ መጠን ላይ ነው። ከዚህ አንፃር ሴቶች በሚሳተፉባቸው የከብት እርባታ ሥራዎች ላይ ከሌሎች የበለጠ ሊያውቁ  ይችላሉ። በተመሳሳይ ምክንያት ሴቶች የሚንከባከቧቸውን እንስሳት በበሽታ ሲጠቁ አስቀድመው ሊያውቁና የበሽታውን የመተላለፊያ መንገዶችንና የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች የተሻለ ሊረዱ ይችላሉ።

ሆኖም ስለ ሴቶች ባለው ማህበራዊ ሥነ ምግባር የተነሳ የሴቶች ዕውቀት በቤተሰብ ደረጃ ዕውቅና አይሰጠውም። ከማኅበረሰቡ ውጭ የሚመጡ ሰዎችም የሴቶችን ዕውቀት ለልማት ሥራ አይጠቀሙበትም። ይህ አድራጎት ሴቶች የራሳቸውን እርምጃ እንዳይወስዱና መረጃዎችንና የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች እንዳይሰጡ ወይንም እንዳያገኙ በማገድ የስርኣተ ጾታ መበላለጥ ሰፍኖ እንዲቆይ ከማድረጉም በላይ የከብት እርባታ ሥራና የቤተሰብ ደህንነት እንዲስተጓጎል ያደርጋል፡ ፡ ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ወንዶችና የልማት ሠራተኞች በበሽታ ክትትልና የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ሴቶችን እንዲያሳትፉ ማድረግ ይገባል።

ከታመሙ እንስሳት ወደ ሰዎች ሊተላለፉ የሚችሉ ብዙ በሽታዎች አሉ። ምንም እንኳን ወንዶችና ሴቶች አንዳንዶቹን በሽታዎች የሚያውቋቸው ቢሆንም እነዚህ በሽታዎች ምን እንደሆኑና እንዴት ወደ ሰው መተላለፍ እንደሚችሉ እንዲሁም የቁጥጥር ዘዴዎቹ ምን እንደሆኑ እምብዛም አያውቁም።

የእንስሳት ምንጭ ምግቦችን አጠቃቀም የተመለከቱ ባሕላዊ ልምዶችና የእንስሳት በሽታዎችን በተመለከተ ያሉ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች ቤተሰብን ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች አደጋ ያጋልጣሉ። ሥጋን ማብሰልና ወተትን ማፍላት በምግቡ ውስጥ ያሉትን አስፈላጊ ንጥረ ነገሮችን ያጠፋል በሚል እምነት ሰዎች ያልተፈላ ወተትና ጥሬ ስጋ ይመገባሉ። ብዙ ሴቶችና ወንዶች እንስሳት በሽታን ወደ ሰው አያስተላልፉም ብለው ይገምታሉ።

በሙከራ ማህበረሰቦች ውስጥ የተደረጉ ጥናቶችና ምርምሮች እንደሚያሳዩት ሴቶችና ወንዶች ጥሬ ሥጋ መብላትና ያልተፈላ ወተት መጠጣት ምንም ችግር የለውም ብለው ያምናሉ። በተጨማሪም የተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ለምሳሌ ጎልማሶችን/አዋቂዎችን ከእንስሳት የሚመጡ በሽታዎች አይዟቸውም ብለው ይገምታሉ። አንዳንድ የእንስሳት ምንጭ ምግቦችን ከመመገብ ጋር የተገናኙ ልምዶች ለአንዳንድ የማህበረሰቡ አባላት በተለይም ለአዋቂዎችና ለህጻናት ተገቢና ተቀባይነት ያላቸው ናቸው ብለው ይገምታሉ።

ጥናቶቹ እንደሚያሳዩት ሴቶች ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች ይበልጥ ተጋላጭ ከመሆናቸውም በላይ በበሽታዎቹ ሲጠቁ ከወንድ የቤተሰቡ አባላት እኩል እንክብካቤ አያገኙም (Kristijansonetal 2010) ። ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች ያሉ ግንዛቤዎች አናሳ ከመሆናቸውም በላይ በሽታዎቹን ከመከላከልና የታመሙ ግለሰቦችን ከመንከባከብ አንፃር በርካታ ማህበራዊና መዋቅራዊ እንቅፋቶች አሉ።

## ተጨማሪ ንባብ

Weland, B., Alemu, B., Desta, H., Kinati, W. and Mulema, A.A. 2016. Participatory epidemiology and gender analysis to address small ruminant disease constraints in Livestock and Fish and Africa RISING project sites in Ethiopia. Nairobi, Kenya: ILRI.

Mulema, A.A., Kinati, W., Desta, H., Alemu, B. and Wieland, B. 2017. Tapping the knowledge of women in small ruminant disease surveillance and management. SmaRT Ethiopia Intervention factsheet 23. Addis Ababa: ICARDA.

# ክፍል 5፡ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ከመከላከል ጋር ተያይዞ ያሉ ተቋማዊና ማህበራዊ ጉዳዮች

## የክፍለ ጊዜው መግለጫ

የዚህ ክፍለ ጊዜ አላማ ወንዶችና ሴቶች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን አደጋ ለማስወገድ የሚረዱ የመረጃና የምክር አገልግሎቶችን ማግኘት/አለማግኘት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ተቋማዊና መዋቅራዊ ጉዳዮችን መመርመር ነው።

የማህበረሰቡ እሴቶችና ደንቦች የሰዎችን የግንኙነት ሁኔታ ይገልፃሉ።ማን ከማን ጋር ግንኙነት እንደሚኖረውና እንደሚግባባ፣ ማን ምን ዓይነት መረጃ እንደሚያገኝ፣ ለምን ነገሮች ተደራሽነት እንደሚኖረውና ማን ምን እንደሚወስን ወዘተ በመወሰን ላይ እሴቶቹና ደንቦቹ ተፅእኖ ያደርጋሉ። ስለሆነም በሽታዎቹን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንፃር ዘላቂ ውጤት የሚገኘው ሴቶችንና ወንዶች በማህበረሰብ ቡድኖች በማሳተፍ መረጃዎችን እንዲያገኙ፣ ሐሳቦቻቸውን እንዲገልጹ እንዲሁም ምርጫ እንዲኖራቸው በሚያስችሉ ማህበራዊና መዋቅራዊ ጉዳዮች ላይ በመስራት ነው።

## የክፍለ ጊዜው ዓላማ

በማህበረሰብ ውይይቱ መጨረሻ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን የማከናወን ብቃት ይኖራቸዋል።

- የሴቶችን ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወር እንዲሁም መረጃንና አገልግሎትን በማግኘት ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ባሕላዊና መዋቅራዊ ጉዳዮች ይለያሉ።
- ሴቶች በማህበረሰቡና ማህበራዊ ቡድኖች (ለምሳሌ እንደ የእርባታ የሕብረት ሥራ ማኅበራት) ውስጥ ያላቸውን ቦታ ይገልጻሉ።
- ሴቶች በቤተሰብና በማሕበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ግንኙነቶች የሚወስኑ/የሚገልጹ እሴቶችንና ደንቦችን ይገመግማሉ።
- በቤተሰብና በማህበረሰብ ውስጥ የተግባቦትና የመረጃ ልውውጥ አካሄድን በመገምገም የሴቶችን ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን የማስወገድ አቅምና በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ሥራዎች ባላቸው ተሳትፎ ላይ የሚያስከትለውን ውጤት ይገልጻሉ።

## የክፍለ ጊዜው ይዘት

- በማህበረሰብ ቡድኖችና በሕብረት ሥራ ማኅበራት የሴቶች ተሳትፎ
- የሴቶችን ግንኙነቶችና በቤተሰብና በማኅበረሰቡ ውስጥ ለመረጃ ያላቸውን ተደራሽነት የሚወስኑ ህጎችና እሴቶች

የሴቶች ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር መገደብና ከሌሎች የመዛመድ አቅም

- ገቢዎችና ሀብቶች በሴቶች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ የበሽታ አደጋዎች የመከላከል አቅም ላይ ያሏቸው ተፅዕኖዎች

## የመማሪያ ዘዴዎችና ቁሳቁሶች

- ፖስተሮች
- ታሪክ ነገራ

- የማሰለስ ጥያቄዎች
- ፋክት ሺቶች

ሊፈጅ የሚችለው ጊዜ፥ 3 ሰዓት

## የመማር እንቅስቃሴዎች

1. ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ይከልሱ። ተሳታፊዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ ይበሏቸው። ክፍለ ጊዜውን ከበፊቱ ክፍለ ጊዜ ጋር ለማገናኘትና ክፍለ ጊዜው ጥሩ ፍሰትና ቀጣይነት እንዲኖው እንዲሁም ተሳታፊዎቹ የአሁኑን ክፍለ ጊዜ ዓላማ በሚገባ እንዲረዱ በሚያስችል መልኩ ይከልሱ።

የሚከተሉትን የክለሣ ዓረፍተ ነገሮች በፊሊፕ ቻርት ላይ በሚገባ ይጻፉ።

- ባለፈው ስብሰባ የተወያየንባቸው ዋና ዋና ነጥቦች ____________________ ነበሩ።
- ከባለፈው ስብሰባ በአዲስ መልኩ የተረዳኋቸውና ያገኘኋቸው ግንዛቤዎች ____________________ ናቸው።
- በአዲስ መልክ የተረዳኋቸውና የተገነዘብኳቸው ነገሮች ለሕይወቴ ያላቸው ጠቀሜታና አንድምታ ____________________ ናቸው።

ጊዜውና ቦታው ከፈቀደ ተሳታፊዎቹ በክብ ቅርፅ እንዲቀመጡ ይጠይቋቸው። የክለሳ አረፍተ ነገሮችን በመሙላት ባለፈው ጊዜ ባገኘናቸው ተሞክሮዎች (አንኳር ሃሳቦች፣ ግንዛቤዎችና የእርምጃ ነጥቦች) ላይ በግል እንዲያሰላስሉ ይጠይቋቸው።

ለተሳታፊዎቹ ትንሽ በግል የማሰላሰያ ጊዜ ከሰጧቸው በኋላ አጠቃላይ ስብሰባውን ይጀምሩ። ፈቃደኛ በሆነ ተሳታፊ ጀምረው በክቡ ውስጥ በመደዳ ሊቀጥሉ ይችላሉ። ተሳታፊዎቹ ብዙም ሳይጨነቁ ተሞክሯቸውን በአእምሮአቸው ውስጥ እንዳመጣላቸው ወዲያውኑ ለሌሎች እንዲያካፍሉ ያበረታቷቸው። የተማሩ ባለመሆናቸው ምክንያት ተሳትፎ ለማያደርጉ ሰዎች የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት በተማሯቸው ጉዳዮች ላይ እንዲያሰላስሉ ይርዷቸው። ሴቶች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፤፤ ተሳታፊዎቹ ለሚሰጡት ምላሾች አድናቆትን በመስጠት በፊሊፕ ቻርቱ ላይ ይመዝግቡ። ምላሾቹን በመገምገም ከዕለቱ የማህበረሰብ ውይይት አጀንዳ ጋር ያያይዟቸው። የውይይቱን መሠረታዊ ህጎች በቀላሉ በሚታይ ቦታ ላይ በማስቀመጥ ተሳታፊዎቹ ሕጎቹን እንዲያከብሩ ያስታውሷቸው።

2. የማህበረሰብ ርዕሶቹን የዕለቱን አጀንዳ በመጠቀም ያስተዋውቁ። የሚከተለውን በመናገር ሊጀምሩ ይችላል። “ዛሬ በማህበረሳባችን ውስጥ ስላሉ ሕጎች፣ እሴቶችና ግንኙነቶችና እነዚህም በበኩላቸው ሴቶችና ወንዶች ከከብት እርባታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች በማግኘትና ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚኖራቸው ችሎታ ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ እንነጋገራለን። በመጀመሪያ አንድ ታሪክ እንሰማለን። በመቀጠልም በታሪኩ ላይ በሰማናቸው ግንዛቤዎች፤ አመለካከቶችና ባህሪዎች ላይ እናሰላስላለን። እናንተም የማሕበረሰቡ እሴቶችና ህጎች የወንዶችና የሴቶችን መስተጋብር በቤተሰቡ፣ በማህበረሰብ ወይንም በገበያ ምን መምሰል እንዳለበት እንዴት እንደሚወስኑ ያላችሁን የሕይወት ተሞክሮና ምልከታችሁን ለሌሎች ታካፍላላችሁ። እነዚህ የማህበረሰቡ ሕጎችና መመሪያዎች እንዴትና በምን ሁኔታ ሴቶችና ወንዶች ለህብቶችና ዕድሎች ባላቸው ተደራሽነት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያስከትሉ ታሰላስላላችሁ።”

3. የማህበረሰብ ውይይቱን ይጀምሩ፥ ውይይቱን ታሪክ በመናገር ይጀምሩ። ተሳታፊዎቹ በሰሚቸው ታሪክ ላይ በማሰላሰል የራሳቸውን ተሞክሮዎችና ታሪኮች እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው። በሰሟቸው ታሪኮችና ተሞክሮዎች ላይ ተጨማሪ የምርመራ ጥያቄዎች ይጠይቁ። ታሪኮቹንና ተሞክሮዎችን ጠቅለል በማድረግ ዋና ዋና ትምህርቶችን ያስቀምጡ።

## ርዕስ 1፥ ምን ዓይነት ተቋሞችና መዋቅሮች ሴቶች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ የበሽታ አደጋዎችን ለመቀነስ የሚረዷቸውን መረጃዎችና ምክሮችን ማግኘት /ያለማግኘት ላይ ተፅእኖ ይኖራቸዋል።

ለሚከተሉት ከአካባቢው ጋር የተገናኙ ምሳሌዎች ይስጡና ይመርምሩ።

- የስብሰባ ቦታ ጊዜና ሰኣት - ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር፣ የቤት ውስጥ ሥራ
- የተግባቦቱ ዘዴ - -ለሴቶች ተስማሚ የሆኑ ኤክስቴንሽንና ሚዲያ
- አካባቢያዊ ማድረግ/መረጃን ለራስ ምቹ በሆነ መንገድ ማዘጋጀት

- ጥንዶችንና የቤተሰቡን አባላት/ማሳተፍ
- በማህበረሰቡ ተቀባይነት ባላቸው ቡድኖች ውስጥ በአባልነት መሳተፍ
- የከብት ገበያዎች

### የምርመራ ጥያቄዎች

- ምን ዓይነት የከብት ገበያዎቹ አሉ? የት ቦታ ላይ ይገኛሉ?
- ሴቶችና ወንዶች ለገበያው እኩል ተደራሽነት አላቸውን?
- ወደ የትኛው ገበያ መሄድ እንዳለባቸው የሚወሰነው እንዴት ነው?
- ሴቶች ነፃ ሆነው ከብቶችን በገበያ ውስጥ መሸጥ ይችላሉ? ምን ዓይነት የከብት ዝርያዎችን?
- ከሴቶች ከብቶቹን የሚገዛው ማነው? ምን ዓይነት ከብቶችን?
- የገበያዎቹ መሠረተ ልማቶች/መገልገያዎች ለሴቶች የሚስማሙ ናቸው? የነዚህ አንደምታዎች ምንድናቸው?
- ሴቶች እንስሳትን ከገበያ ውስጥ ከመግዛታቸው በፊት የታመሙና ያልታመሙ መሆናቸውን ለይተው ያውቃሉ?

## ርዕስ 2፡ የ ግንኙነት ሁኔታን ማለትም ማን ከማን ጋር መገናኘትና መግባባት እንዳለበት የሚገልጹና ተፅዕኖ የሚያሳድሩ የትኞቹ የማህበረሰቡ እሴቶችና ደንቦች ናቸው? ማን ምን ዐይነት መረጃና አገልግሎት ሊያገኝ ይችላል? ማን ምን ይወስናል?

ስለ ሴቶች ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስና ለመረጃና ስልጠና ያላቸው ተደራሽነት

- በዚህ ማህበረሰብ ያሉ ሴቶች የሚሄዱባቸው ቦታዎች የትኞቹ ናቸው? (ለምሳሌ፡ ወደ ገበያዎች፣ የማሰልጠኛ ማዕከሎች፡ቤተክርስቲያኖችና ወደ መሳሰሉት ቦታዎች)
- ሴቶች ወደፈለጉበት ቦታ በፈለጉት ጊዜ የመሄድ ነፃነት አላቸው?
- ሴቶች ለመረጃ ቅርበት እንዲኖራቸው ወንዶች ምን ያህል ይረዷቸዋል?
- የኤክስቴንሽን አማካሪዎች ወደ ቤትዎ ሲመጡ የሚገናኙት ከማን ጋር ነው? ሴቶችንና ሌሎች የቤተሰቡን አባላት ያሳትፋሉ? አማካሪዎች ወደ ቤትዎ ሲመጡ እርስዎ ባለቤትዎ እንዲሳተፉ ያደርጋሉ?

በአባወራ የሚመራ ቤተሰብ ውስጥ ሴቶችን ተጠ ለማድረግ ያሉ ባህላዊ ችግሮች

- ባሎቻቸው በሌሉበት ሁኔታ ወንድ የኤክስቴንሽን አማካሪዎች ሴቶችን አግኝተው ማነጋገር ይችላሉ? ሴቶች የኤክስቴንሽን አገልግሎት አማካሪዎችስ?
- በአባወራ በሚመሩ ቤተሰቦች ሴቶች ስለ ከብት እርባታ ጉዳዮችና ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎችና እንዴት የተሻለ የኤክስቴንሽን ምክሮችን ሊያገኙ ይችላሉ?

ስለ ከብቶችና ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች በቤተሰብ ውስጥ መረጃን መለዋወጥ

- ከስብሰባዎችና ከስልጠናዎች ያገኟቸው መረጃዎች ወንዶች ለቤተሰብ አባላት በተለይም ለሚስቶቻቸው ያጋራሉ?
- ምን ዓይነት መረጃዎችን ለማን ያጋራሉ?
- ብዙ ጊዜ ሴቶች ለየትኞቹ መረጃዎች ቅርብ ናቸው? መረጃዎችን ከቤተሰቡ አባላት ማጋራት ያለው ጥቅም ምንድነው?

# ርዕስ 3፡ ምን ዓይነት ተግባቦትና የመረጃ ልውውጥ ለሴቶች ጠቃሚ ነው?

- ምን ዓይነት ቡድኖች ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው?
- ወንዶች የየትኞቹ ዓይነት ቡድኖች አባላት ናቸው?
- ሴቶች የየትኞቹ ዓይነት ቡድኖች አባላት ናቸው?
- በነዚህ ቡድኖች ውስጥ ሰዎች ምን ዓይነት መረጃዎችን ይለዋወጣሉ? መረጃዎቹን የሚያጋራው ማነው?
- አንድ ሰው የአንድ ቡድን አባል የሚሆነው እንዴት ነው? መስፈርቶቹ ወንዶችንና ሴቶችን እኩል ይነካሉ? እንዴት?
- ሴቶች በማህበረሰብ ውስጥ በሚገኙ የሪቢ ቡድኖች ውስጥ አባል ይሆናሉ? በቡድኖቹ ውስጥ የአመራር ሚና ይጫወታሉ?
- ሴቶችና ወንዶች የአንድ ቡድን አባላት በመሆናቸው ምን ልናገኝ ወይንም ልናጣ እንችላለን?

ከውይይቱ የተገኙትን ዋና ዋና ሐሳቦች (ጭብጦች) ያጠቃሏቸው።

የምርመራ ጥያቄዎች

- በማህበረሰብዎ ውስጥ ሴቶች የሕብረት ሥራ ማኅበራት አባል ናቸው? ካልሆኑ ለምን?
- በማህበረሰብዎ ውስጥ የትኞቹ ቡድኖች ወይንም የሕብረት ሥራ ማኅበራት በጣም አስፈላጊ ናቸው? ለምን? ብዙ ጊዜ የነዚህ ቡድኖች ወይንም ማህበራት አባል የሚሆነው ማነው?
- ሴቶች በነዚህ ቡድኖችና ማሕበራት ውስጥ የአመራር ቦታ ይይዛሉ? የአመራር ቦታ የማይዙ ከሆነ ለምን?
- በቤተሰብ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲሁም በገበያና በመሳሰሉ ሕዝባዊ ቦታዎች ወንዶችና ሴቶች ያላቸውን መስተጋብር የሚገልጹ /የሚወስኑ የትኞቹ ደንቦች ናቸው?
- በማኅበረሰብዎ ውስጥ ሴቶች ምን ዓይነት አውታረ መረቦች (networks)፣ ግንኙነቶች ወይንም ፎረሞች አሏቸው? እነዚህ ወንዶች ካሏቸው አውታረ መረቦች በምን ይለያሉ?
- ምን ዓይነት ግንኙነቶች ወይንም አውታረ መረቦች ወንዶችና ሴቶች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን የመከላከልና የመቆጣጠር አቅማቸውን የማጎልበት ወይንም የመገደብ ሚና ይኖራቸዋል?
- የሴቶች ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወርና ከሌሎች ጋር ግንኙነት የመፍጠር አቅም ማነስ ምን ውጤት ይኖረዋል?
- ሴቶች ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፍ በሽታ ሲጠቁ ሕክምና /መድሃኒት ያገኛሉ?
- ሴቶችና ወንዶች ከእንስሳት በሽታዎችና ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች ላይ የሚሰጡ መረጃዎችንና ምክሮችን እኩል ያገኛሉ?
- በማኅበረሰብዎ ሴቶች ከቦታ ወደ ቦታ በነጻነት ተንቀሳቅሰው እንደ ጤና ጥበቃ፣ የከብቶች ሕክምናና ስልጠና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ?

4. በተገኙት ቁልፍ ትምህርቶች ላይ በማሰላሰል ክፍለ ጊዜውን ይጨርሱ። የሚከተለውን ሊናገሩ ይችላሉ። እንግዲህ ወደ ውይይታችን ማብቂያ ደርሰናል። አሁን ጠቅለል አድርገን በዋና ዋና ሐሳቦች፣ ግንዛቤዎችና ባስደነቁን ነገሮች ላይ እናሰላስል።"

የማሰላሰያ ጥያቄዎቹን በፊሊፕ ቻርት ላይ ይጻፉ

- ከውይይቱ እርስዎ በግልዎ ያገኙት ነገር ምንድነው?
- የተማሩትን በሕይወትዎ እንዴት ሊተገብሩት አስበዋል?

ተሳታፊዎች በግላቸው ለጥቂት ጊዜ እንዲያሰላስሉ ይጠይቋቸው። በአጠቃላይ ስብሰባ ውስጥ ጥቂት ተሳታፊዎችን ከውይይቱ ጎልተው በአዕምሯቸው የተቀረፁትን ነገሮች እንዲያጋሩ ይጠይቋቸው። እነዚህን ነገሮች በፊሊፕ ቻርት ላይ ይመዝግቧቸው። ከተሳታፊዎቹ የሚመጡትን ምላሾች በመገምገም የጋራ የሆኑ ጭብጦችን ይለዩ። ሴቶችና ወንዶች ካቀረቧቸው ጭብጦች መካከል ልዩነት ሊኖር ስለሚችል የተለየ ትኩረት ያድርጉ። ጭብጦችን በፊሊፕ ቻርት ይመዝግቧቸው።

አሁን የሚቀጥለው ሥራ እስከሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ በግልና በጋራ መማሩና ማሰላሰሉ እንዲቀጥል ለማስቻል እርምጃዎችን መለየት መሆኑን ለተሳታፊዎቹ ይንገሯቸው።

ተሳታፊዎቹ እጅግ በጥሩ ሁኔ ትምህርቱን የተከታተሉት መሆኑን ገልፀው ምስጋና ያቅርቡላቸው። ማስታወሻ ያዢችንም በሚገባ ያመስግኗቸው። የሚቀጥለውን ስብሰባ ቀን፣ ሰዓትና አጠቃላይ አጀንዳ ካስታወቁ በኋላ ሁሉም ተሳታፊዎች በሰዓቱ በቦታው እንደሚገኙ ያሎትን ተስፋ ይግለፁ።

## ለአመቻቾች ተጨማሪ መረጃዎች

ወንዶችና ሴቶች (ወንዶች ልጆችና ልጃገረዶች) ፍላጎታቸውና የኑሮ ዘይቤያቸውን የሚከተሉት በተቋማዊ መዋቅሮች አውድ ውስጥ ነው። እነዚህም ባሕርይን፣ ሐሳብ መግለፅን፣ የሐብት ቁጥጥርንና ክፍፍልን የሚወስኑ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ደንቦችና አሠራሮች ናቸው።

የስርዓተ ጾታ ሕጎች የሥራ ክፍፍልን በመወሰን ሴቶችንና ወንዶችን በተለያየ ደረጃ ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች ያጋልጧቸዋል። በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ መዋቅራዊ አደረጃጀቶች ሴቶችና ወንዶች የከብቶቻቸውን ጤንነት እንዲከታተሉና በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ላይ እንዲሳተፉ የሚያስችሏቸውን መረጃዎችና አገልግሎቶች የማግኘት እድላቸውን ሊያሰፉ ወይንም ሊገድቡ ይችላሉ። እነዚህ ሕጎችና አደረጃጀቶች ማን ምን ዓይነት ሐብቶችን ለማግኘትና ከብቶችን ከበሽታ ለመጠበቅ እንደሚችል ይወስናሉ። ይህ ደግሞ የከብቶችን ምርታማነት በመወሰን በቤተሰብ ደህንነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ሴቶችና ወንዶች ማሕበረሰቡን በሚመለከቱ ውሳኔዎች ላይ እንዳይሳተፉ የሚያግዱ ተቋማትና መዋቅሮች እስካልተለወጡ ድረስ የእንስሳት ጤና ሥራዎች የተጠበቀውን ውጤት ሊያስገኙ አይችሉም።

የሴቶች በአመራርና በውሳኔ ሰጭነት እንዲሁም በጋራ በሚወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ መሳተፍ ገዳቢ የሆኑ ተቋማትና መዋቅሮችን ሊፈታተናቸው ይችላል። ይህ ደግሞ በበኩሉ ወደ ሀብትን እንደገና የመከፋፈል፣ ውሳኔ የመስጠት አቅምን የመፍጠር፣ ለሴቶች ሚናና መብቶች ተገቢውን ዕውቅና ወደ መስጠት ሊያመራና የሽግግር ለውጥ ሊቀሰቅስ ይችላል።

በሥራ ክፍፍል ለውጥ እንዲሁም በሐብት ቁጥጥርና በተቋማዊ መዋቅሮች መካከል ጠንካራ ትስስር አለ። ይህ ትስስር ማሕበረሰቦች የስርዓተ ፆታ ፍትሐዊነት በሰፈነበት መንገድ የራሳቸውንና የእንስሳቶቻቸውን ጤና እንዲጠብቁ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ይህ በበኩሉ ደግሞ ሴቶች ድምጻቸውን እንዲያሰሙና በመረጃ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲወስኑ በማድረግ ሴቶችን የማብቂያ አንዱና መሠረታዊ መሸጋገሪያ መንገድ ነው።

# ክፍለ ጊዜ 6፡ ማሰላሰል፣ ግምገማና መዝጊያ

## የክፍለ ጊዜው መግለጫ

የመዝጊያው ክፍለ ጊዜ በማሕበረሰብ ውይይቱ የተሳታፊዎችን የመማር ሂደትና ልምዶች ለመገምገምና ለማሰላሰል የሚያልም ነው። ክፍለ ጊዜው በማሕበረሰብ ውይይቱ የተገኙ ልምዶችን አሳታፊ በሆነ መንገድ በመገምገም ተሳታፊዎቹ ያመጧቸውን ለውጦችን ለይቶ ይመዘገባል። ተሳታፊዎቹን የተለያዩ በጥልቀት ለማሰብ የሚረዱ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የማህበረሰብ ውይይቶቹ የሚያስገኟቸውን ጥቅሞችና ተሳታፊዎች እራሳቸው በግልም ሆነ በቡድን ያመጧቸውን ለውጦች ለይተው እንዲሰንዱ ይበረታታሉ።

## የክፍለ ጊዜው ዓላማዎች

በማህበረሰብ ውይይቱ መጨረሻ ተሳታፊዎቹ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይችላሉ።

- የማህበረሰቡ ውይይቱን ልምዶች ይገመግማሉ፣ ያሰላስላሉ።
- በግልና በጋራ የተገኙ ጥቅሞችንና ለውጦችን ይለያሉ።
- በማህበረሰብ ውይይቱ አደረጃጀት የማመቻቸት ሂደት ላይ አስተያየትና ግብረ መልስ ይሰጣሉ።
- ከመማርና ከትግበራ ቡድኖች የተገኙ ልምዶችንና ጥቅሞችን ለሌሎች ያጋራሉ።
- በተሳትፎና በዕቅድ ትግበራ ወቅት ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶች ለሌሎች ያጋራሉ።

## የክፍለ ጊዜው ይዘት

- የማህበረሰብ ውይይት ልምዶች፡ ማደራጀት ማመቻቸት/ማሳለጥ፣ የውይይቶቹ ጊዜና ቦታ፣ የመማርና የመተግበር ቡድኖች፣ ግላዊና የጋራ ጥቅሞች

- የስርዓተ ጾታ ግንኙነቶችንና የሴቶችን የእንስሳት ባለቤትነት በተመለከተ የተደረጉ የግንዛቤና የተግባር ለውጦች
- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን መከላከልንና መቆጣጠርን በተመለከተ የመጡ የዕውቀት የአመለካከትና የድርጊት ለውጦች
- በማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜዎች ምክንያት የመጡ ለውጦችን ከማስቀጠል አንፃር ያሉ ዕድሎችና ተግዳሮቶች
- የማህበረሰብ ውይይቱ ያስከተላቸው የማኅበረሰብ ብቃቶች

## የመማር ዘዴዎችና ቁሳቁሶች

- የዋና ዋና ነጥቦችና በሰነድ የተያዙ እርምጃዎች ግምገማ
- በግልና በቡድን ማሰላሰል
- የአጠቃላይ ስብሰባ ውይይቶች
- ማስፋትና ዘላቂነት

ሊወስድ የሚችለው ጊዜ፥ 2 ሰዓት

## የመማር እንቅስቃሴዎች

1. ፖስተሮችን፣ ምስሎችን፣ ፊሊፕ ቻርቶችን፣ የቪዲዮ ክሊፖችንና የመሳሰሉትን የማኅበረሰብ ውይይት ውጤቶችን ያሳዩ።
2. ተሳታፊዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ይቀበሏቸው። ጊዜያቸውን ሰጥተው በግምገማና በዕውቀት ማጋራት ክፍለ ጊዜ በመገኘታቸው ያመስግኗቸው።
3. የዕለቱን አጀንዳ በመጠቀም ክፍለ ጊዜውን ያስተዋውቁ።

ክፍለ ጊዜውን በሚያስተዋውቁበት ጊዜ የሚከተለውን በመናገር ሊጀምሩ ይችላሉ “ዛሬ የማኅበረሰብ ውይይቱን በማካሄዳችን ምክንያት በግልና በጋራ ያገኘናቸውን ልምዶችና ጥቅሞች እንገመግማለን፣ እናሰላስላለንም። የስርዓተ ፆታ ሚናዎችንና የሴቶችን የከብት ሀብት ባለቤትነትንና ቁጥጥርን እንዲሁም ሴቶች በቤተሰብና በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቦታ በተመለከተ የታዩ አዎንታዊ ለውጦች እንለያለን። በተመሳሳይ መልኩ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች መከላከልንና መቆጣጠርን በተመለከተ የመጡ የዕውቀትና የተግባር ለውጦችን እንለያለን። በግልና በትናንሽ ቡድኖች በመሆን የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እናደርጋለን። አሳታፊ የሆኑ የአጠቃላይ ስብሰባ ውይይቶችና የግብረ መልስ ክፍለ ጊዜያትም ይኖሩናል።

4. በማህበረሰብ ውይይቱ ልምዶች ላይ በማሰላሰል የለውጥ ታሪኮችን ለይተው ይያዙ። በሁሉም የማኅበረሰብ ውይይቶች የተካፈሉ ተሳታፊዎችን በመማር ልምዳቸው ላይ እንዲያሰላስሉ ይጠይቋቸው። ተሳታፊዎች በትናንሽ የወንዶች እና የሴቶች ቡድኖች ተቧድነው በማኅበረሰብ ውይይቶች በመሳተፋቸው ያመጧቸውን ለውጦችና ያገኟቸውን ልምዶችን እንዲገመግሙና እንዲያሰላስሉ ይጠይቋቸው። የሴቶችና የወንዶች ቡድኖች በሚከተሉት የውይይት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ የሚያግዟቸውን የቡድን አመቻቾች ማስታወሻ ያዦችን ይመድቡላቸው።

## የማሰላሰል ጥያቄዎች

- በማኅበረሰብ ውይይቱ ላይ ያገኙት ተሞክሮ ምንድነው? በውይይቱ ውስጥ በጣም የሚያስታውሱት ጊዜ የትኛውን ነው?
- ስለ ስርአተ ፆታ የሥራ ክፍፍልና ስለ ሴቶች የእንስሳት ባለቤትነትና ቁጥጥር ያልዎትን አመለካከትና ግንዛቤ እንዲለውጡ የማኅበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜዎች እንዴት ሊያግዝዎት ችለዎል?
- በቤተሰብዎ ወይንም በማህበረሰብዎ ሴቶችና ወንዶች ሚናቸውን የሚያከናውበትና በከብት ሀብት ላይ ውሳኔ የሚሰጡባቸውን መንገዶች ለመለወጥ የማኅበረሰብ ውይይቱ በምን ዓይነት መንገድ እገዛ አደረገ?
- የማኅበረሰብ ውይይቶቹ በቤተሰብና በማኅበረሰብ ደረጃ ክርክሮችን አስነስተው ያውቃሉ? መልስዎ ‹አዎ› ከሆነ ‹ምንና እንዴት›?

- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ያልዎትን ዕውቀት፣ አመለካከትና ግንዛቤ ለመቀየር የማሕበረሰብ ውይይቶች እንዴት ሊረዳዎት ቻሉ
- የእንስሳት አያያዝና ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦችን አመጋገብን በተመለከተ ከበፊቱ የተለየ አሁን ምን ዓይነት የጥንቃቄ ባህርይ ያሳያሉ?
- እርስዎ በማኅበረሰብ ውይይቱ በመሳተፍዎ በቤተሰብዎና በጎረቤትዎ ውስጥ ምን ዓይነት ተጽዕኖ አሳርፈዋል?
- የማኅበረሰብ ውይይቱ በምን ዓይነት መልክ እንዲሻሻል ይፈልጋሉ? በትምህርቱ ሲሳተፉ ሆነ የተማሩትን ሲተገብሩ ምን ዓይነት ተግዳሮቶች ገጥሞዎታል?
- በመማርና በመተግበር ቡድች ውስጥ ያገኙዋቸውን ተሞክሮዎች እንዴት ይገመግሟቸዋል?
- በማኅበረሰብ ውይይቱ በመሳተፍም ያገኙዋቸውን ለውጦች ዘላቂ ለማድረግ በግልና በጋራ ምን ምን ያደርጋሉ?
- ትናንሽ ቡድኖች ውጤቶቻቸውን/መልሶቻቸውን ለአጠቃላይ ስብሰባ ያቀርባሉ። መልሶቻቸውን በፊሊፕ ቻርት ላይ ይጻፋና ከቀረቡት ውጤቶች /መልሶች ያገኟቸውን የጋራ የሆኑ ጭብጦችን ለየት ባለ ቀለም አጉልተው ያሳዩአቸው። የማህበረሰቡ መሪዎችና ባለሥልጣናት የመጨረሻውን ክፍለ ጊዜ እንዲሳተፉ ይጋብዟቸው። ባለሥልጣናትን የግምገማውንና የልምድ ልውውጥ ስብሰባዎችን እንዲከፍቱና እንዲዘጉ ማድረግ ሥራው ተቋማዊ ባለቤትና ተቀባይነት እንዲኖረው በማድረግ የተገኙት ለውጦች ዘላቂ እንዲሆኑ ይረዳል። በዕለቱ የግምገማው ሒደትና የዘላቂነት መርሐ ግብር ሲቀርብ በቪዲዮ እንዲቀረጽና ፎቶግራፎች እንዲነሱ አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

በዕለቱ ጥቂት ወንድና ሴት ተሳታፊዎችን በማኅበረሰብ ውይይቱ ላይ ስላላቸው ተሞክሮ ቁልፍ ትምህርቶች፣ በኑሯቸው ላይ ስለመጡ ለውጦችና ትምህርቶች እንዲሁም ትምህርቶቹንና ለውጦቹን ዘላቂ ለማድረግ የሚወጡ ዕቅዶችን በተመለከተ ቃለ መጠይቅ ያድርጉላቸው።

5. ተሳታፊዎቹን ስለሰሩዋቸው ትልልቅ ሥራዎች ካመሰገኗቸው በኋላ አሁን ክፍለ ጊዜው ለማለቅ መቃረቡን ይንገሯቸው።

የተሳትፎ ግብረ መልስ ቅኝት (participatory feedback survey) በመጠቀም የማኅበረሰብ ውይይቱን ሒደት ይገምግሙ። የሚከተሉትን የመሳሰሉ የግምገማ ጥያቄዎችን ያዘጋጁ።

- የውይይት ነጥቦቹ በማኅበረሰባችን ውስጥ የሚገኙትን ችግሮችን የሚፈቱና ተገቢነት ያላቸው ናቸው።
- ውይይቱ አስደሳች የነበረ ሲሆን የማኅበረሰቡ አባላት በውይይቶቹ የነቃ ተሳትፎ አድርገዋል።
- የማኅበረሰብ ውይይቱ የተደረገበት ቦታና ሰዓት ተገቢና አመቺ ነበር።
- በማኅበረሰብ ውይይቱ ተገቢ የሆኑ ሰዎች ተሳትፈውበታል።
- በማኅበረሰብ ውይይቱ የነበረኝ ተሞክሮ አስደሳች ከመሆኑ የተነሳ ከእንግዲህ በማኅበረሰብ ስብሰባዎች ላይ በንቃት ለመሳተፍ ብቃት እንዳለኝ ይሰማኛል።

"በጣም ረክቻለሁ"፣ "ረክቻለሁ"፣ "በመጠኑ ረክቻለሁ"፣ "አልረካሁም" ተብሎ የተጻፈባቸው ካርዶችን መሬት ላይ በአግድም ያስቀምጡ። ለተሳታፊዎቹ የተወሰኑ የግምገማ ዓረፍተ ነገሮች እንደሚያነቡላቸው ይንገሯቸው። አረፍተ ነገሮቹ በሚነበቡት ጊዜ ተሳታፊዎቹ በማኅበረሰብ ውይይቶቹ ላይ የእርካታቸውን መጠን በሚያሳዩ ካርዶች ላይ እንዲቆሙ ይጠይቋቸው። በመጀመሪያ እርስዎ እራስዎ ይህንኑ በማድረግ በተግባር ያሳዩአቸው።

አሁን የግምገማ ዓረፍተ ነገሮችን ያንብቡና ቡድኖቹ የእርካታቸውን መጠን እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው። ተሳታፊዎቹ በካርዶቹ ላይ ቆመው እንዳሉ የእርካታቸው መጠን ለምን እንደዚያ እንደመዘኑት ይጠይቋቸው። አስተያየቶቻቸውንና ግብረ መልሶቻቸውን በፊሊፕ ቻርቱ ላይ ይመዝግቡ።

የማኅበረሰቡን መሪዎች በመጋበዝ ተሳታፊዎቹን እንዲያመሰግኑና ለተገኙት ለውጦች ቀጣይነት እንደሚሰሩ ለተሳታፊዎቹ ቃል እንዲገቡ ካደረጓቸው በኋላ የማኅበረሰብ ውይይቱን ያጠናቁ።

በመጨረሻም ተሳታፊዎቹን ጊዜያቸው ሰጥተው በማኅበረሰብ ውይይቶቹ ላይ በመሳተፋቸውና የተለያዩ ጠቃሚ ሀሳቦችን በማቅረባቸው ያመስግኗቸው። ማስታወሻ ያዦችም የትናንሽ ቡድኖችን ውይይቶች በማሳለጥና እያንዳንዱን የማኅበረሰብ ውይይት በመሰነድ ስላበረከቱት ታላቅ አስተዋጽዖ ምስጋና ያቅርቡላቸው።

# አባሪዎች

## አባሪ 1፡ የተሳታፊዎች ቃለ ምልልስ ማጣሪያ ዝርዝር (ቼክ ሊስት)

1. በዚህ ውይይት መሳተፍ ምን ዓይነት ስሜት ይፈጥራል? ይህንን እንዴት ሊሉ ቻሉ?
2. አሁን በውይይቱ ያነሳናቸው ጉዳዮች እርስዎንና ቤተሰብዎን በግላችሁ በምን ዓይነት መንገድ ሊነካችሁ ይችላል?
3. በዚህ ውይይት በመሳተፍዎ ምን ተምረዋል? ወይንም ምን አግኝተዋል?
4. በዚህ ውይይት በመሳተፍዎ ስለ ስርዓተ ፆታና ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች አሁን አስቀድሞ ከሚያስቡት የተለዩ ያስባሉ?
5. የዚህ ውይይት አካል በመሆንዎ ለወደፊት ለየት ባለ መልኩ የሚሰሩት / የሚያከናውኑት ነገር አለ? እርስዎና በእርስዎ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎች ከነዚህ ስብሰባዎች መጠናቀቅ በኋላ በምን መልኩ ማስቀጠል ትችላላችሁ

## አባሪ 2፡ የማኅበረሰብ ውይይት ሪፖርት ንድፍ (template)

ወረዳ/ማኅበረሰብ ______________________________

የማኅበረሰብ ውይይቱ ቀን ______________________________

ውይይቱ የተካሄደበት ቦታ ______________________________

የተሳታፊዎች ቁጥር (ወንድ/ሴት)______________________________

አመቻቾች______________________________

ማስታወሻ ያዥች ______________________________

1. የውይይቱ ሰዓት፣ ቦታና አቅርቦቶች የተመቹና የተሳኩ ነበሩ የተሳኩበት/ያልተሳኩበት ምክንያት ምንድነው?
2. የቡድኑ ተለዋዋጭነት (የተሳታፊዎቹ የተሳትፎ መጠንና ውክልና) ምን ይመስል ነበር? ተሳታፊዎችን ለማነሳሳትና በንቃት እንዲሳተፉ ለማድረግ የተጠቀሙባቸው ምን ዓይነት ዘዴዎችና አቀራረቦች ውጤታማ ሆነው አገኟቸው?
3. በጥሩ ሁኔታ ያልተከናወነው ምንድነው? ለምን?
4. ምን ዓይነት ፈጠራ ወይንም ማስተካከያ ተጠቅመዋል?
5. ከውይይቱ ምን ዓይነት ዋና ጭብጦች (ዋና ዋና ሐሳቦች፣ ስምምነቶች፣ ቁልፍ ትምህርቶች) ተገኝተዋል?
6. ከውይይቱ ምን ዓይነት የእርምጃ/የድርጊት ነጥቦች ወጡ?
7. ወንዶችና ሴቶች በውይይቱ በመሳተፋቸው ምን ጥቅሞችን ያገኙ ይመስልዎታል?
8. በአጠቃላይ የማሕበረሰብ ውይይቱን እንዴት ይገመግሙታል?

9. የሚቀጥለው ስብሰባ የሚካሄደው መቼ ነው?

ቀን _______________ ሰዓት ____________________ ቦታ ________________________

# አባሪ 3፡ የማስታወሻ አያያዝ ዘዴዎች

- በማስታወሻው መያዝ ያለባቸው የሚከተሉት ናቸው። የውይይቱ ሂደት፣ ውይይት የተደረገባቸው ጉዳዮች፣ ግንዛቤዎች፣ ስምምነቶች፣ የእርምጃ ነጥቦችና ከማኅበረሰብ ውይይቱ የተገኙ ሆነው የጸሐፊውን ሐሳብ ያላካተቱ ጥቅሶች ናቸው።
- ሰዎች የተናገሩትን ሁሉ ቃል በቃል ለመፃፍ አይሞክሩ። ማጠቃለያዎችን ምልክቶችንና ምህጻረ ቃሎችን በመጠቀም የተፃፉ ጽሑፎች ቃል በቃል ከተጻፉ ጽሑፎች ይልቅ የተሻለ ተመራጭ ናቸው።
- ለጥቅስ የሚበቁ ዓረፍተ ነገሮች ካሉ በሚገባ አዳምጠው ይፃፏቸው።
- ተሳታፊዎቹ ያሏቸውን ነገሮች በምን ምክንያት እንዳሏቸው በጥሞና ይከታተሉ። ካሏቸው ነገሮች በስተጀርባ ምን ነገሮች እንዳለ ያስቡ። የሰውነት እንቅስቃሴ ቋንቋ ጠቃሚ የሆኑ ፍንጮች ሊሰጥ ይችላል።
- ሰዎች ምን እንደሚሉ ብቻ ሳይሆን የሚሏቸውን ነገሮች በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚሏቸው አስተውሉ።
- አመቻቾቹ ውይይቱን በሚያጠቃልሉበት ወቅት በትኩረት ያዳምጡ
- የውይይቱ አካሄድ የሚለወጥበት ጊዜ በሚገባ ያስተውሉ። ለምሳሌ ውይይቱ ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚገባበትን ጊዜ ወይንም አለመግባባቶች ወደ መግባባት የሚለውጡበትን ጊዜ ወይንም ስምምነቶች የሚደረሱበትን ጊዜ በጥሞና ያስተውሉ።
- ተሳታፊዎቹ በውይይቱ መጀመሪያ አካባቢ የሚሏቸውን ነገሮችና በመጨረሻ የደረሱባቸውን ነገሮች ያነፃፅሩ።
- በክለሳና በማሰላሰያ ክፍለ ጊዜዎች መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በንቃትና በትኩረት ማስታወሻ ይያዙ።
- ለሰነድ አያያዝ እንዲመች በፊሊፕ ቻርት ላይ የተፃፉትን የውይይቱ ውጤቶች ቁጥርና ቀን በሚገባ ይጻፉ።
- በስብሰባው መሃል ባሉ የዕረፍት ጊዜዎች ከተሳታፊዎቹ ጋር በመገናኘት ተሳታፊዎቹ ስለ ማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜዎቹ የተሰማቸውን ስሜት ለመረዳት ይሞክሩ።
- በተቻለ መጠን ውይይቱ እንዳለቀ ወዲያውኑ ከአመቻቹ ጋር በመሆን ማስታወሻዎቹን በመገምገም በሚገባ ያደራጁ።

# አባሪ 4፡ የአመቻች መመሪያዎች

ውጤታማ የሆኑ አመቻቾች የሚከተሉትን ያከናውናሉ

- ውይይቶችን ይመራሉ።
- በውይይት ላይ ባሉ አርዕስቶች ላይ የራሳቸውን ሐሳቦች ከማንጸባረቅ በመቆጠብ ገለልተኛ ይሆናሉ።
- ከሰዎች ጋር ሆኖ ሐሳቦችን ያሰላስላሉ፣ ይመረምራሉ።
- ሰዎች ከአመቻቹ ላይ እምነት እንዲኖራቸው በማድረግ መልካም ግንኙነት ይፈጥራሉ።
- ሰዎች የተለያዩ ዕይታዎችን ከግምት እንዲያስገቡ ያበረታታሉ
- ባሕልና ልምዶችን ያከብራሉ

## የማመቻቸትና የቡድን አስተዳደር ጠቃሚ ምክሮች

- ውይይቶች በቂ አየር ባላቸው ክፍሎች ወይንም ከቤት ውጭ ሊካሄዱ ይችላሉ።
- ተሳታፊዎቹ መሬት ላይ የሚቀመጡ ከሆነ እርስዎ ወንበር ላይ አይቀመጡ።
- ያልተማሩ ተሳታፊዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ አሳታፊ ዘዴዎችንና እንቅስቃሴዎችን ይጠቀሙ
- መረጃዎን ሲያቀርቡ ተሳታፊዎቹ በሚገባ እንዲረዱ የሚጠቀሙበት ቋንቋና የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ከአካባቢው ጋር የሚሄዱ መሆኑን ያረጋግጡ
- በአካባቢው የሚገኙ ምሳሌዎችንና ጉዳዮችን ይጠቀሙ።
- ተሳታፊዎችና ማስታወሻ ያዦች ግብረ መልስና የመረጃውን ፍሰት እንዲያገኙ ውይይቱን በማጠቃለል መግለጫ ይስጡ።
- ምቹ የሆነ የመማማሪያ አካባቢ በመፍጠር ውይይቱ እንዲቀጥል ያድርጉ። ለውይይቱ የተሰጠውን ሰዓት ተቆጣጥረው በሚገባ ይጠቀሙ።

## ውይይቶችን በሚያመቻቹበት/በሚያሳልጡበት ወቅት የሚከተሉትን ያድርጉ

- ተሳታፊዎች ብዙ ምላሾችን እንዲሰጡ ለማነቃቃት ክፍት የሆኑ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።
- ጥያቄዎቹን ከጠየቁ በኋላ ለተሳታፊዎቹ የማሰቢያ ጊዜ ይስጧቸው።
- ከተሳታፊዎቹ ጋር በቀጥታ አይን ለአይን በመተያየትና ስማቸውን በመጥራት ሰዎች ለውይይቱ አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ያበረታቱ።
- በሚገባ ለመረዳት በጥሞና ያዳምጡ መልዕክቶቹን በተለያዩ ቃላት በመግለጽ ውይይቱን ይምሩ።
- ብዙ ምላሾች ከተሳታፊዎቹ እንዲመጡ ያበረታቱ።
- የተሳታፊዎቹን መልዕክቶች የተለያዩ ቃላቶችን በመጠቀም በመግለጽና የበለጠ መረዳት እንዲኖር ያድርጉ። ለተሳታፊዎቹ ያልዎትን አድናቆት ይግለፁ።
- እርስዎ የተጠየቁትን ጥያቄዎች ተሳታፊዎች እንዲመልሱ በመጋበዝ ሌሎችም እንዲሳተፉ ያድርጉ።
- የበለጠ መረጃና የተለያዩ እይታዎችን ለማግኘት የምርመራ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።
- ማን እየተሳተፈ እንዳልሆነ በማስተዋል ይፈትሹ።
- ንቁ አድማጭ ይሁኑ። በዓይንዎ የተሳታፊዎችን የሰውነት ቋንቋ ምልክቶችን በማስተዋል ይከታተሉ።
- ውይይቱን አጠር አድርጎ ማጠቃለል ተሳታፊዎቹ የበለጠ እንዲረዱና ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ያደርጋቸዋል።

# አባሪ 5፥ በራስ አባባል የመግለጽና የማጠቃለል ዘዴዎች

- ገላጭ የሆነ ቋንቋ በመጠቀም የተነሱትን ሐሳቦች ይግለጧቸው።
- ተናጋሪዎቹ ሃሳባቸውን ለመግለጽ ብዙ ዓረፍተ ነገሮች ተጠቅመው ከሆነ ሐሳቦቹን አጠር አድርገው ያጠቃሉ።
- የተሳታፊዎችን ሃሳቦች በሚያጠቃልሉበት ወቅት በሚከተሉት ሀረጎች መጀመር ይችላሉ። "በትክክል ተረድቼ ከሆነ . ." ወይንም "እርስዎ የሚሉት …. ይመስለኛል"፣ "በትክክል አድምጬ ከሆነ እርስዎ ያሉት…"
- ማጠቃለያዎ ትክክል ስለመሆኑ የተናገረውን ሰው ማረጋገጫ ይጠይቁ። "እርስዎ የሚሉት… ይመስለኛል…። የተሳታፊዎቹ ማረጋገጫ የቃላት ብቻ ላይሆን ይችላል። እንደ ራስ ማነቃነቅ ያሉ እንቅስቃሴዎች የተሳታፊዎቹ መስማማት ወይንም አለመስማማት ሊገልጹ ይችላሉ።
- ማጠቃለያው ትክክል ነው የሚል ምላሽ ካላገኙ ተናገሪው የሰጧቸውን ሀሳቦች በድጋሚ እንዲያብራሩ በማድረግ ይህንኑ በድጋሚ አሳጥሮ ማጠቃለል ይቻላል፥ ፥ ይህንንም ለማድረግ አንዱ መንገድ ተናጋሪውን ክፍት የሆኑ ጥያቄዎችን ወይንም ለንግግራቸው ተጨማሪ ምክንያቶችን በሚከተለው መልክ መጠየቅ ይችላሉ። "አሁን ላነሷቸው ጉዳዮች ምሳሌ ሊሰጡኝ ይችላሉ?" "እባክዎ ስለዚህ ጉዳይ ተጨማሪ ነገሮችን ይንገሩኝ…" "…በትክክል መረዳቴን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ…"

- በውይይቱ የተነሱትን የተለያዩ ሀሳቦች በሚያጠቃልሉበት ወይንም በሚገልጹበት ጊዜ ሳይገልፁ ወይንም ሳያጠቃለሉ የቀሩ ሐሳቦች መኖር አለመኖራቸውን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተሳታፊዎችን በመጠየቅ ያረጋግጡ። "ሁሉንም ጭብጦች አካትቻለሁ..." "እስካሁን ድረስ ያነሳናቸው ነጥቦች ሁሉም ተጠቃለው ቀርበዋል..."

# አባሪ 6፡ የክትትል ሥራዎች የማጣሪያ ዝርዝር (ቼክሊስት)

ይህ ዝርዝር የማኅበረሰብ ውይይት አመቻቾች የማኅበረሰብ ውይይት ተሳታፊዎችን ለመከታተልና ለመደገፍ እንዲሁም የማኅበረሰብ ቡድኖች ሊወስዱ የተስማሙባቸውን እርምጃዎች አፈፃፀም ለመከታተል የተዘጋጀ ነው።

በእያንዳንዱ የማኅበረሰብ ውይይት መጨረሻ ተሳታፊዎቹ በግልና በቤተሰብ ደረጃና በጋራ በማኅበረሰብ ደረጃ ሊወስዱ ያቀዷቸውን እርምጃዎች ይለያሉ፡ ፡ የሃይማኖትና የማኅበረሰብ መሪዎች ለሌሎች የማኅበረሰብ ቡድኖች ተመሳሳይ እርምጃዎች እንዲወስዱ በማህበራዊና ሃይማኖታዊ ስብሰባዎች ለማሳመን ቃል ይገባሉ። ይህንኑ የሚከታተሉ የማህበረሰብ የክትትል ቡድኖች ይቋቋማሉ።

የማኅበረሰብ አመቻቾች በበኩላቸው የዕቅዶቹን ተግባራዊነት በመከታተል የባሕርይ ለውጥ ምልክቶች ካሉ ይህንኑ በመሰነድ ይይዛሉ።

የሚከተሉት የአመቻቾቹ የክትትል ሥራዎችና ከእያንዳንዱ የማህበረሰብ ውይይት ክፍለ ጊዜ በኋላ አመቻቾቹ የሚሰንዷቸው የለውጥ አመልካቾች ናቸው።

## በከብት እርባታ የሥርዓተ ፆና ሚና

### የማህበረሰብ አመቻቾች የክትትል ሥራዎች

- በቤት ለቤት ጉብኝት ጊዜዎችና በማኅበረሰብ ስብባዎች እንዲሁም የማኅበረሰብ ውይይት ተሳታፊዎች በተገኙባቸው ቦታዎች ሁሉ ተሳታፊዎቹ ከውይይቶቹ ምን እንደተማሩና ትምህርቱን እንዴት እየተጠቀሙበት እንዳሉ ይጠይቋቸው። ተሳታፊዎቹ ያገኙዋቸውን መረጃዎች ለሌሎች ለማካፈል ምን ዓይነት ጥረቶች እንዳደረጉና ከማን ጋር እንደተወያዩ ይጠይቋቸው። ውይይቶቹ ከቤተሰብ አባላትና በማኅበረሰብ ግንኙነቶች (በማህበረሰብ ስብሰባዎች፣ በሀይማኖት ዝግጅቶች፣ በገበያ ቦታ ላይ ወዘተ የተደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ።) እነዚህ አድርገው ከሆነ የሰዎቹን ስምና ፆታ በመጥቀስ ሰዎቹ ለጥያቄዎችዎ የሰጧቸውን መልሶች በጽሑፍ ይሰንዱ።

- በቤት ለቤት ጉብኝትዎ ወቅት ተሳታፊዎቹ በማኅበረሰብ ውይይቶቹ ወቅት ተወያይተው የተስማሙባቸውን ጉዳዮች በተግባር እያዋሉ መሆናቸውን የሚያሳዩ ድርጊቶችን ካሉ አስተውለው ይመዝግቧቸው።

- በማኅበረሰቡ ውስጥ አዎንታዊ ለውጦችን ያመጡ ሰዎች (ለምሳሌ ውሃ የሚቀዱና እንጨት የሚለቅሙ ወንዶች፣ የመኖሪያ ቤት ወይንም የከብቶችን ማደሪያ የሚያፀዱ፣ የቤት ውስጥ ሥራ የሚሠሩ፣ የቤት ውስጥ ሥራን ለወንዶች የሚያስተምሩ ሴቶች፣ ወንዶች የቤት ውስጥ ሥራን እንዲያከናውኑ የሚያግዙ ሴቶች፣ ዶሮ የሚያርዱ ሴቶች ወዘተ) ካሉ አስተውለው በማየት ማስታወሻ ይያዙ። በእያንዳንዱ ቤተሰብ ውስጥ ያዩዋቸውን ለውጦችን ይሰንዱ። ስለሌሎች የቤተሰብ አባላት ያገኙትንም ይጥቀሱ።

- በገበያ ቦታዎች በመገኘት ምን ያህል ሴቶች ከብቶችንና የእንስሳት ተዋጽዖ እየሸጡ እንደሆነና የትኞቹን ዝርያዎች (ለምሳሌ፡ በግ፣ ፍየል፣ በሬ) እየሸጡ መሆኑን በማስተዋል ተመልክተው የነዚህን ሴቶች ስም ይመዘግቡ። ሴቶች ከብት መሸጣቸውን ማኅበረሰቡ በምን መልክ እንደሚያየው ያጥኑ። ሴቶች በገበያ ውስጥ ከብቶችን ሲሸጡና ከብቶቹን በመግዛትና በመሸጥ ሒደት ውስጥ ሲሳተፉ የሚያሳዩ ፎቶግራፎችን ያንሱ።

- የኃይማኖትና የማኅበረሰብ መሪዎች በቤተክርስቲያንና በመስጊድ ወይንም በማኅበረሰብ ስብሰባዎችንና በሌሎች ማኅበራዊና ሐይማኖታዊ ዝግጅቶች ላይ የስርዓተ ፆታ እኩልነትና ሚዛናዊ የሥራ ክፍፍልን በተመለከተ የሚያውቁትን መረጃ በውይይት መልክ ለማህበረሰቡ እንዲያካፍሉ ያበረታቷቸው። የሐይማኖትና የማኅበረሰቡ መሪዎች ስለ ስርዓተ ፆታ እኩልነትና ስለ ሴቶች የሥራ ጫና በማኅበረሰቡ ስብሰባዎች ላይ የሚያነሷቸውን ሐሳቦች በማስተዋል ማስታወሻ ይያዙ። ማን እንደተናገረ፣ ምን እንደተናገረና መቼና የት እንደተናገረ በማስታወሻዎ ይያዙ።

- በውይይቶቹ ተሳታፊ የነበሩ ቢሆንም ምንም ለውጥ ያላመጡ ተሳታፊዎችን በመለየት እንዳይለወጡ ያደርጓቸውን ችግሮች ለማወቅ ጥረት ያድርጉ፡ ፡ በውይይቶቹ ተሳትፈው የተማሩትን በመተግበራቸው የተነሳ የቅጽል ስም የወጣላቸው ወይም የተፌዘባቸው ወንዶችና ሴቶችን ካሉ በመለየት ታሪኩን በማስታወሻ ይያዙ።

የለውጦችን የመጀመሪያ ምልክቶች ለይቶ ለመሰነድ የሚረዱ አመልካች ውጤቶች

- የሴቶች የሥራ ጫና መቀነስ ወይም አስቀድሞ ከሚሰሩት ሰዓት ያነሰ መስራት

- የወንዶች በቤት ውስጥ ሥራዎች ያላቸው ተሳትፎ መጨመር

- በቤተሰብ አባላት መካከል ያለው ተግባቦት፣ መረጃን መጋራት፣ ግልፅ ውይይትና የጋራ የሆነ ውሳኔ ሰጭነት መጨመር
- በቤተሰቡ ውስጥ በቤት ውስጥ ሥራ አዲስ ችሎታ ያገኙ ወይንም እየተለማመዱ ችሎታቸውን ለማዳበር ፍቃደኛ የሆኑ የቤተሰብ አባላት ዝርዝር
- የሴቶችን የሥራ ጫና በመጋራት የተሳተፉ ወንዶችን ዝርዝር (ሥራዎቹ የከብቶችን ማደሪያ ማጽዳት ውሃ መቅዳት ሰሐን ማጠብና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ።)
- የወንዶችን ባሕላዊ ሚና የተማሩ ሴት ተሳታፊዎችን ዘርዝር
- የወንድ የቤተሰብ አባላትን ልብስና የማብሰያ ዕቃዎችን ማጠብ፣ ቤት መጥረግ፣ ቂጣ መጋገር፣ ቡና ማፍላትና ምግብ ማብሰልን ያስተማሩ ሴቶች ዝርዝር
- በቤተሰብ ውስጥና በጎረቤት በማኅበረሰቡ ውይይት ስለተነሱ ጉዳዮችና ስለተወሰኑ ውሳኔዎች መረጃ የደረሳቸው ሰዎች ቁጥር
- በቤተሰብ ውስጥ የሚደረገውን መስተጋብር በተመለከተ የመጡ ለውጦች (ለምሳሌ በከብቶች ጉዳይ ሴቶች ያላቸውን ውሳኔ ሰጭነት በተመለከተ)
- በጋራ እርምጃዎች ላይ የመጡ ለውጦች (ለምሳሌ በግብይት ጉዳዮች)
- የሃይማኖትና የማህበረሰብ መሪዎች ስለ ስርዓቱ ፆታ ጉዳዮች አንስተው የተወያዩባቸው የጊዜ ድግግሞሽና የማኅበረሰብ ዝግጅቱ ዓይነት
- በገበያ ውስጥ ከብት ወይንም የከብቶችን ውጤቶች ሲሸጡ የተስተዋሉ ሴቶች ስሞች (ሴቶች የሸጧቸውን ከብቶች ዝርያዎች ይጥቀሱ።)
- ሴቶችና ወንዶች ከማኅበረሰብ ውይይቶቹ የተማሯቸውን በተግባር በሚያውሉበት ወቅት የገጠሟቸውን የስርዓተ ፆታ ስውር ዘይቤዎች (gender stereotype) ታሪኮች
- በማኅበረሰብ ውይይቶች ወቅት ወንዶች የተማሩትን ሲተገብሩ የሚያሳዩ ፎቶግራፎች (ፎቶግራፎቹ ወንዶች ውሃ ሲቀዱ፣ የከብቶችን ቤቶች ሲያጸዱ፣ ህፃናትን ሲንከባከቡ፣ ምግብ ሲያበስሉ የሚያሳዩ ሊሆኑ ይችላሉ)

## ከእንስሳት ወደ ሰውየሚላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ያሉ ዕውቀቶችች አመለካከቶችና ልምዶች

### የማህበረሰብ አመቻቾች ተግባራት

- የቤት ለቤት ጉብኝት በሚያደርጉበት ወቅት ተሳታፊዎቹ ከውይይቶቹ ምን ተምረው እንደነበርና በተማሩት ነገር ምን እያደረጉበት እንደሆነ ይጠይቋቸው። ከእንስሳት ወደ ሰውየሚተላለፉ በሽታዎች በተመለከተ የተማሩትን ለቤተሰቦቻቸው ለጎረቤቶቻቸው እንዲሁም በተለያዩ በማህበረሰብ ስብሰባዎች ተገኝተው ለማጋራት ምን ጥረት አድርገው እንደሆነ ይጠይቋቸው።
- የቤት ለቤት ጉብኝት በሚያደርጉበት ወቅት ምን ምን ደህንነታቸውን የሚያስጠብቁ የከብት እርባታ ሥራዎችን እንደሚሠሩና ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦችን አመጋገብ እንደሚከተሉ በማስተዋል ማስታወሻ ይያዙ። ድርጊቶቹ ወተት ማፍላትንን ሥጋን ማብሰል፣ የታመሙ እንስሳትን ከነኩ በኋላ እጅ መታጠብን፣ ከእንስሳት ጋር አንድ ቤት ውስጥ አለማደርን፣ የተመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ
- በውይይቶቹ ምክያት ለውጥ ያመጡ ተሳታፊዎችን ስምና እያንዳንዱ ቤተሰብ ያመጣውን ለውጥ ይመዝግቡ። ስለሌሎች የቤተሰቡ አባላትም የታዘቡትን ይመዝግቡ።
- በገበያ ውስጥ የአዙሪት በሽታ ያለባቸውን በጎች እየተሸጡ እንደሆነ ያጣሩ። እንደዚህ ዓይነት በጎች እየተሸጡ ከሆኑ ሻጮቹ ጉዳዩን ለእንስሳት ጤና ባለሞያዎች አሳውቀው እንደሆነ ይጠይቋቸው።
- ደህንነታቸውን ለመጠበቅ እንደ ቦት ጫማ፣ ጭንብል፣ ጓንትና የመሳሰሉትን የመከላከያ ዕቃዎችን እየተጠቀሙ ያሉ ሴቶችና ወንዶች ካሉ ፎቶግራፍ ያንሷቸው።
- የሃይማኖት መሪዎች፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ፣ በማህበረሰብ ስብሰባዎች፣ በኃይማኖት በዓላት ወቅት ወይንም ቤት ለቤት ጉብኝት በሚያደርጉባቸው አጋጣሚዎች ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች ያገኙትን ዕውቀት ለሌሎች እንዲያካፍሉ ያበረታቷቸው።
- የሃይማኖትና የማኅበረሰብ መሪዎች በማኅበረሰብ ስብሰባዎች ላይ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ሲናገሩ በሚገባ አስተውለው ማስታወሻ ይያዙ። ማን ምን እንዳለና መቼና የት እንዳለ በሚገባ ይፃፉ።
- በማኅበረሰብ ውይይቶቹ ተሳታፊ የነበሩ ቢሆንም ምንም ለውጥ ያላመጡ ሰዎችን ለይተው በማወቅ ለውጥ ሊያመጡ ያልቻሉበትን ምክንያት ለማወቅ ጥረት ያድርጉ።

- በበዓላትና ድግስ በሚኖርባቸው ጊዜያት በተሳታፊዎች ቤቶች በመገኘት ተሳታፊዎቹ ጥሬ ሥጋ ወይንም የበሰለ ስጋ፣ የተፈላ ወይንም ያልተፈላ ወተት እየተጠቀሙ እንደሆነ አስተውለው ፎቶግራፍ ያንሱ

## የለውጦችን የመጀመሪያ ምልክቶችን ለይቶ ለመሰነድ የሚረዱ አመልካች ውጤቶች

- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች እንዳይተላለፉ ለማድረግ እርምጃ የወሰዱ (በአባወራ ወይንም በእማወራ የሚመሩ) ቤተሰቦች ዓይነት
- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች እንዳይተላለፉ ተሳታፊ ቤተሰቦችና ወንዶችና ሴቶች የወሰዷቸው የእርምጃ ዓይነቶች
- በቤተሰብ ውስጥና በሰፈሩ በመረጃ መጋራት ተደራሽ የሆኑ የቤተሰብ አባላት ቁጥርና ፆታ
- የሀይማኖትና የማኅበረሰቡ መሪዎች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን አደጋ በተመለከተ መልዕክት ያስተላለፉባቸው የማኅበረሰቡ ዝግጅቶች ዓይነትና ቁጥር
- ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመቆጣጠር እርምጃ የወሰዱ የቤተሰብ አባላት ፎቶግራፎች
- ስለታመሙ እንስሳቶቻቸው ለእንስሳት ሐኪሞች ያሳወቁ ሴቶች ዝርዝር
- የታመሙ እንስሳቶቻቸውን ወደ እንስሳት ጤና ኬላ ያመጡ ሴቶች ዝርዝር

## የሴቶች የከብት ሀብት ባለቤትነትና ቁጥጥርን በተመለከተ ያሉ አመለካከቶችና ድርጊቶች

የአመቻቾት የክትትል ተግባራት

- በቤት ለቤት ጉብኝት ወቅት፣ በማኅበረሰቡ ስብሰባዎች ሆነ የማኅበረሰብ ውይይቶቹን ተሳታፊዎች በሚያገኙበት ጊዜ ሁሉ ከውይይቶቹ ምን እንደተማሩና የተማሩትን ትምህርት እንዴት እየተጠቀሙባቸው እንደሆነ ይጠይቋቸው። ተሳታፊዎቹ ያገኟቸውን መረጃዎች ለሌሎች ለማካፈል ምን ዓይነት ጥረቶች እንዳደረጉና ከማን ጋር እንደተወያዩ ይጠይቋቸው። ውይይቶቹ ከቤተሰብ አባላትና በማኅበረሰብ ግንኙነቶች (በማኅበረሰብ ስብሰባዎች፣ በኃይማኖት ዝግጅቶች፣ በገበያ ቦታ ላይ ወዘተ) የተደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ፈጽመው ከሆነ የሰዎቹን ስምና ፆታ በመጥቀስ ሰዎቹ ለጥያቄዎችዎ የሰጧቸውን ምላሾች በጽሑፍ ይሰንዱ።
- በቤት ለቤት ጉብኝት ወቅት ከተለያዩ የቤተሰቡ አባላት ጋር በመነጋገር ከማኅበረሰብ ውይይቶቹ የተገኙና የሴቶችን የከብት ሀብት ባለቤትነትንና ቁጥጥርን የሚመለከቱ ጉዳዮች ለሕብረተሰቡ መድረሳቸውንና በጉዳዮቹ ላይ ውይይቶች መደረጋቸውንና አለመደረጋቸውን ያጣሩ።
- በባልና ሚስት መካከል ውሳኔ ሰጭነትን፣ ከከብቶች የተገኘ ገቢንና የከብቶችን ባለቤትነትና ቁጥጥር የተመለከቱ ስምምነቶች ወይንም የተደረጉ ለውጦች መኖር አለመኖራቸውን ያጣሩ።
- ውሳኔ የመስጠት አቅምንና ከከብቶች የሚገኘውን ገቢ በተመለከተ የተለወጠውን የስርዓተ ፆታ ግንኙነት ሕፃናት እያወቁት መሆኑንና እናቶችና አባቶች ይህንኑ ለልጆቻቸው እያስተማሩ መሆን አለመሆኑን ያጣሩ።
- በማኅበረሰቡ ውስጥ ሴቶች በማኅበረሰብ ስብሰባዎች ወይንም ውሳኔ በሚሰጥባቸው የእርባታ ቡድኖች ውስጥ መሳተፍ አለመሳተፋቸውን ያጣሩ። እነዚህን ሴቶችና ባለቤቶቻቸውን በቤተሰባቸው ውስጥ እየተለወጠ ስላለው የስርዓተ ፆታ ግንኙነት በማነጋገር ማስታወሻ ይውሰዱ።
- በገበያ ቦታዎች በመገኘት ሴቶች ከብቶችንና የእንስሳት ተዋፅዖ እየሸጡ እንደሆነና የትኞቹን ዝርያዎች (ለምሳሌ፡ በግ፣ ፍየል፣ በሬ) እየሸጡ እንዳሉ በማስተዋል ተመልክተው የነዚህ ሴቶች ስሞች ይመዝግቡ። ከብቶችና ከከብቶች የሚገኘውን ገቢ በተመለከተ ውሳኔ እንዴት እንደሚሰጡ እንዲሁም ሴቶች ከብቶችን መሸጣቸውን ማሕበረሰቡ በምን መልክ እንደሚያየው ይጠይቋቸው። ሴቶች በከብቶች ገበያ ላይ ከብቶችን ሲሸጡና ከብቶችን በመግዛትና በመሸጥ ሂደት ውስጥ ሲሳተፍ ፎቶግራፍ ያንሷቸው።
- የሃይማኖትና የማኅበረሰቡ መሪዎች በማኅበረሰቡ ስብሰባዎች (በእምነት ቦታዎች፣ በማኅበረሰብ ስብሰባዎች፣ በቤት ለቤት ጉብኝቶች ወቅት በማኅበራዊ ኃይማኖታዊ ዝግጅቶች) ላይ የመተማመንን፣ ነፃ ውይይቶችን የማድረግንና የመማከርን አስፈላጊነት የሚመለከቱ መረጃዎችንና መልዕክቶችን እንዲያስተላልፉ ያበረታቷቸው። እነዚህን ተግባራት የከብቶችን ሀብት ባለቤትነትንና ቁጥጥር እንዲሁም ከከብቶች የሚገኘውን ገቢ በሚመለከቱ ጉዳዮች ማህበረሰቡና ቤተሰቦች ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው እንዲመክሩ ያበረታቷቸው።
- በማኅበረሰብ ስብሰባዎችና በስልጠና የተሳተፉት ሴቶች በማኅበረሰቡ ስብሰባዎችና በስልጠና የተሳተፉት ዝርዝር የሃይማኖት መሪዎችና የማኅበረሰብ መሪዎች ሴቶች በከብቶች ላይ ስላላቸው ባለቤትነትና ቁጥጥርና ገቢን በተመለከተ በማኅበረሰብ ስብሰባዎች ላይ ሲናገሩ አስተውለው ማስታወሻ ይያዙ።

- ማን ምን እንደተናገረና መቼና የት እንደተናገረ በጽሑፍ ይያዙ።
- ምንም ለውጥ ያላመጡ ተሳታፊዎችን በመለየት ለውጡን ከማምጣት ያገዷቸውን ምክንያቶች ፈልገው ይወቁ።

## የለውጦችን የመጀመሪያ ምልክቶችን/ለይቶ ለመሰነድ የሚረዱ አመልካች ውጤቶች

በቤተሰብ ውስጥ የውሳኔ ሰጭነት ሁኔታ መሻሻል

- የከብቶችን ባለቤትነትንና ቁጥጥርን እንዲሁም ከከብቶች የተገኘ ገቢን በተመለከተ በባልና በሚስት እንደሁም በሌሎች የቤተሰቡ አባላት መካከል የሚደረግ ግልጽ ውይይት መኖር
- በባልና በሚስት መካከል መተማመንና መከባበር መኖር
- ከብቶችን የመግዛትንና የማስወገድን/የመሸጥን እንዲሁም ከከብቶች የሚገኘውን ገቢ በተመለከተ የሴቶች ሃሳቦቻቸውን ወይም ዕቅዶቻቸውን ለማቅረብ ችሎታና በራስ መተማመን መኖር
- ከከብቶች የሚገኝን ገቢ የመቆጣጠርና በገቢው ምን መደረግ እንዳለበት ውሳኔ መስጠት አቅም ማደግ
- የሴቶች ከከብቶች የሚገኘውን ገቢ መጠንና አጠቃቀም በተመለከተ ሴቶች ባሎቻቸውን የመጠየቅና ተጠያቂ ለማድረግ ያላቸው በራስ መተማመንና ችሎታ ማደግ
- የሕፃናት በከብቶች ባለቤትነትና ቁጥጥር እንዲሁም ከከብቶች በሚገኘው ገቢ አጠቃቀም ላይ በሚደረጉት ምክክሮችና ውሳኔዎች ላይ ተሳትፎ መኖር
- የከብቶችን ባለቤትነትና ቁጥጥር በተመለከተ የተሻሻለ ተግባቦት፣ የመረጃ ልውውጥ፣ ግልፅ ውይይትና የጋራ ውሳኔ ሰጭነት በቤተሰቡ አባላት መካከል መኖር
- ሴቶች ከብቶችንና ከከብቶች የሚገኘው ገቢ እንዲሁም የገቢውን አጠቃቀም በእኩልነት የሚወስንባቸው ቤተሰቦች ዝርዝር
- የከብቶች ሽያጭና ከሽያጩ የተገኘውን ገቢና አጠቃቀሙን በተመለከተ የተነሱት ቅራኔዎችና ቅራኔዎቹ የተፈቱባቸው መንገዶች
- በጋራ የእርምጃ አወሳሰድ ላይ የታዩ ለውጦች (ለምሳሌ ገበያ ነክ ውሳኔዎችና በገበያ ላይ የተደረጉ ውሳኔዎች)

## ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታችን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንፃር ያሉ ተቋማዊና መዋቅራዊ ጉዳዮች

### የአመቻቾች የቁጥጥር ስራዎች

- በቤት ለቤት ጉብኝት ጊዜዎች ወይንም በማኅበረሰብ ስብሰባዎች እንዲሁም የማኅበረሰብ ውይይት ተሳታፊዎች በተገኙባቸው ቦታዎች ሁሉ ተሳታፊዎች ከውይይቶቹ ምን እንደተማሩና ትምህርቱን እንዴት እየተጠቀሙበት እንዳሉ ይጠይቋቸው። ተሳታፊዎቹ ያገኟቸውን መረጃዎች ለሌሎች ለማካፈል ምን ዓይነት ጥረቶች እንዳደረጉና ከማን ጋር እንደተወያዩ ይጠይቋቸው። ውይይቶቹ ከቤተሰብ አባላትና በማኅበረሰብ ግንኙነቶች (በማህበረሰብ ስብሰባዎች፣ በኃይማኖት ዝግጅቶች፣ በገበያ ቦታ ላይ ወዘተ) የተደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህን ፈፅመው ከሆነ የሰዎቹን ስምና ፆታ በመጥቀስ ሰዎቹ ለጥያቄዎችዎ የሰጧቸውን ምላሾችን በጽሑፍ ይሰንዱ።
- በቤት ለቤት ጉብኝትዎ ወቅት የተለያዩ የቤተሰብ አባላትን በማነጋገር የሚከተሉትን ፈልገው ያግኙ።
- የወንዶችና የሴቶችን መስተጋብራዊ አቅምና ለመረጃና ለምክር አገልግሎቶች ያላቸውን ተደራሽነት የሚመለከቱ ከውይይቱ የተገኙ መረጃዎችን መጋራት መኖሩን
- ከውጭ ከሚመጡ ሠራተኞች (ለምሳሌ፡የልማት ሠራተኞች፣ የከብቶች ጤና አጠባበቅ ሠራተኞች ወዘተ) ጋር በሚኖሩት ውይይቶች ሴቶችና ሕፃናት መመከራቸውና መሳተፋቸውን
- በቤተሰብ ጉብኝትዎ ወቅት ባሎች ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን በውይይታችሁ እንዲሳተፉ ያድርጉና እያደረጉ እንደሆነ ያስተውሉ።

- የቤቱን አባወራና ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በስብሰባ በስልጠናና በመስክ ቀናት ማን መሳተፍ እንደሚችል የሚደረጉ ውሳኔዎች በምን ዓይነት መንገድ እንደሚደረጉ ይጠይቋቸው።
- በሴቶች ላይ የሚጣሉ የመንቀሳቀስ ገደቦች (ለምሳሌ ወደ ገበያ ወደ ሥልጠና ቦታዎች፣ የምክር አገልግሎት ወደሚሰጥባቸው ቦታዎች መሄድን) በተመለከተ በምን መልኩ ሴቶች ለመረጃዎች ያላቸውን ተደራሽነት፣ የተለያዩ ክህሎቶች የማግኘታቸውን ዕድልና የቤተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅና ምርታማነትን ለማሳደግ ሊኖራቸው የሚችለውን አቅም እንደሚጎዳው ይወያዩ።
- ሴቶችን በስልጠናና በምክር አገልግሎት ያላቸውን ተሳትፎ በተመለከተ የቤተሰቡን ዕይታና በመካከላቸው የሚነሱ ክርክሮች ምን እንደሆኑ ለማወቅ ይሞክሩ። በተጨማሪም ሴቶች በስልጠናዎች፣ በማህበር ቡድኖችና በመሳሰሉት እንዲሳተፉ ቤተሰቡ የሚሰጣቸውን ድጋፎች ወይንም የሚወስዷቸውን እርምጃዎች ለማወቅ ጥረት ያድርጉ።
- ሴቶች በማኅበረሰቡ ውይይቶችና በማኅበረሰቡ ቡድኖች ውስጥ ተሳትፎ በማድረግ በተቋሞችና በመዋቅሮች ላይ ተፅእኖ የሚያሳርፉ ከሆነ ይህንኑ እውነታ በማስታወሻ ይያዙ።
- በገበያ ቦታዎች በመገኘት ምን ያህል ሴቶች ከብቶችንና የእንስሳት ተዋፅዖ እየሸጡ እንደሆነና የትኞቹን የከብት ዝርያዎች (ለምሳሌ፡ በግ፣ ፍየል፣ በሬ) እየሸጡ መሆኑን በማስተዋል ተመልክተው የነዚህን ሴቶች ስም ይመዝግቡ። ሴቶች ከብት መሸጣቸውን ማኅበረሰቡ በምን መልክ እንደሚያየው ያጥኑ። ሴቶች በገበያ ውስጥ ከብቶችን ሲሸጡና ከብቶችን በመግዛትና በመሸጥ ሂደት ውስጥ ሲሳተፉ የሚያሳዩ ፎቶግራፎችን ያንሱ።

## የለውጦችን የመጀመሪያ ምልክቶች ለይቶ ለመሰነድ የሚረዱ አመልካች ውጤቶች

- የሴቶች በስብሰባዎች፣ በማማከር አገልግሎቶችና በስልጠናዎች ያላቸው ተሳትፎ መጨመር
- ባለሙያዎች የቤት ለቤት ጉብኝት በማድረግ ውይይቶችን በሚያደርጉበት ጊዜ የሴቶች ተሳትፎ መኖር
- ዕውቀትን ለማጋራት በሚከናወኑ ዝግጅቶችና በማኅበረሰቡ ስብሰባዎች ላይ ሴቶች እንዲገኙ ድጋፍ የሚያደርጉ ወንዶች ቁጥር መበርከት
- በገበያዎች፣ በስልጠናዎችና በተለያዩ ሕዝባዊ ቦታዎች መገኘታቸውን ሪፖርት የሚያደርጉ ሴቶች ቁጥር መጨመር
- በከብት ገበያዎች ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሴቶች ቁጥር መጨመር

# አባሪ 7፡ የለውጥ ታሪኮችን ለመሰነድ የሚውል የማጣሪያ ዝርዝር (ቼክሊስት)

ይህ መሣሪያ በአንድ የውይይት ክፍለ ጊዜ ወይንም በተከታታይ የውይይት ክፍለጊዜዎች ምክንያት የተገኙ ለውጦችን ለመሰነድ ያገለግላል።

| | |
|---|---|
| ትምህርቱን ማስታወስ | በማኅበረሰብ ውይይቱ ምን ጉዳዮች ላይ ውይይት ተደረገ<br>ከማህበረሰብ ውይይቱ ምን ተማራችሁ? |
| ዕውቀትን ማካፈል | ተሳታፊ<br>ከማህበረሰብ ውይይቱ ያገኙትን ትምህርት ለሌሎች አጋርተዋል?<br>መረጃዎቹን በማጋራት ረገድ ያሎትን ተሞክሮ ይንገሩን<br>- የቤተሰቡ አባላት<br>- ጎረቤትዎ<br>- ጓደኞችዎ<br>- ሌሎች ሰዎች<br>መረጃዎችን የማጋራት ሂደቱ የትና በምን ዓይነት መንገድ ተከናወኑ? ሰዎች ስለመረጃው ምን ተሰማቸው?<br>ምርመራ<br>መረጃውን ለማንም አላጋሩ እንደሆነ እንዲያጋሩ የገደብዎት ችግር ምን ነበር?<br>በሚቀጥለው ምን ሊያደርጉ አስበዋል? ይህን ለማድረግ ምን ዓይነት ድጋፍ እንዲደረግሎት ይፈልጋሉ? ማን ድጋፍ እንዲያደርግሎት ይሻሉ?<br>የቤተሰብ አባላት<br>በቤተሰብዎ ውስጥ ምን ጉዳዮችን እንደተነጋራችሁ ይንገሩን።<br>በቤተሰብዎ ውስጥ ባለቤትዎ፣ አባትዎና እናትዎ ወይንም ሁለቱም ለእርስዎ ምን አጋርተዎት እንደሆነ ይግለፁልን።<br>መረጃውን እንዴት አገኙት? በተጋራችሁት መረጃዎች ላይ ስምምነት ላይ ደረሳችሁ?<br>ከማህበረሰብ ውይይቶች የተገኙትን መረጃዎች ሌላ ማን አጋርቶት ያውቃል? ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?<br>በቤተሰብ ውስጥ መረጃ መጋራትን እንዴት አገኙት?<br>ብቃት እንዳገኙ ተሰማዎት? ጠቃሚ ነበር?<br>ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በሚመለከት የሴቶችና የወንዶች የሥራ ክፍፍል፣ የውሳኔ አሰጣጥ፣ የሀብት አያያዝ ምን እንዲመስል ይፈልጋሉ? በዚህ ረገድ ያልዎት ራዕይ ምንድነው? |

| | |
|---|---|
| ትምህርቱን ማስታወስ | በማኅበረሰብ ውይይቱ ምን ጉዳዮች ላይ ውይይት ተደረገ<br>ከማህበረሰብ ውይይቱ ምን ተማራችሁ? |
| ዕውቀትን መተግበር | ምርመራ<br>በቤተሰብዎ ውስጥ በማኅበረሰብ ውይይቶቹ ምክንያት የስርዓተ ፆታ ግንኙነቶችንና ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን በተመለከተ ምን ተለወጠ? (ለውጦቹ የስርዓተ ፆታ ግንኙነቶችን ለምሳሌ የስርዓተ ፆታ የሥራ ክፍፍልን፣ ውሳኔ የመስጠት አቅምንና በከብት ሐብት ላይ ያለን ተደራሽነትንና ቁጥጥርን የተመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ)<br>• የቤተሰብዎ አባላት ከዚህ በፊት የማይፈፅሟቸውን ባሕርይ ወይንም ተግባራት ሲፈፅሙ አስተውለዋል?<br>• የቤተሰብ አባላቱ ከዚህ በፊት የማያደርጉትን ነገር እንዲያደርጉ እርስዎ አስተምረዋል? ስለ አዲሶቹ ተግባራት ድርጊቶች ምን ተሰማቸው? ምሳሌዎችን ይስጡ።<br>ምንም የአዲስ ዕውቀት ትግበራ ከሌለ ላለመኖሩ ምክንያቶቹን ይወቁ።<br>በማህበረሰብ ውይይቶች በማሳተፍዎ ምን ጥቅም ያገኛሉ?<br>• ስለ ባህላዊ ተፅዕኖዎች ማወቅ<br>• የአመለካከት ለውጥ<br>• የተግባር ለውጥ እንዳይኖር እንቅፋት የሚፈጥሩ የማህበረሰቡን ደንቦችና እሴቶች የመሟገት ችሎታ<br>• በቤተሰብ ውስጥ የመጡ ለውጦች<br>• ግልጽ ውይይት፣ ትብብር፣ የተሻለ መረዳት፣ አዎንታዊና አሳታፊ ግንኙነት፣ ፍሬያማ የሰዓት አጠቃቀም፣ አዳዲስ ክህሎቶች፣ ለመረጃ ያለው ተደራሽነት፣ ፍትሐዊ የስርዓተ ጾታ የሥራ ክፍፍል ወዘተ |
| አውድ/ዳራ መረጃ | • ስም፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ የትምህርት ደረጃ<br>• የቤተሰብ ብዛት<br>• ከወረዳ ከተማ ያለው ርቀት<br>• ቦታ፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ<br>• የእርሻ ስነ ምህዳር<br>• ከፍታ፣ የአየር ንብረት፣ አፈር፣ ዝናብ፣ እፅዋት ወዘተ<br>• የመሬት መጠን<br>• ሰብሎችና የከብት ዝርያዎች<br>• አመራር/አባልነት - የሕብረት ሥራ ማህበራት፣ የማህበረሰብ የርቢ ቡድኖች፣ የግብይት ቡድኖች... ወዘተ<br>• መሠረተ ልማት - መንገዶችና የገበያ ተጠቃሚነት |

# አባሪ 8፡ የቃላት መፍቻ

ስርዓተ ፆታ፡(Gender) -በባሕል ላይ የተመሰረቱ ከሴቶችና ከወንዶች የሚጠበቁ ሚናዎችና ባሕሪዎች ናቸው። ቃሉ ማህበረሰቡ የመሠረታቸውንና በባዮሎጂ (በተፈጥሮ) የተወሰኑትን የወንዶችና የሴቶችን ገፅታዎች ለይቶ ያያል። ፆታ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ባዮሎጂካዊ (ተፈጥሯዊ) ልዩነቶች የሚመለከት ሲሆን ስርዓተ ፆታ ደግሞ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያሉትን ማህበራዊ ግንኙነቶች ይመለከታል። ስለሆነም ስርዓተ ፆታ የሚመለከተው ወንዶችንና ሴቶችን ሳይሆን በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነትና ይህ ማህበራዊ ግንኙነት እንዴት እንደተመሠረተ ነው። የሥርዓተ ጾታ ግንኙነቶች እንደየአግባቡ/ዐውዱ የሚለይ ሲሆን ሁኔታዎች ሲለዋወጡ አብሮ የሚለዋወጡ ናቸው።

የስርዓተ ጾታ የሥራ ክፍፍል (gender division of labour) - ለሴቶችና ለወንዶች ለየብቻ የተመደቡ ተግባራት፣ ሥራዎችና ሐላፊነቶች

ተጠቃሚነት (Access) - ሀብትን ለመጠቀም ያለ ዕድል

ቁጥጥር (Control) - ሀብትን እንዴት መጠቀም እንደሚገባና ሀብቱን ማን ለመጠቀም እንደሚችል የመወሰን ሀይል

የስርኣተ ፆታ ግንኙነት (Gender Relation) - በቤት ውስጥ፣ በገበያ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ፣ በቡድኖችና በድርጅቶች ባሉ ሰዎች መካከል ካሉ ግንኙነቶች ጋር የተጣመሩ ከሰዎች የሚጠበቁ ነገሮች፣ ትብብሮች ወይንም የድርድር ተለዋዋጭነት

መዋቅሮች (Struture) - አካባቢን፣ ማህበራዊ ደንቦችን፣ እውቅናን፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰጠውን አንፃራዊ ቦታና የመሳሰሉትን የሚወስኑ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ተቋማዊ ህጎች። ተቋማዊ ህጎቹ ግለሰቦችና ተቋማት ለሚፈጽሟቸው ድርጊቶች መሠረት ናቸው።

ማብቃት (Empowerment) - ስልታዊ የሕይወት ምርጫ የማድረግ መብታቸውን የተነፈጉ ሰዎች ይህንንን የማድረግ ብቃት እንዲያገኙ የሚደረግበት ሂደት።

የስርዓተ ፆታ እኩልነት (gender Equality) - በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሴቶችና ወንዶች በተፈጥሮ ወንድ ወይም ሴት በመሆናቸው ምክንያት ሳይነፈጉ ፍትሕና እኩልነት በሰፈነበት መንገድ የተለያዩ ጥቅሞችን ለማግኘት፣ ለመጠቀም፣ ለመቆጣጠርና አድሏዊ ያልሆኑ ዕድሎች፣ ህጎችን፣ ዕቃዎች፣ አገልግቶሎች በማህበረሰቡ ውስጥ የማግኘት መብት።

Zoonotic diseases- ከእንስሳት ወደ ሰውና ከሰው ወደ እንስሳት የሚተላለፉ በሽታዎች።

ሆኖም በዚህ መመሪያ ውስጥ ቃሉ የሚያመለክተው ያልበሰሉ ወይንም ያልተቀቀሉ ከእንስሳት  የሚገኙ ምግቦችን በመመገብ ወይንም የመከላከያ መሳሪያ ሳይጠቀሙ ከእንስሳት ጋር በመነካካት ከታመሙ እንስሳት ወደ ሰዎች  የሚተላለፉ በሽታዎችን ነው።

# ማጣቀሻዎች

Desta, H., Kinati, W., Alemu, B., Mulema, A. and Wieland, B. 2017. Women and men in livestock production. Poster. November 2017. Nairobi, Kenya: ILRI. https://hdi.handle.net/10568/91712

Kabeer, N. 1999. Resources, Agency and Achievements: Reflections on measurement of women's empowerment. Development and Change 30:435-464.

Kiristjanson, P., Waters-Bayer, A. Johnson, N. Tipilda, A., Niuki, J., Baltenweck, I., Grace, D. and MacMillan, s. 2010.

Livestock and women's livelihoods: A review of the recent evidence. Discussion paper No. 20. Nairobi, Kenya ILRI, https:hdl.handle.net/10568/3017.

Pyburn, R. and Eerdewjk, jk, A. van 2016. A different kettle of fish? Gender integration in livestock and fish research. Volendam: LM publishers. https://hdi.handle.net/10568/76684.